የማርቆስ ወንጌል የትምህርት መማሪያ ሞጁል

ሊድስታር ስነ-መለኮት ኮሌጅ

ግንቦት 2011

ማውጫ
የትምህርቱ መግቢያ
የትምህርቱ ዓላማ
ክፍል አንድ
የትምህርቱ ዋና ሃሳብ፡ የኋላ መረጃ
1. ጸሃፊው
2. ቦታውና ተደራሲያኑ
3. ሶስቱ በግልጽ የሚታዩ ጭብጦች
የማርቆስ ወንጌል ቅደም ተከተል
4. ባህርያቶቹ
5. ለማን ተጻፈ
6. የማርቆስ ወንጌል አበርክቶው
7. እንዴት ተቀናጀ (ቅንጅቱ)
8. ስነ መለኮታዊ ጭብጡ
ክፍል ሁለት
ማርቆስ ለሚያነቡ ጥያቄዎች
የመግቢያ ጉዳዮች
መቅድም
ወንጌል
የእግዚአብሔር ልጅ
የሃይሉ ወንጌል፡ ኢየሱስ ጠላቶቹን መቃወሙ
ተዓምራት
ምሳሌዎች
የመከራው ሃይል፡ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን መማረኩ (ማሸነፉ)
ስሜትን የሚይዝ ትረካ
መጨረሻው መጀመርያ ብቻ ነው
ከፍል ሶስት
ጭብጦቹ በዝርዝር
የትረካው ፍጥነትና ድምጸት
ምፀት
ክፍል አራት
ውጫዊ ስነአፈታት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት
አሳጥሮና ማጠቃለያ
የውይይት ጥያቄ
ተግባራዊ ትግበራ
የማጠቃለያ አስተያየት

የማርቆስ ወንጌል

የትምህርቱ መግለጫ

የማርቆስ ወንጌል ጠለቅ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነው፤ ምክንያቱም ከአራቱ ቀኖናዊ ወንጌላት ቀደምት በመሆኑ ነው፡፡ ማርቆስ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ አገልግሎትና ማንነት በመጀመርያ የተጻፈ ሀተታ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት፤ ይህ ትምህርት ትኩረቱን በኢየሱስ ሰውነት እና አገልግሎት እንደ ማርቆስ አገላለፅና እንዲሁም በፀሃፊው ፍላጉትና ዓላማ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ የመጨረሻ አላማዎች፤ ግላዊ መንፈሳዊ ስልትና አሁን ባለችው ቤትክርስትያን ውስጥ የማርቆስን መልዕክት በብቃት ማገልገል ላይ ነው፡፡ እነዚህን ዓለማዎች ለማሳካት፤ ትምህርቱ የአተረጓጎም ታሪክ ላይ፤ የመግቢያ ጉዳዮች ላይ፤ የመዋቅሩ አመሰራረት ላይ፤ የአጠቃላይ የፅሁፉ ውጫዊ አፈታት እና ዋና ጭብጦች ላይ ለምሳሌ ‹የሰው ልጅ› አባባሎችን ፤‹የመሲህንት ሚስጥር› እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

የትምህርት ክፍሉ መግቢያ

ውድ ተማሪዎች፡ እንኳን ወደ ማርቆስ ትምህርት መጣችሁ፡፡ ይህ በሶስት ሰዓታት የሚሰጥ የመጀመሪያው የትምህርት ክፍል አጋማሽ ትምህርት ነው፡፡ ትምህርቱ እናንተን ጥልቀት ባለው እውቀትና አድናቆት ውስጥ፤ ወንጌሉን የማጥናት ጠቀሜታውን ዘርዘር ባለ መንገድ ማሳየትና የመፅሃፍ ቅዱስ ስነ መለኮታዊ ክፍልን መረዳት እንድትችሉ ግንዛቤያችሁን መጨመር ነው፡፡

በሌላ በኩል፤ የማርቆስ ወንጌል ከአራቱ ወንጌላት አንዱ ሲሆን ስለ ኢየሱስ ህይወት፣ ተልዕኮ፣ አስተምህሮ፣ ሞትና ትንሳኤ በጥልቀት ያስተምራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፤ ይህ ወንጌል አንዱ ዋነኛ ወንጌል እንደሆነ ይታወቃል (ይህ ማለት ማቴዎስ፤ ማርቆስና ሉቃስ ዋነኛ ወንጌላት ናቸው)፤ በተጨማሪም የማርቆስ ወንጌል ለማተዎስ እና ለሉቃስ ወንጌል እንደ ዋና ግብዓት ነው ብለው ብዙ ተመራማሪዎች ያምናሉ፡፡

ቀለል ባለ መልኩ ለማቅረብ፤ ይህ ሞጁል በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሏል፡፡ የመጀመሪያው የሞጁል ክፍል ስለ ማርቆስ ወንጌል መነሻ መሰረታዊ መረጃን ያመላክታል፡፡ ይህም ዝርዝር የሆኑ ሃሳቦችን ያካተተ ክፍል ሲሆን፤ ስለ ማርቆስ ወንጌል ዋና ሃሰብ ዳሰሳ፤ ስለ ደራሲው መረጃ፤ ስለ ተደራሲዎቹ፤ ስለ ቦታውና ተያያዥነት ስላላቸው እውነታዎች ያብራራል፡፡

የሞጁሉ ሁለተኛ ክፍል ፤ የሞጁሉ መጀመሪያ ክፍል ላይ የተዘረዘሩ ሃሳቦች ላይ በመንተራስ፤ በጥልቀትና በስፋት ትንታኔ ይሰጣል ፡፡ ሶስተኛው የሞጁል ክፍል፤ የማርቆስ ወንጌል ዋና ጭብጥ ያብራራል፤ በመጨረሻም አራተኛው የሞጁል ክፍል፤ ምዕራፎቹንና ቁጥሮቹን በስፋት ከሌሎች ክፍሎች ጋር በማዛመድ ትረጓሜና ትንተና ይሰጣል፡፡

በመጨረሻም፤ ውድ ተማሪዎች፤ ይህንን ሞጁል በጥንቃቄ ልታጠኑ፤ መልመጃዎቹንና የተግባር ስራዎቹን ልትሰሩ ይገባል፡፡ መልካሙን ሁሉ እየተመኘን፤ትምህርቱ፤ ሳቢና ጠቃሚ እንደሚሆንላችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡፡መልካም እድል፡፡

የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ክፍል ሲጨርሱ፤

1. የማርቆስ ወንጌልን መነሻ ሃሳብ ያብራራሉ፡፡
2. የማርቆስ ወንጌልን ዋነኛ (ገዢ) ጭብጥ ለይተው ያብራራሉ ፡፡
3. የማርቆስ ወንጌልን ዋና ትኩረት በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ፡፡
4. የማርቆስ ወንጌል ክስተቶችን በመለየት፤ ሶስት ጭብጦችን ያብራራሉ፡፡
1. ሁለተኛውን የማርቆስ ወንጌል ክፍለ አብራራ፡፡ ----- የወንጌሉን ሃይል፤
2. ሶስተኛውን የማርቆስ ወንጌል ክፍል አብራራ፡፡------- የመከራውን ሃይል
3. በሶስተኛው የማርቆስ ወንጌል ክፍል ውስጥ የሚገኙትን፤ የኢየሱስን ሞት አመላካቾች፤ ሶስት ሃሳቦች በመለየት አብራራ፡፡
4. በሶስተኛው የማርቆስ ወንጌል ክፍል ውስጥ ያለውን ጥልቅ ትርክት አብራራ፡፡
5. አራተኛውን የማርቆስ ወንጌል ክፍል አብራራ፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>የትምህርት ክፍሉ ዋና ሃሳብ፡ መነሻ ሃሳብ (ዳራ)</u>

<u>መግቢያ</u>

የዚህ ሞጁል የመጀመሪያ ክፍል አምስት የጥናት ክፍሎችን የያዘ ነው። ስለ ማርቆስ ወንጌል ጅማሬ ለምሳሌ ስለ ደራሲው (ፀሃፊው)፣ስለ ተቀባዮቹ ፣ስለ ተፃፈበት ጊዜ፣ ስለ ሁኔታዎቹ፣ ስለ ፅሁፉ ታሪካዊ ዳራ እና ተያያዥነት ስላላቸው ጉዳዮች የምታውቁበት ትልቅ አጋጣሚ ይፈጥርላችኋል።

ዓላማው፡

ከዚህ ትምህርት ማብቂያ በኋላ፤ ተማሪዎች

- የማርቆስ ወንጌልን በተመለከተ፤ አምስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን፤ ለምሳሌ ጸሃፊውን፣ ተደራሲዎቹን፣ ጊዜውን፣ ቦታውን፣ ዓላማውንና ተያያዥነት ያላቸውን እውነታዎች ያውቃሉ።
- በወንጌሉ የተብራሩትን እውነታዎች፤ ውጫዊ እና ውስጣዊ ማስረጃዎች ያብራራሉ።
- የራሳቸውን የወንጌሉን ቅደም ተከተል በመፍጠር፤ ወንጌሉን በራሳቸው መንገድ ለማጥናት ይሞክራሉ።

ውድ ተማሪዎች፤ በመፅሃፍ ቅዱሳችን ውስጥ፤ የዚህን መፅሃፍ ፀሃፊ ክፍል የት የምታገኙት ይመስላችኋል። ስለዚህ ጉዳይ ስታስቡ በአእምሮአችሁ የሚመጣውን ማንኛውንም ሃሳብ ፃፉ።

---

1. ***<u>ፀሃፊው</u>***

ማርቆስ በመፃሀፍ ውስጥ የመፅሃፉ ፀሃፊ እንደሆነ ራሱን አይገልፅም። ምናልባትም ምክንያቱ የኢየሱስ ፍላጎት ስለራሱ ስም ሳይሆን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በዓለም መዳረስ ሊሆን ይችላል።

ውጫዊ አስረጂ፡ ፓፒያስ የተባለው የቀድሞው ቤተክርስትያን አባት፤ ማርቆስ የሁለተኛው ወንጌል ፀሃፊ እንደሆነ ሰይሞታል። ማርቆስ ከጴጥሮስ ጋር የተለየ ቅርበት ምናልባትም ደቀመዝሙሩ እንደነበረ ፓፒየስ ዘግቧል።

ውስጣዊ አስረጂ፡ 1 ጴጥ 5፡13 በጴጥሮስና ማርቆስ መካከል ጥብቅ ቁርኝት እንዳለ ሲያሳይ፤ /ልጄ/ ብሎ እንደጠራው ያሳያል። ቆላስያስ 4፡10 ማርቆስ የባርናባስ ወንድም ልጅ እንደሆነ ይናገራል። በ ሐዋ 12፡25 ከጳውሎስና ከባርናባስ ጋር የተጓዘ ሰው እንደነበር ተዕፏል።

<u>መመዘኛ</u>

የማርቆስ ወንጌል ደራሲ (ፀሃፊ) ማን ነው? (የራሳችሁን ምርምር አድርጉና ከላይ ከተገለፀው ሃሳብ ጋር አስታርቁ።)

1. **ጊዜው**፤ ማርቆስ ከተጻፉት አራቱ ወንጌላት መካከል አንዱ ነበር። ብዙ አዋቂዎች ከ70 ዓ.ም በፊት እንደተፃፈ ጊዜውን ይገልፃሉ።

የማርቆስ ወንጌል የተፃፈበትን አካባቢ ታሪካዊ ሁኔታ

ሀ. የጴጥሮስና ለኢየሱስ ቅርብ የሆኑት ሌሎችም.ሞት በ60 ዓ.ም አጋማሽ እንደነበር፤

ለ. አዳዲስ ክርስትያኖችን ደቀመዛሙርትነት ለማስተማር የሚሆን፤ታሪክ የመሰብሰብ ፍላጎት፤

ሐ. ክርስትና እያደገ በመሄዱ፤ ተሰንዶ የተቀመጠ ጽሁፍ እንዲኖር ፍላጎት ማነሳሳቱ፤

መ. የክርስትና ሃይማኖትና የይሁዲ ሃይማኖት (አምነት) ለመለየት ፤ በተለይ በ70 ዓ.ም የቤተመቅደሱ መፍረስ፤

2. **ቦታና ተደራሲዎች**

ውጫዊ አስረጂ፡ በልማድ ቦታው ሮም ተደራሲዎቹ ሮማን እንደነበሩ ይነገራል፡፡

ውስጣዊ አስረጂ፡ በማር 7፡14 ላይ፤ ማርቆስ ስለተለመደው ይሁዲ ባህል (ወግ) ገለፃ ይሰጣል፡፡ ለይሁዲዎች ቢጽፍ ኖሮ፤ይህንን ገለፃ መስጠት አያስፈልገውም፡፡በተጨማሪም፤ ብዛት ያላቸውን የአርማይክ ቃላቶች ወደ ግሪክ መተርጎም አያስፈልገውም ነበር፡፡ ለምሳሌ፤ የኢየሱስ የመስቀል ላይ የመጨረሻ ቃላት በማር 15፡34 እንዲሁም በሌሎች የማርቆስ ክፍሎች በ 3፡17 በ 15፡22 ላይ ይገኛሉ፡፡

3. ሶስት ዋነኛ ጭብጦች

1. የኢየሱስ መከራና ሞት ከምዕራፍ 11 -- 16
2. እውነተኛ ደቀመዝሙርነት -- ለወንጌሉ ሲባል ራስን ለእግዚአብሔር አገልግሎት አሳልፎ መስጠት
3. የመከራ ወንጌል 8፡34፣ 10፡45

4. ማርቆስ ወንጌል አቀማመጥ

ሀ. መግቢያ፡ የመጀመርው የኢየሱስ የምድር አገልግሎት፤ (1፡1 — 15)

ለ. የወንጌሉ ሃይል፡ ኢየሱስ ጠላቶቹን መቃወሙ (1፡ 16 — 8፡21)

ሐ. የመከራው ሃይል፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ማሸነፉ (8፡22 — 15፡47)

መ. ቅጣይ፤ መጨረሻው መጀመርያ ብቻ ነው፤ (16፤1 — 8)

5. ባህርያት

የማርቆስን ወንጌል ከሌሎቹ ወንጌላት ለየት የሚደርጉት አያሌ ባህርያት አሉት፡፡ **መጀመርያ**፤ ከትምህርቱ ይልቅ በኢየሱስ ድርጊት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ማርቆስ 18 የኢየሱስ ተዓምራቶችን፤ አራት ምሳሌዎችን (4፡2 - 20, 26- 29, 12፡1-9) እና አንድ ዋና ትንተናን (13፡3-37) ይዟል፡፡ ማርቆስ ያልተሰነዱ የኢየሱስ ትምህርቶች እንደነበሩም ፅፏል(1፡21, 39፣ 2፡2, 13, 6፡2, 6,34, 10፡1, 12፡35)፡፡ አብዛኛው ትምህርት የመጣው ፤የኢየሱስ ተቃውሞ ከይሁዲ የሃይማኖት መሪዎች ማድረጉ ነበር (2፡8-11,19-22, 25-28, 3፡23-30, 7፡6-23, 10፡2-12, 12፡10-11, 13-40)፡፡

ሁለተኛ፤የማርቆስ የአፃፃፍ ዘዴ ግልፅ፤ ጠንካራና ገላጭ እንዲሁም የአይን ምስክርነት ምንጭ በማንፀባረቅ ነበር፡፡ ለምሳሌ እንደ ጴጥሮስ (2፡4, 4፡37-38, 5፡2-5, 6፡39፣ 7፡33, 8፡23-24, 14፡54)፡፡ የግሪክ አጠቃቀሙ ኢ-ስነፅሁፋዊ ፤ በጊዜው ከሚታወቅ የቀን ተቀን ንግግር ጋርተቀራራቢ፤ስነ ፍቻዊ ቃና እንደነበረው ያሳያል፡፡ የግሪክ ሰዋስዋዊ አጠቃቀሙ፤ በተለይ ታሪካዊ ‹የአሁን ጊዜ› የሚለውን ቃል ከ 150 ጊዜ በላይ ተጠቅሟል፡፡ ቀላል ዓረፍተ ነገሮችን በአያያዥ ቃላት (እና) ፤ በተደጋጋሚ (ወዲያውኑ) የሚለውን መጠቀሙ እና ጠንካራ ቃላት መጠቀሙ (ለምሳሌ አስተያየት 1፡10) ለትረካው ግልፅነጽን አላብሰውታል፡፡

ሶስተኛ፡ ማርቆስ ባልተለመደ ግልፅነት ትምህርቱን አስቀምጧል፡፡ የኢየሱስን አድማጮች ምላሽ ፤በተለየ የአድናቆት አገላለፅ አተኩሮበታል፡፡ (አስተያየት ስጥ 1፡22, 27, 2፡12, 5፡20, 9፡15) የኢየሱስን ዘመዶች ጉዳይ፤ አእምሮውን ከሳተ ሰው ጋር አያይዞታል፡፡ (3፡21, 31-35) ስለ ደቀመዛሙርቱ ግንዛቤ ማጣትና ውድቀት በቅንነትና በተደጋጋሚ ሃሳብን በሚገዛ መልኩ ገልጧል፡፡ (4፡13, 6፡52, 8፡17, 21, 9፡10, 32, 10፡26)፡ በተጨማሪም የኢየሱስን ስሜት አሳይቷል፡፡ ለምሳሌ ፍቅሩን (1፡41, 6፡34, 8፡2 10፡16) ቁጣውንና መከፋቱን (1፡43, 35, 8፡33, 10፡14) እና የጭንቀቱንና የሃዘኑን ምጥ (7፡34, 8፡12, 14፡33-34)፡፡

አራተኛ፡ የኢየሱስ የመስቀል ጉዞ እና ትንሳኤው፤ በማርቆስ ወንጌል ላይ በባለይነት ተቀምጧል፡፡ ከማርቆስ 8፡31 ጀምሮ በቀጣይ ባሉት ክፍሎች፤ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ከሲዛርያ ፊሊፕ በሰሜን በገሊላ በኩል ወደ ኢየሩሳሌም በደቡብ በኩል በጉዞ ላይ እንደነበሩ ያሳያል፡፡ (9፡33, 10፡32)፡፡ 36 ፐርሰንት የሆነው የቀረው ትረካ፤ በስቃዩ ሳምንት ላይ አተኩሯል፤ ስምንት ቀናት፤ ከኢየሱስ ወደ እየሩሳሌም መግባት (11፡1-11) እስከ ትንሳኤው (16፡1-8)፡፡

6. ለምን ተፃፈ

አንደ ወግ (ባህል)፤ይህ ወንጌል፤የሮማን ሰዎች አስቸኳይ ጥያቄ ለማሟላት፤ጴጥሮስ በከተማዋ የሰበከውን፤ በፅሁፍ ተከልሶ ያለውን ስብከት እንደተቀናበር ይገለፃል፡፡ ይሁንና በመፅሃፉ ውስጥ ያለው መረጃ፤ በነዚህ ምዕራፍና ቁጥሮች ግልፅ እንደሆነው (1፡37, 10፡45, 12፡9, 13፡10 እና እንዲሁም 16፡15 (ምንም ይሁን እውነቱ)፤ከከተማው ውጭ ያሉትን አያካትትም ማለት ግን አይደለም፡፡ይህ ወንጌል በአለም ሁሉ፤የግሪክን ቋንቋ ለሚናገሩ ሁሉ እንዲደርስ ታቅዱ ነበር፡፡ የመልዕክቱ ሃሳብ የነበረው እና የሚሆነው ለሁሉም ሰው ትርጉም እንዳለው ነው፡፡

ተያያዥነት ያለው ጥያቄ፡ ማርቆስ ሲፅፍ መረጃን ለማቅረብ ነው ወይንስ ለውጥ ለማምጣት ነው አስቦ የነበረው? ዓለማው ትረካን ሰንዶ እንደማስቀመጥ ነበር ወይስ ይህን በማድርግ ህያው ለሆነው ከእግዚአብሔር ክብር ሽልማት ለማግኘት ነበር? በተለየ ሁኔታ ለመግለፅ ኢየሱስን እንዴት ገለጸው ሳቢ በጣም ሳቢ የሆነ ማንነት እንዳለው ብቻ? የታሪኩ ታላቅነት ተግባርን ከሰዎች የማወቅ ፍላጎት ለማርካት እና አስደናቂነቱ ጋር የግድ ለማያያዝ ወይንስ የኢየሱስን ክብርና አዳኝ ንጉስ መሆኑን ክብር ቀዳሚ ለማድረግ? ሁሉም ሰው ትህትና በተሞላ እምነት ወደ ኢየሱስ እንዲመለሱ በርግጠኛነት የመጨረሻ ሃሳቡ ነበር፡፡ ማርቆስ የጴጥሮስ ተርጓሚ እንደነበረ፤ በአእምሮ ውስጥ እንደ ተወለደ ግልፅ ነበር፡፡ ጴጥሮስ ምንግዜም ሲሰብክ ንስሃን ግድ ይላል፡፡ አልሞ የሚነሳው ልባዊ ምክርን ለመስጠት በማሰብ ነው (የሐዋ 2፡36-40, 10፡43)፡፡ ለህይወት በሚሆን ንስሃ እና እምነት ውስጥ ሰዎች እግዚአብሔርን ማክበር እንደሚገባቸው ይገልፃል (የሐዋ 11፡18)፡፡ አሁን ያ እውነት ከጴጥሮስ የተነሳ ከሆነ፤ ከማርቆስ የተነሳም እውነት ነው ማለት ይሆናል፡፡ የማርቆስ ወንጌል ትክክለኛ ቀኖናዊና ተግባራዊ ዓላማ አለው፡፡በርግጥ ትረካ ነው፤ በጣም ውድ የሆነ ትረካ (ማር 10፡45, 12፡28-34, 16፡16)፡፡

የሰው ራሱን በፈቃደኝነት ለኢየሱስ የመስጠቱ (የማስገዛቱ) ሁኔታ ጥገኛ የሚሆነው፤ ኢየሱስን በሚያየው ልክ ነው፡፡ በሌላ አባባል፤ እምነት ሁልጊዜ ቀኖናን ያሳያል፡፡ ትረካ ራሱ ያለ ቀኖናዊ እንድምታ የለውም፡፡ ባጠቃላይ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የተገለፀው፤ስነ ክርስቶሳዊ ሃሳብ ፤ ሲጀመርም ኢየሱስ ፍጽም ሰው እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ ይበላል (2፡16) ፣ይጠጣል(15፡36)፣ ተርቧል(11፡12)፣ሰዎችን ዳሷል(1፡41)፣በሰዎች ተዳሷል(5፡27)፣አዝኗአል (3፡5)፣ተበሳጭቷል(10፡14)፡፡ ከድካም የተነሳ አንቀላፍቷል፣ ከእንቅልፍ ተነስቷል (4፡38,39)፡፡ ሰዎች እንዳያጋፉት፤ታንካ ያቆዩለት ዘንድ ጠይቋል(3፡9)፡፡ ለጥቂት ጊዜ ጠርቧል፡፡ እናት፤ ወንድሞችና እህቶች ነበሩት(6፡3)፡፡ እንደ ሰው ታይቷል፣ አውቀቱ ውስን ነበር(13፡32) በዚህም ምክንያት የነካውን ለማየት ወደ ኋላው ዞሯል (5፡30)፡፡ የሚበላ ፍሬ እንዳላት ለማየት ወደ በለስ ዛፍ ሄዷል (11፡13)፡፡ የሰው አካል(15፡43) እና የሰው መንፈስ አለው (2፡8)፡፡ ሞቷልም (15፡37)፡፡

በተቃራኒው፤ይህ አንዱ ኢየሱስ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ፍፁም መለኮት ነው፡፡ የሰው ልጅ (2፡10,28)፤ በተጨማሪም የእግዚአብሔር ልጅ ነው(1፡1,3፡11 ወዘተ)፡፡ይህ በማርቆስ የተገለጠው፤ በህመም፣በአጋንንትና በሞት ላይ የበላይ ገዢ ነው፡፡ ሁሉንም የበሽታ አይነት ፈውሷል፤ አጋንንትን አስወጥቷል(1፡32-34)፡፡አይነ ስውርን፣ደንቆሮዎችን ፈውሷል ወዘተ(8፡22-26,10፡46-52)፤ ለምፃም አንፅቷል (1፡40-45)፤ የሞተን እንኳን አስነስቷል (5፡21-24, 35-43)፡፡ ባጠቃላይ ሃይሉን በፍጥረት ገዢ ላይ ተጠቅሟል፡፡ ማዕበልና ወጀብን ፀጥ አድርጓል (4፡35-41)፤ በውሃ ላይ ተራምዷል (6፡48)፤ የበለስ ዛፏ ፍሬ እንድትጠወልግ አድርጓል (11፡13,14,20) ፡፡ስለ ወደፊት ያለው እውቀት እጅግ ሰፊና የተሟላ ከመሆኑም በላይ ወደፊት በኢየሩሳሌም፣ በዓለም፣ በደቀመዛሙርቱ (ምዕ 13) እና በራሱ ላይ ምን እንደሚሆን አስቀድሞ ተናግሯል(ቅድመ ትንበያ) (8፡31, 9፡9,21 10፡32-34, 14፡17-21)፡፡ በሰው ልብ ውስጥ ያለውን (2፡8, 12፡15) እና ያሉበትን ሁኔታ ያውቃል (12፡44)፡፡ ስልጣኑ እጅግ ድንቅ ነው፡፡ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ ሊያደርግ የማይችለውን የሰውን ሃጥያትን ያስተሰርያል (2፡1-12)፤(በተለይ ቁ. 5 እና 6)፡፡ ለሞት ተላልፎ ተሰጥቷል፤ እንደገና ከሞት ተነስቷል፤ በዚህም የታላቅነቱ ጫፍ (ጥግ) ተገልጧል (16፡6)፡፡

ማርቆስ ኢየሱስን እንደ እምነት ጉዳይ ቢወስደውም፤ ይህ ጥያቄ አዎንታዊ በሆነ ብርቱ መንገድ መመለስ ይገቧዋል፤ በርግጥ በግልፅም ታይቷል፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የሚመጣው ጌታ፤ በነብያት እንደተነገረው፤ ‹መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ› ተብሎለታል (1፡1-3)፡፡ መላዕክቶች የሚያገለግሉት (1፡13)፤ ደሙ ብዙዎችን ነፃ ያወጣል (10፡45, 14፡24)፡፡ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ (1፡8) የሰንበት እንኳን ጌታ የሆነ(2፡28)፡፡ የራሱን ተወካዮች የሰየመ(3፡13-19)፤ የራሱ በሆነ አገር ላይ በእምነት የተቀባይነት መብት የነበረው(6፡6)፤ ሰዎች እንዲከተሉትና እንዲቀበሉት፤የመጥራት ስልጣን ያለው (8፡34, 9፡37)፤ አስቀድሞ ዳዊት በጊዜው ጌታ ብሎ የጠራው፡፡ (በ12፡37 ውስጥ ተገልጧል) በአባቱ ክብር (8፡38) በደመና ላይ በታላቅ ሃይልና ክብር በድጋሚ የሚመጣው ፤ የተመረጡትን አንዲሰበስቡ መልአክቱን ወደፊት የሚልክ (13፡26,27)፡፡

እንደነዚህ ወንጌላውያን፤ ሁለቱ ባህርያት፤ ሰው እና መለኮት በፍጹም አንድ (በአንድ አካል) ናቸው፡፡ ይህ እውነት ነው፡፡ ማንም ሰው የተወሰኑትን አንቀጾች በማጥናት መለየት አይሳነውም (4፡38,39 41-43, 8፡1-10, 14፡32-41 ወዘተ)፡፡

የማርቆስ ዋነኛ ዓላማ ይህንን ኢየሱስ፤ የሰው ልጅ እና የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን፤ አሸናፊውን ንጉስ፤በየትም ቦታ ያለ ማንኛውም ሰው እንደ ግል አዳኙ እና ጌታው አድርጎ እንዲቀበለው ነው፡፡

7. የማርቆስ ወንጌል፡አበርክቶው ምንድን ነው

የማርቆስ ወንጌል በርከት ያሉ ጠቃሚ እውነታዎችንና ጠቃሚ ትምህርቶችን ያቀርባል፡፡ በመጀመርያ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ትንቢት የተነገረለት መሲህ እንደሆነ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ ሁለተኛ፡

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያረጋግጣል፤ ሃጢያት የሌለበት እና ፍፁም ህይወት እንደነበረው ያስረዳል። ሶስተኛ፤ ወንጌሉ፤ ኢየሱስ በተፈጥሮ ላይ ተዓምራት እንዳደረገ፤(ማዕበሉን እንዳዘዘ ማር 4፡37-41)፤ በውሃ ላይ እንደተራመደ (ማር 6፡48-51) እና የበለስ ዛፏን እንዳደረቀ (ማር 11፡12-14) ተሰንዷል። በተጨማሪም ተዓምራቱ ብዙ ሰዎችን መፈወስ፤ የጴጥሮስን አማት ጨምሮ (ማር 1፡30-31)፤ እግሩ የሰለለችውን ሰው (ማር 2፡3-12፤ ደም ሲፈሳት የነበረችን ሴት (ማር 5፡25-29) እና መስማት የተሳነውን (ማር 5፡31-37) ያጠቃልላል። ኢየሱስ የምኩራብ አለቃውን ሴት ልጅ ከሞት በማስነሳት በሞት ላይ ስልጣን እንዳለው አሳይቷል(ማር 5፡37-39)።

የማርቆስ ወንጌል ዋነኛው ጠቃሚ እውነት፤ ኢየሱስ ከመቃብር በትንሳኤው በመውጣት የሞትን ሃይል ድል ማድረጉን መረጃን ያቀርባል። ምንም አይነት ሃይል እሱን ድል እንዳላደረገው አረጋግጧል፤ የሰዎችን ሃጢያት የማስተሰረይ ስልጣንም አለው፤ አንድና ብቸኛው እግዚአብሔር ልጅ ነው። በመጨረሻም፤ እግዚአብሔር ሰዎች እንዴት መኖር እንዳለባቸው እንደሚፈልግ ፤አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፉ እንዴት መመላለስ እንዳለባቸው፤ እና ወደፊት ስለሚሆነው፤ የዘላለም ህይወትን በተመለከተ የራሳቸውን ምርጫ እንዲመርጡ፤ኢየሱስ ፍጹም የሆነን መመርያ ሰጥቷል። እምንት እንዲኖራቸው (ማር 2፡5)፤ ፍርሃትን በእምነት እንዲቀይሩ(ማር 4፡40)፤ በእግዚአብሔር ሃይል እንዲታመኑ(ማር 5፡36)፤ ክርስቶስን እንዲከተሉ(ማር 8፡35)፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲረዱ(ማር 9፡35) እና መስዋዕትነትን(ማር 10፡21) እነዚህን ጥቂት ምሳሌዎች ሰጥቷል። በዚህ ወንጌል ላይ የተሳፈውም ይሁን የተነገረው ማንኛውም ቃል ተግባራዊ በሆን መልኩ በህይወት ሊተገበር ይችላል።በርግጥ፤ የዚህ ወንጌል ማጠቃለያ፤ የጸሃፊው ሙሉ ቃል ዳሰሳ እንዲዘጋጅ ማስቻል እና ሊቀየር እንደማይችል መግለጽ ነው። ስለ ኢየሱስ በይበልጥ እንድትማሩ ወንጌሉን እንድታነቡ ትበረታታላችሁ።

የማርቆስ ወንጌል ተጠብቆ የተቀመጠ ቀድምት ወንጌል ነው። ቀደም ያለውን የኢየሱስ ህይወት በፅሁፍ በማቅረብ የመጀመርያውን ድረሻ ይይዛል። ማስረጃ ባይገኝም፤ ከማርቆስ በፊት የነበሩት ተመሳሳይ ፅሁፍ እንዳልፀፉ ይገለፃል። ነገር ግን እውነትነት ያለው አይመስልም። በማንኛውም ሁኔታ፤ እንደዚ ያለ፤ የፀሃፊውን ሙሉ ሃሳብ የያዘ እንዳለ አናውቅም። የማርቆስ ፅሁፍ፤ ቀደም ካሉ ተመሳሳይ አይነት ካላቸው ፅሁፎች እንዳልተቀዳ በበቂ ሁኔታ ማስረዳት ችሏል።

ወንጌሉን ለመሰነድ፤ ማርቆስ ባህላዊ ቁሶችን እንደተጠቀመ ጥርጥር የለውም። በወንጌሉ ውስጥ ያሉ አንዳንድ አባባሎች ፤እንደ ሉቃስና ማቴዎስ አገላለፅ፤የወንጌሉ ፀሃፊ ራሱ ምንጩን እንደጠተቀመበት ባጠቃላይ ይታመናል። ይህ የሚያሳየው፤ ይህ አባባል፤ የቀድሞው የማርቆሳውያን ክርስትያኖች ባህል(ወግ) አካል ነበር። አንዳንድ የወንጌሉ ታሪኮችም መነሻነታቸው የማርቆስ አልነበሩም፤ ነገር ግን በክርስትያን ማህበረሰብ ውስጥ ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር። ማርቆስ የተወሰኑትን እነዚህን ባህላዊ (ወጎች) ታሪኮች ያውቅ ነበር ማለት ነው፤ወይም የእየሱስ አባባሎች በስፋት ይታወቁ ነበር ማለት ነው? ይሁንና ወንጌላውያኑ በኢየሱስ ህይወት ላይ ተቀናጅቶ የተሰነደ ፅሁፍ እንዳለ የሚያሳይ ማስረጃ እንደሌለ ይገልፃሉ።

በሌላ አነጋገር፤ ስለ እየሱስ ህይወት መግለጫን ሲፅፍ የተለመደ አካሄድን ያልተከተለ የነበረ መሆኑ፤ የማርቆስ ወንጌል በጊዜው የነበረውን የማንንም ቅጂ ያልተጠቀመ ይመስላል። ይህ ምልከታ ብዙ ወንጌላውያን፤ ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጡት አደርጓል። ለምን ማርቆስ ስለ ኢየሱስ ህይወት ለመፃፍ ወሰነ? መነሻው ምን ነበር? በጽሁፍ ውስጥ የወንጌላውያኑ ዓለማ ምን ነበር? የዚህ ጥናት ዓላማ፤ የማርቆስ ወንጌል መጀመርያና ዓላማውን ተንተርሰው ለሚነሱ ጥያቄዎች የተሟላና የተቀናጀ ምላሽ ለማዘጋጀት ነው።

የማርቆስ ወንጌል ለነዚህ ጥያቄዎች ቀጥተኛ ምላሽ አይሰጥም። ስለሆነም መረጃውን ፤የክፍሉን ዋና ሃሳብ በማጥናትና ታሪካዊ ዳራውን በመመልከት መረጃን ማመላከት መቻል ነው። ምክንያቱም እንደዚ ያለ ዳሰሳ ፤የተለያየ አመለካከትን ይሰጣል።

የተወሰኑ አመለካከቶች፡ ሀ) ኢየሱስን የጌታ አገልጋይ አድርጎ፤ የህይወት ታሪኩን በመሳል ማቅረብ፤ (ለ) የተቀየሩትን ለመማረክ (ሐ) ለአዳዲስ ክርስትያኖች መመሪያ ለመስጠትና በሃይማኖታዊ ጭፍጨፋ ፊት፤ እምነታቸውን ለማጠንከር (መ) ወንጌላውያንና አስተማሪዎች፤ ለማስተማሪያ የሚጠቀሙበት ግብዓት ለማዘጋጀት፤ (ሰ) ስለ እየሱስ እና ስለ መሲሃዊ አገልግሎቱ የተሳሳተ ሃሰብን ለማረም፤ እነዚህ አስተያየቶች ጠቃሚ ቢሆኑም፤ የተወሰነው የወንጌል ክፍል ግምት ውስጥ ያላስገባ ወይም ማርቆስን ትኩረት የሰጠውን ጉዳይ ቦታ ያልሰጡ ናቸው።

የማርቆስ ዓላማ በመሰረቱ፤ መጋቢነት ነበር።በሮም ያሉ ክርስትያኖች መልካሙን የእግዚአብሔርን የማዳን ዜና ሰምተው አምነዋል። (ሮሜ 1፡8) ነገር ግን በውርደትና በጥላቻ ሁኔታ ውስጥ፤ ለህይወታቸው የሚሰጣቸውን አዲስ ነገር በትኩረት እንደገና መስማት ይፈልጋሉ። የደቀ መዝሙርነት ተፈጥሮ ምን እንደሆነ መረዳት፣ ኢየሱስን መከተል ፣ኢየሱስ ማን እንደሆነ እና ስላደረገላቸውና ስለሚደርግላቸው ነገር መስማት ይፈልጋሉ።

ልክ አንደ መልካም መጋቢ፤ ማርቆስ ስለ ኢየሱስ ወንጌል ማለትም ‹የእግዚአብሔር ልጅ› ይህንን ፍላጎት በሚመጥንና በቀጣይ የአንባቢዎቹ ህይወት ለመቅረጽ በሚችልበት መንገድ አቅርቦታል(1፡1)። ይህንንም፤ ኢየሱስን በመግለፅ(በመሳል) እና አስራ ሁለት ደቀመዛሙርት አንደተደራሲ ተስፋ አድርጎ በመለየት አሳክቶታል (ስነመለኮታዊ ጭብጥ በሚለው ስር ይመልከቱ)። ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት መሲህ እንደሆነ፤ምክንያቱም እሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ነው። የእግዚአብሔር እቅድ የሰው ልጅ ስቃይ፤ በሞቱ ሰዎችን እንዲቤዥ ነው። በዚህ እይታ ውስጥ፤ ኢየሱስ ለተከታዮቹ እንዴት እንደሚጠነቀቅ፤ የሞቱና የትንሳኤው ሃሳብ እና ስለ ደቀመዛሙርትነት ባጠቃላይ ስለነዚህ ጉዳዮች አስተምሯል። ኢየሱስን ለሚከተሉ ሁሉ ተመሳሳይ ጥንቃቄና ትምህርት ያስፈልጋል።

1. የማርቆስ ወንጌል እንዴት ተደራጀ

አንደ ማርቆስ አገላለጽ ወንጌሉ ስለ ኢየሱስ ውልደት ምንም ትረካን አልያዘም። ይሁንና፤ ገና መጀመርያው ምዕራፍ ሲጀምር ከሰማይ የመጣ አውነት እንደሆነ ገለፃን ይሰጣል(ቁ. 38 ተመልከት)። መወለድ ብቻ አይደለም መምጣቱንም ያረጋግጣል። የማርቆስ ምዕራፍ 1 ሰላሳ ስምንት ቁጥሮች ከ የሁንስ ምዕራፍ 6 ሰላሳ ስምነት ቁጥሮች የተለየ መሰረታዊ ትርጉም እንደሌላቸው፤ የሚያሳምን ምንም አሳማኝ ምክንያት የለም። በርቆስ በግልፅ የተነገረው ዓላማ፣ በስም፣ መስበክ(1፡38),፣ሃጥያተኛን መጥራት (ንስሃ መግባት)፣ (2፡17፤ ለብዙዎች ራሱን አሳልፎ መስጠት (10፡45)፣የተፋውን ለማዳን (ሉቃ 19፡10) ፣ሃጠያተኛውን ለማዳን (1 ጢሞ 1፡15) ከነዚህ ክፍሎች ጋር ማነፃፀር ይቻላል። ጳውሎስ እንዳለው ሀብታም ሲሆን፤ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሃ ሆነ (2 ቆሮ 8፡9)። አባት ልጁን ወደ አለም ሲልክ ልጁ ሊፈጽመው የሚገባ ስራ፤በስም ‹ የዓለም አዳኝ ሊሆን› እንደላከው (1ዮሐ 4፡14)ይገልፃል።

2. ስነ መለታዊ ጭብጥ

የማርቆስ ገለፃ የኢየሱስንና የደቀመዝሙርነት ትርጉም፤ ስነ መለኮትን ማዕከሉ አድርጎ አሳይቷል።

በመጀመርያው ቁጥር እየሱስ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ተገልጧል (1፡1)። በአባቱ ተረጋግጧል (1፡11, 9፡7)፣ በክፉ (3፡11, 5፡7) ፣በእየሱስ በራሱ (13፡32, 14፡36 61-22) እና በእየሱስ ሞት ጊዜ በሮማውያን ጠባቂ (በመቶ አለቃው(15፡39) ተረጋግጧል። በተጨማሪም ስልጣን ባለው ትምህርቱ (1፤22,27) እና በበሽታና በደዌ ላይ (1፡30-31, 40-42; 2:3-12; 3:1-5; 5:25-34; 7:31-37; 8:22-26; 10:46-52)፣በክፉ ላይ (1:23-27; 5:1-20; 7:24-30; 9:17-27)፣ በተፈጥሮ ላይ (4:37-39; 6:35-44, 47-52; 8:1-10), እና በሞት ላይ ፍፁም የሆነ ስልጣን እንዳለው አረጋግጧል (5:21- 24, 35-43)። እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር መንግስትን፣ ንግስናውን፤ ኢየሱስ በቃልም ሆነ በስራ ለሰዎች መቅረቡን አሰማኝ ማስረገጫዎች ናቸው(1፡15 አስተያያት ስጥ)።

እውነት በማይመስል መንገድ ኢየሱስ ሰይጣን ዝም እንዲል አድርጎታል (1:25, 34; 3:12)። ይህም ተዓምራት ለህዝብ ሁሉ አልተገለፀም (1:44; 5:43; 7:36; 8:26)። ህዝብ በተሰበሰበት ቦታ ኢየሱስ ምሳሌ በመጥቀስ ማስተማሩን ትኩረት ተሰጥቶታ (4:33-34)፤ ምክንያቱም ንጉስነቱ ተሸፍኖ ነበር። ይህ ሚስጥር የእምነት ሰዎች ለሆኑት ብቻ ታወቀ (4:11-12)። የኢየሱስ ህልውና ከነሱ ጋር የመሆኑን ትርጉም፤ በመጀመርያው ገለፃ፤ ደቀመዛሙርቱን ለመረዳት የዘገዩ መሆናቸውን ማርቆስ አተኩሮት ሰትቶታል(4:13, 40; 6:52; 7:17-19; 8:17-21)።ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ማንነት ከተናገረ በኋል፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ስለማንነቱ ለማንም እንዳይናገሩ ማዘዙን ትኩረት ሰጥቶታል(8:30)። ኢየሱስ ይህንን ያደረገው፤ አይሁዶች ስለመሲሁ የተሳሳተ አመለካከት ስለነበራቸውና ይህም ከኢየሱስ የምድራዊ አገልግሎቱ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ነበር። ምን አይነት መሲህ እንደነበረና የአገልግሎቱን አይነት ለደቀመዛሙርቱ ግልፅ እስኪያደርግላቸው ድረስ፤ ማንነቱ በግልፅ እንዳይነገር ፈልጓል። ማርቆስ ጴጥሮስ አንተ ክርስቶስ ነህ ብሎ የተናገረውንም ፅፏል(8:29)። ኢየሱስ መሲህነቱን በቀጥታም ይሁን በተዘዋወሪ፤ በቀላሉ አልተቀበለም ወይም አልተቃወመም። ነገር ግን የደቀመዛሙርቱን ትኩረት ከማንነቱ ጥያቄ ይልቅ፤ ሊሆን ወደ አለው ነገር ቀይሮታል (8:31, 38)። ‹የሰው ልጅ› የሚለውን ስያሜ መርጧል፤ እናም ለደቀመዘሙርቱ መከራ ሊቀበል ሊገደልና ሊነሳ እንዲገባው ‹የሰው ልጅ› የሚለውን መጠሪያ በመጠቀም አስተምሯል። እየሱስ በማርቆስ ቁጥሮች ውስጥ 12 ጊዜ ተጠቅሞበታል። በተለይ 9፡41 ላይ ክርስቶስ መሲሁ እንደሆነና፤ ያሁንና የሚመጣው የመሲህነት አገልግሎቱ እንዳለው አስቀምጧል። (አገናዝብ 8:31, 38; 14:62)። የያህዌ የመከራ አገልጋይ ፤እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ህይወቱን ለሌሎች የሰጠ ነበር (ኢሳ 52:13-53:12, ማር 8:31)። በተጨማሪም፤ የሰው ልጅ በክብር ለፍርድ አንደሚመጣ እና ምድራዊ መንግስቱን እንደሚመሰርት ተነግሯል (8:38-9:8; 13:26; 14:62)። ነገር ግን፤ ከመሲህነቱ መንግስት ክብር ድል በፊት፤ በመጀመርያ ስለሰዎች ሃጢያት እንደ እግዚአብሔር ሃሳብ ቤዛ ሊሆን (10:45) መከራን ሊቀበልና ሊሞት ይገባው እንደነበር በግልፅ አስቀምጦታል(14:36; 15:34)። ለሚከተሉት ሁሉ ይህ መሰረታዊ እንድምታ እንዳለው ማርቆስ ፅፏል(8:34-38)።

ለአስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርቱ ይህንን መረዳት አዳጋች ነበር። ንጉሱን መሲህ እንጂ ፤መከራ ተቀብሎ የሚሞተውን ማየት ተስኖአቸው ነበር። በተለየ በደቀመዘሙርት ክፍል ውስጥ (8:31-10:52)፤ ኢየሱስ ወደ እየሩሳሌም አየተጓዘ ፤እሱን መከተል ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለደቀመዛሙርቱ እንዳስተማራቸው ማርቆስ በግልፅ አስቀምጧል። እይታቸው የሚስብ አልነበረም። ነገር ግን በፊታቸው በተለወጠ ጊዜ፤ በሃይልና በክብር ወደ ፊት እንደሚመጣ የሚያሳይ ማረጋገጫ ለሶስቱ ደቀመዛሙርት ሰትቷቸዋል(9:1-8)። በዚያኑ ጊዜ፤ እግዚአብሔር ልጅነቱን አረጋግጧል፤ አንዲታዘዙትም አሏል። በአጠቃላይ በዚህ ክፍል፤ ደቀመዛሙርቱ ‹አዩ› እንጂ አልተገደዱም (8:22-26)። ባለማስተዋል እና ምን ሊሆን እንደሚችል በመፍራት ይከተሉት እንደነበር ማርቆስ በመደነቅ ትኩረት ሰጥቶ ፅፎታል (9:32; 10:32)። ኢየሱስ ሲያዝ ሁሉም ተተውት ሸሹ(14:50)። ማርቆስ የስቅለቱን እና ተከታታይነት ያላቸውን ኩነቶች ትርጉም፤ በጥንቃቄ ዘግቧል(15:33-39).።

ነገር ግን ማርቆስ ባዶውን መቃብር እና የመላዕክቱን መልዕክት፤ ስለ ኢየሱስ ሞትና መነሳት፤እንዲሁም ወደገሊላ በመሄድ ላይ ስለነበሩት ደቀመዛሙርት ትኩረት ሰጥቶ ገልፆታል (14:28; 16:7)። አገልግሎታቸው ለመጀመርያ ጊዜ የተደረበትንም ቦታ ገልጧል (6:6ለ-13)። የማርቆስ ድንገተኛ ማጠቃለያ፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ለመምራት እና ፍላጎታቸውን እንደቀድሞው ለማሟላት ህያው እንደሆነ ድራማዊ በሆነ መልኩ ያውጃል። ስለዚህም፤ የደቀመዛሙርትነት ‹ጉዞ› ፤ በኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ብርሃንና ቁርጠኛነት ውስጥ ሆነን መንገዝ እንዳለበን ይገልፃል (9:9-10)።

9.1 የወንጌሉ ሃይል፤ ኢየሱስ ተቃዋሚዎችን ተቃወመ (ማር 1፡16-20)

ይህኛው የማርቆስ ክፍል፤ የኢየሱስን ደቀመዛሙርቱን የመጥራቱን ጥሪ ያሳያል። ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ሰው አጥማጅ እንዲሆኑ ጠርቷል ምዕራፍ 3፡13–19። ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ለምን እንደጠራ ሶስት ምክንያቶችን ይሰጣል።

1. መንግስቱን አንዲሰብኩ
2. ክፉ መንፈስን እንዲያሰወጡ
3. በአገልግሎት እንዲካፈሉ

መንግስቱን ሲሰብኩ፤በመጀመሪያ፤ ደቀመዛሙርቱ ከተቃዋሚዎች ተቃውሞ በተከታታይ ደርሶባቸው ነበር። ሁለተኛ፤ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ለመታደግ ያለውን ፍላጎት በመግለፅ፤ ማርቆስ ቀጣይነት ያለውን ፈውስ፣ ክፍ መንፈስን ማስወጣት፣ እና የተለያዩ ተዓምራትን ዘግቧል። ሶስተኛ፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን በአገልግሎት እንዲሳተፉ መላኩ፤ ለምሳሌ 5,000 የተመገቡበት አገልግሎት ላይ መሳተፋቸው። ስለሆነም፤ በማርቆስ ወንጌል አካፋይ ክፍሎች ሁሉ፤ ድርጊቶቹ ሁሉ ትኩረት የሚያደርጉት እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ለመታደግ ያለውን ፍላጎት እና ጠላትን ድል የመንሳት ዓለማን ያዘለ ይመስላል።

በተጨማሪ ይህ ክፍል፤ ኢየሱስ ሁለቱን ዋነኛ ጭብጦች ማለትም የእግዚአብሔርን ፀጋ እና ከእግዚአብሄር የሆነውን መገለጥ የያዘውን የዘሪውን ምሳሌ በማብራራት ተናግሯል።

1. በእግዚአብሔር ፀጋ ጭብጥ ውስጥ፤ የእግዚአብሔር ፀጋ በሁሉ ስፍራ እንዳለ፤ ዘር በሁሉ ቦታ ሊዘራ እንደሚችል የሚወክል እንደሆነ፤ ማንም ሰው ሊረዳው ይችላል።

2. ከእግዚአብሄር በሆነው መገለጥ ውስጥ ያለውን ጭብጥ፤ ኢየሱስ በምሳሌ መናገር አስፈላጊ እንደሆነ መረዳቱን፤ መገንዘብ ይቻላል። የእግዚአብሔርን መንግስት ሚስጥር ለነሱ (ለደቀ መዛሙርቱ) ማወቅ እንደተሰጣቸው ፤ ነገር ግን በውጭ ላሉት ሁሉ ግን፤ ነገር በምሳሌ እንደሚነገራቸው ኢየሱስ ገልፆላቸዋል።

9.2 የመከራውን ሃይል፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን መማረኩ (ማር 8፡22, 15፡47)

ኢየሱስ ክፍ መንፈስን ያስወጣ፤ አስደናቂ ተዓምራቶችን የከወነ፤ እና አካለዊ ፈውስ ለሰዎች ያመጣ ሰው ብቻ ሳይሆን፤ ይልቁንም፤ደቀመዛሙርቱን ለመማረክ ሃይሉንም በማሳየት ገልፆአል።

ስለ ኢየሱስ ሞት የተነገረው ሶስት ዋና ዋና ቅድመ ትንበያም (አስቀድሞ ሊሆን ያለውን መናገር) በዚህ ክፍል ውስጥ ይገኛል።

1. ኢየሱስ በማርቆስ 8፡27 ፤ ክርስቶስ እንደሆነ፤ ጴጥሮስ የእምነት ምስክርነት መስጠቱ ተዕፏል። በጴጥሮስ የእምነት ምስክርነት ተንተርሶ፤ ኢየሱስ የሰው ልጅ መከራን ሊቀበል እንደሚገባው፤ እንደሚሞት እና በሶስተኛው ቀን ከሞት እንደሚነሳ እንዳስተማረ ተዕፏል። ይህ የመጀመርያው የኢየሱስ ሞት ቅድመ ትንበያ ነው።

2. በማርቆስ 9፡30–37፤ ልጁ ታላቅ እንደሆነ ተዕፏል። ኢየሱስ የሰው ልጅ በሰው እጅ አሳልፎ እንደሚሰጥ፤ እንደሚገድሉት፤ ነገር ግን በሶስተኛው ቀን እንደሚነሳ ለደቀመዛሙርቱ በዚህ ክፍል ውስጥ እንዳስተማረ ተገልያአል። ይሁንና ደቀመዛሙርቱ ይህን በሚገባ አልተረዱትም። እናም እርስ በርሳቸው በመንግስተ ሰማያት ማን ታላቅ እንደሚሆን መከራከር ጀምረው ነበር። ይህንንም በመመልከት፤ ኢየሱስ ህፃን ወስዶ፤ በመካከላቸው በማቆም፤ ማንም ታላቅ ሊሆን የሚወድ ቢኖር እንደ ህፃኑ ሊሆን እንደሚገባው ነግሯቸዋል። ስለሆነም፤ በዚህ የኢየሱስ ሞት ቅድመ ትንበያ ላይ፤ አንድ ሰው ከዚህ ሊማር የሚገባው፤ ‹ማንም ታላቅ ሊሆን የሚወድ ቢኖር እንደ ሀጻን መሆን እንዳለበት ነው።›
3. በማርቆስ 10፡32–45፤ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የሁሉ አገልጋይ ይሁን ተብሎ ተዕፏል። ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ወደ እየሩሳሌም በጉዞ ላይ እያሉ፤ ኢየሱስ የሰው ልጅ በሊቀ ካህናቱ እና በህግ መምህሮች ተላልፎ እንደሚሰጥ ያስተምራቸው ነበር። ያዕቆብና ዮሃንስ በኢየሱስ መንግስት በቀኝና በግራ እንዲቀመጡ ጠየቁ። የቀሩት 10 ደቀመዛሙት በዚህ ምክንያት በጣም ተቆጥተው ነበር። ፊተኛ ለመሆን፤ የሁሉ አገልጋይ መሆን እንዳለባቸው ኢየሱስ በሚገባ ነገሯቸዋል። ስለሆነም፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ፤ አንድ ሰው ስለ ሶስተኛው የኢየሱስ ሞት ቅድመ ትንበያ ትኩረት በመስጠት ይሰማል።

ማርቆስ 14፡1, 15፡47 በዚህ ትረካ ውስጥ፤ የኢየሱስ መከራ እውነተኛውን የሃይሉን ትርጉም በሚገባ ገልያታል። በተጨማሪም፤ እውነተኛ መከራ ፍፁምኢመለየትን ሊያካትት ይችላል። እየሱስ በመስቀል ላይ ከሰማዩ አባቱ ተለይቶ (ማር 15፡34) ብቻውን እንደሞተ ማርቆስ በዚህ ክፍል አሳይቷል። መሰረታዊ የሆኑ ሁለት ቁልፍ ሁነቶች በኢየሱስ ሞት ተከስተዋል።

1. የመቅደሱ መጋረጃ ከላይ ወደ ታች አኩል ቦታ ተቀዷል። ይህ ማለት ሁሉም ሰው በክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር መግባት ችሏል። ይህ በተጨማሪ እግዚአብሔር ሰውን ለመዋጀትና ለማዳን ያለውን ዘላለማዊ እቅድ አሳይቷል።
2. ከጠባቂዎቹ አንዱ የሆነው የመቶ አላቃ፤ ኢየሱስ በርግጥም የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆን እውነተኛ ምስክርነት ሰጥቷል። ከዚህም ነጥብ መነሻ በማድረግ፤ በኢየሱስ ሞት ውስጥ ኢየሱስ በርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የተረዳ የመጀመርያው ሰው ነበር። እነዚህ ሁለቱ ግልፅ ምልክቶች፤ ማርቆስ የኢየሱስ የመዋጀት ስራ፤ ከመከራው ጋር ተያያዥነትና በቅርበት የሚገናኝ መሆኑን ይናገራል።

9.3 መጨረሻው መጀመርያ ብቻ ነው (ማር 16፡9–20) በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ሶስት ፍፃሜ ያለው ታሪክ ያለው ይመስላል።

1. በቀኖናዊ ጽሁፍ ውስጥ፤ ምዕራፍ 16 በግልፅ ቁጥር 8 ላይ ያበቃል።

2. በአራተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ፤ ይህ አጭር ፍፃሜ እንደዚህ የሚነበብ ሃሳብ ጨምሯል።

ነገር ግን ለጴጥሮስና አብረውት ለነበሩት ሁሉ በግልፅ ተናግሯቸው እንደነበረ ተዘግቧል። ከዛ በኋላም፤ ኢየሱስ ራሱ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ, ከሃይማኖት ጋር የተያያዘና የማይጠፋውን የዘላለም ህይወት አዋጅ እንዲነግሩ ልኳቸዋል።

3. ረጅሙ የማርቆስ ወንጌል ፍፃሜ ፤ቁጥር 9 እስከ 20 ባለው ሃሳብ ላይ ይጠቃለላል። እነዚህ ቁጥሮች፤እስከ ቅርብ ጊዜ ማለትም እስከ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን ፤ በግልጽ የማርቆስ ወንጌል ክፍል ሆነው ታይቷል። በዚህ ረጅም ፍፃሜ ውስጥ፤ አንድ ሰው እነዚህን ጉዳዮች ያገኛል፡

ሀ. ምልክቶች አማኞችን ይከተሏቸዋል፤

ለ. ሰዎች በልሳን ይናገራሉ፤

ሐ. አማኞች በእባቦች ላይ የሚጫመብት ሃይል ያኖራቸዋል፤

ማርቆስ ሃሳቡን በስምንተኛው ቁጥር ቢያበቃ ኖሮ፤ በባዶ መቃብር ያበቃ ነበር። ይሁንና፤ ሴቶቹም ፈርተው ነበር። ስለሆነም፤ የማርቆስ ወንጌል በሞት ወይም በፍርሃት ምርጫ መልዕክት ፍፃሜውን ያገኘ ነበር። በአጠቃላይ የማርቆስ ወንጌል ውስጥ፤ ደቀመዘሙርቱ ምርጫ እንዲያደርጉ ተነግሯቸዋል። በዚህ መጨረሻ ምዕራፍ ውስጥ፤ የመጨረሻ ምርጫ ተሰቷል። አንድ ሰው በታሪክ ውስጥ የተከወነውን አስደናቂ ተዓምራዊ ድርጊት ለመዘገብ አጅግ ፍርሃት ውስጥ መሆኑ ወይም አንድ ሰው ይህንን በወንጌል ውስጥ ያለውን የመከራ ታሪክ ለማያያዝና ሌሎችን ደቀመዛሙርተ ለማድረግ ያለውን ሂደት ለመጀመር እምነት አለው?

ትኩረት የሚሹ ነጥቦች፡

- የዚህ ወንጌል ፀሃፊ ማርቆስ ነው።
- ተደራሲዎቹ ሮማንያውያን ነበሩ።
- ይህ ወንጌል የተፃፈበት ጊዜ በ70 ዓ.ም አካባቢ ነው።
- የዚህ ወንጌል ቦታው ሮም ነው።
- የማርቆስ ወንጌል የመከራ ወንጌል በመባል ይታወቃል።

ማገናዘቢያ

ይህ ጥናት የማርቆስ ወንጌልን፤ በጥልቀት ስታጠኑ የሚነሱትን ዋና ዋና ነጥቦችን አስተዋውቋል። ስለሆነም፤ ከዚህ ክፍል መጨረሻ በኋላ፤ ተማሪዎች

- ከማርቆስ ወንጌል ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መሰረታዊ ሃሳቦች ያውቃሉ፤
- የዚህን ወንጌል ዋና ጭብጥ ያብራራሉ፤
- የወንጌሉን ዋና አከፋፈሎችና ተያያዥነት ያላቸውን ሃሳብ ይገልጻሉ፡

መመዘኛ መልመጃዎች

መመሪያ አንድ፡ እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልስ ስጥ

1. ማርቆስ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ራሱን እንደ መፅሃፉ ደራሲ ራሱን ገልጧል።
2. ማርቆስ ከአራቱ ወንጌላት የመጀመርያው ነበር።
3. የማርቆስ ወንጌል በእየሱስ የመስቀል ጉዞና ትንሳኤ ላይ በስፋት ትኩረት ያደርጋል።
4. የማርቆስ ዓላማ በዋናነት ትንቢታዊ ነበር።
5. የማርቆስ ወንጌል በፍርሃት ወይም በእምነት የምርጫ መልዕክት ያጠናቅቃል።

መመሪያ ሁለት፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ አብራራ

1. የማርቆስ ወንጌል ሶስቱን ዋነኛ ጭብጦች ዘርዝር።
2. የማርቆስ ወንጌልን አራት ዋነኛ ኩነቶች (ክንዋኔዎችን) ግለፅ።
3. የመፅሃፍ ቅዱስ አዋቂዎች ስለ ማርቆስ ወንጌል ዓላማ ያላቸውን ሃሳብ ዘርዝር።
4. በራስህ ቃላት (አገላለፅ) የማርቆስ ወንጌልን ዋነኛ አላማ ግለፅ።
5. እየሱስ ደቀመዛሙርቱን ለምን ጠራቸው (በሞጁሉ ላይ ያገኘኸውን ሃሳብ ሳይሆን የራስህን ገለፃ ተጠቀም)

ክፍል ሁለት

ጥያቄ ለማርቆስ አንባቢዎች

መግቢያ

ይህ ክፍል የማርቆስ ወንጌልን በሚያነቡ ሰዎች የሚነሱትን መሰረታዊ ጥያቄዎች እንድትገነዘቡ ያስተዋውቃችኋል። ከጥያቄዎቹ በተጨማሪ፤ ይህ የሞጁል ክፍል ለጥያቄዎቹ የተሰጡትን የተለያዩ ምላሾችን ይመረምራል። ከባሃፊነት ማንነት፣ ከአንባቢው፣ ከዓለማው ፣ከጊዜ ና ቦታው፣ ከስነመለኮታዊ ጭብጡ እና ከሌሎች ተያያዥነት ካላቸው ጉዳዮች ጋር የሚነሱ መሰረታዊ ጥያቄዎች የተለየ ትኩረት ይሰጣል።

ዓላማው

ይህንን ክፍል በብቃት ካጠናቀቁ፤ ተማሪዎች

- የማርቆስ ወንጌል በማርቆስ እንደ ተፃፈ ባህላዊ፤ ታሪካዊ እና ስነፅሁፋዊ አገባቦችን ይረዳሉ፤
- የማርቆስን ዋና ስነ-ክርስቶሳዊና መንፈስ ቅዱሳዊ ጭብጥ ይለያሉ፤
- የማርቆስ ወንጌል ለስነ-ክርስቶስና መንፈስ ቅዱስ ያለውን ስነ መለኮታዊ አበርክቶ ያደንቃሉ፤
- ማርቆስ ፤ኢየሱስን በመግለፅና የወንጌልን ስነመለኮታዊ ይዘት በማሳየት ፤ያደረገውን አካሄድ ይረዳሉ፤
- በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ያሉትን ፤ክርስትያናዊ መርሆችን በራሳችንና በቤተ ክርስትያናችን ውስጥ በጥንቃቄና ቀጣይነት ባለው መንገድ በመተግበር መንፈሳዊ እድገት ያመጣሉ፡
- የማርቆስ መልዕክት መመሪያ፤ ዋና ሃሳብ እና ያለውን እንድምታ በሚያስተምሩና በሚሰብኩ ጊዜ ይተገብራሉ፤

ውድ ተማሪዎች፤ የማርቆስ ወንጌልን ስታስቡ በአእምሮአችሁ የሚነሱ ጥያቄዎች አሉ፤ በባዶ ቦታው ላይ ግለፁ።

-

ምንም እንኳን የማርቆስ ወንጌል አጭሩ ቀኖናዊ ወንጌል ቢሆንም፤ በመጀመርያ የተፃፈ ወንጌል ነው። የኢየሱስን አስደናቂ የመጀመርያ ቀኖናዊ ምስልን አዘጋጅቷል። ይሁንና፤ ይህን ወንጌል በተመለከተ በብዙዎች ዘንድ፤ ብዙ አጨቃጫቂ ጉዳዮች ይነሳሉ። የመፅሓፍ ቅዱስ አዋቂዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በማንሳት፤ የማርቆስ ወንጌልን ጠለቅ ባለ መንገድ ለማየት ይሞክራሉ።

ሀ. መጀመርያው በመጨረሻ፡ የማርቆስ ወንጌል የት ነው የሚያበቃው? እና በዚህ መንገድ ለምን ሊያበቃ ቻል?

ለ. መጀመርያው በመጀመርያ፡ ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ ሲጠቅስ ፤ማርቆስ ምን ለማለት ፈልጎ ነው? የእግዚአብሔር ልጅን እንደ አገልጋይ ማየት፤ የኢየሱስን ማንነት ለመረዳት ቁልፍ ጉዳይ ነው።በዚህም ምክንያት ኢየሱስ መከራን እንደተቀበለ፤ አገልጋይና መሲሁ የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎ የወሰደ መሆኑ፤ሰማያት ሲቀደዱና እግዚአብሔር ራሱ ትክክለኛ በሆነ መገለጥ ወደዚህ ታሪክ ውስጥ ውስጥ መግባቱን ያሳያል(ማር 1፡9–12)። ነገር ግን ፤ የእግዚአብሔር በዚህ ትእይንት ውስጥ መግባት ሁለተ ጉዳዮችን አስከትሏል ፤ጥፋት (ስጋትና አደጋ) በተጨማሪም ባርኮት ይዟል። የኢየሲስ ወደ ምድር መምጣት፤ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር ለመግባት አስችሏል። በተጨማሪም እግዚአብሔርን በሚገባ እናውቃለን ብለው ለሚሉት ፍርድን ያመጣበት ሂደት ነው።

ሐ. የመሲህነቱ ሚስጥር፡ ስለ ኢየሱስ ያለው ሚስጥር ምንድን ነው? በወንጌሉ ውስጥ ሁሉ በተደጋጋሚ የሚነሳው ጥያቄ፤ የኢየሱስ ማንነት ነው፡ ነገር ግን የማርቆስ አንባቢዎች ኢየሱስ ከመጀመርያው ጀምሮ ፤ የእግዚአብሄር ልጅ አንደሆነ አውቀዋል፤ ሚስጥሩ በመቀጠል፤ ማርቆስ በራሱ ጊዜ በወንጌሉ ውስጥ፤ አንባቢዎቹን የኢየሱስ መሲሃዊነት ሚስጥር በመንሳት ይሞግታቸዋል።

መ. የደቀመዘሙርቱ ግራ መጋባት፤ ማርቆስ ስለ ደቀመዛሙርቱ ግራ መጋባትና አለመረዳት በዚህን ያህል መንገድ አጉልቶ ሊያሳይ ለምን ፈለገ?

እዚህ ጋር አንድ አፍታ ጊዜ ውሰዱ፤ ሞጁሉን ማንበብ አቁሙ እና ሌሎች የማጣቀሻ ጽሁፎችን በመውሰድ፤ ከላይ በተዘረዘሩት አራት መሰረታዊ ጥያቄዎች ዙርያ የራሳችሁን የምርምር ንባብ አድርጉ።

የመግቢያ ጉዳዮች

የማርቆስ ወንጌል የመከራ ወንጌል ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ይህ ምዕራፍ፤ የማርቆስ ወንጌልን የመግቢያ ጉዳዮች በሚገባ ያብራራል፤ ከዚያም አጠቃላይ የማርቆስን ወንጌል በመዳሰስ እያብራራ ይቀጥላል።

የመግቢያው ጉዳዮቹ፤ ለምሳሌ ከፀሃፊነት፣ ከጊዜው፣ ከቦታው፤ ከሁኔታው፣ ከተደራሲው እና ገገር ከሆኑት ጭብቶች (በተለይ ሁለቱ ጭብጦች) ጋር፤ ያለውን ጉዳይ ያካትታል። በመቀጠልም፤ የማርቆስን ወንጌል ዳሰስ ከመጀመሩ በፊት፤ ግልጽ የሆነ መዋቅርን (የመፅሃፉን ቅደም ተከተል) ያቀርባል። ሃሳቡንም በሚገባ እያብራራ ይቀጥላል። የፀሃፊውን ማንነት በሁለት መንገድ ሊፈትን ይችላል። በአንድ በኩል ውጫዊ በሆነ ወግ (ባህል)፤ በሌላ በኩል ውስጣዊ ወግ (ባህል) ከራሱ ከአዲስ ኪዳን፤ በተለይ ከማርቆስ ወንጌል በማጠቀስ ለማሳየት ይሞክራል።

ውጫዊ መረጃ

እንደ ውጫዊ ክርስትያናዊ ወግ (ባህል)፤የአዲስ ኪዳን ከቀደመው ወግ ውጭ; የሁለተኛው ወንጌል ፀሃፊ፤ ማርቆስ የተባለ ሰው እንደነበር ይፅፋል። የቀደመው የቤተክርስትያን አባት፤ ፓፒያስ በ 120 ዓ.ም ገደማ ፤ ማርቆስ የሁለተኛው ወንጌል ፀሃፊ እንደሆነ ተናግሮ ነበር። የፓፒያስ ደብዳቤ፤ የአራተኛው ክፍለ ዘመን የታሪክ ፀሃፊ በነበረው ፤ ኢዩሱበስ በተባለው ሰው ተብራርቶ ነበር። ፓፒየስ በተጨማሪም ማርቆስ የወንጌሉ ፀሃፊ ብቻ እንዳልሆነና፤ ነገር ግን ከጴጥሮስ ጋር የቀረበ ግንኙነት እንደነበረው፤ ምናልባትም የጴጥሮስ ደቀ መዝሙር እንደነበር ተናግሯል።

ውስጣዊ ማስረጃ

በ 1ጴጥ 5፡13 ላይ፤ እንዲህ ተብሎ የተፃፈ ፅሁፍ እናገኛለን፤ ‹ከእናንተ ጋር ተመርጣ በባቢሎን ያለች ቤተክርስትያን፤ ልጄም ማርቆስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል›። ይህ የሚያመለክተው በጴጥሮስና በማርቆስ መካከል የጠበቀ ግንኙነት እንዳለ ነው።

በተጨማሪም፤ ብዙዎች ይህ ዮሐንስ ማርቆስ ተብሎ በሌሎች የመፅሃፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የሚታወቀው ያው ማርቆስ እንደሆነ ሃሳብ ያቀርባሉ። እንደ ቆላስያሰ 4፡10 ‹የባርናባስ የወንድሙ ልጅ› ተብሎ ተጠርቷል። በሐዋ 12፡25 ላይ ከባርናባስና ከ ጳውሎስ ጋር የተገዘ ሰው ማርቆስ እንደነበር ተገልጧል። በሐዋ 15፡37–39 ውሰጥ ፤ ጳውሎስና ባርናባስ ከተለያዩ በኋላ ከባርናባስ ጋር የሄደው ሰው፤ማርቆስ እንደሆነ ይታወቃል። ውስጣዊው ምንጭ እንደሚያሳየው ከሆነ፤ ይህ የሚያመላክተው፤ ውስጣዊው ባህል (ወግ) ራሱ የማርቆስ ወንጌል እንደሆነ ነው። ይሁንና፤ ማርቆስ ወንጌል የፀሃፊው ስም ያልታወቀ እንደሆነ ይታሰባል፤ ምክንያቱም ወንጌሉ እንደ ጳውሎስ የእስር ቤት ፅሁፎች፤ በማርቆስ እንደተፃፈ የሚናገር ምንም ነገር ስለሌለ ነው።

በርግጥ ሳይኖፕቲክስ ወንጌላት፤ ማቴዎስ ማርቆስ እና ሉቃስ፤ ሁሉም ስማቸው ሳይጠቀስ የተተዉ ወንጌላት ናቸው። ምን ማለት ነው? ምናልባት እነዚህ ወንጌላውያን፤ ተደራሲው ብዙ ወይም አንድ ነገር እንደ ፃሀፊ ፤ስለነሱ እንዲያውቅ ፍላጎት ስላልነበራቸው ሊሆን እንደሚችል በመፈለጋቸው ነበር። የነሱ ፍላጎት የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በዓለም እንዲዳረስ ብቻ ነበር። ስለሆንም፤የማርቆስ ወንጌል፤ የወንጌሉን መጀመርያ ስለ ኢየሱስ ፤ ‹የእግዚአብሔር ልጅ› እንደሆነ በመግለፅ ይጀምራል።

ጊዜው

እንደ ብዙ መፅሃፍ ቅዱስ አዋቂዎች፤ ማርቆስ ካሉት ወንጌላት ማለትም ከማቴዎስ ከማርቆስ ከሉቃስ እና ከዮሀንስ በመጀመርያ የተፃፈ እንደሆነ ይናገራሉ። አብዛኞቹ አዋቂዎች፤ የማርቆስ ወንጌል የተፃፈበው፤ ከ 70ዓ.ም ቀድም ብሎ እንደሆነ ጊዜውን ያስቀምጣሉ። ይህ ጊዜ፤ በመጀመርያው ክፍለ ዘመን ጊዜ፤ በአይሁድ ታሪክ ውስጥ የሚታወቅ ጊዜ ነው። ሮማውያን ከ 66 ዓ.ም እስከ 70 ዓ.ም ለጦርነት የመጡበት ጊዜ ነው። በ70 ዓ.ም የኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ የተደመሰሰበት የጠፋበት ጊዜም ነበር። ከ 70 ዓ.ም በኋላ የተፃፉት አብዛኞቹ ሌሎች ሰነዶች፤ ስለዚህ ታሪካዊ ክስተት ጠቅሰዋል። ከዚህ በመነሳት የማርቆስ ወንጌል፤ አብዛኛዎቹ አዋቂዎች እንደሚያምኑት፤ ከ70ዓም በፊት እንደተፃፈ ይስማማሉ። ልክ እንደ ፃሀፊው፤ እንዲሁም በጊዜውም ፤ በማርቆስ ውስጥ ይህንን የሚገልጽ ምንም ነገር አይገኝም። ይሁንና፤ከዚህ ነጥብ በመነሳት ወንጌሉ የተጻፈበትን አካባቢ ያሉ ውጫዊ ታሪካዊ ምክንያቶችን መጥቀስ አስፈላጊ ነው። ስለ መፅሃፉ ጊዜ በትክክል ላይነግሩን ይችላሉ፤ነገር ግን በርግጠኛነት መፅሃፉ ስለያዘው ታላቅ ዓላማ ይገልፃሉ።

ሌላኛው ውጫዊ ታሪካዊ ምክንያቶች፤ የወንጌሉን የጊዜ መረጃን እንድናገኝ ይረዳናል። ለምሳሌ፤ ጴጥሮስ ህይወቱን አጥቷል፤ ጳውሎስም በተመሳሳይ በ60 ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ህይወቱን አጥቷል፤ መከራን በሮም ውስጥ ባስነሳበት፤ በንጉስ ኔሮ መንግስት ጊዜ እና ክርስትያኖችን በሃሰት መወንጀል በተፈለገበት በዚያን ጊዜ ፤ ክርስትያኖችን በዚህ ጥፋት ውስጥ እንዲጠየቁ እንደረጉ ይታመናል። ዋነኞቹን ክርስትያኖች ጴጥሮስና ጳውሎስን በዚህ ጉዳይ ይፈለጉ ነበር። እነሱም ሕይወታቸውን ያጡት በዚህ ጊዜ ነበር። ስለዚህ የሐዋርያቶች ሞትና በተጨማሪም ሌሎች ለኢየሱስ ቅርብ የነበሩት ሰዎች ህይወታቸውን መገበራቸው፤አንዱ ውጫዊ ምክንያቶች ሊሆኑ የሚችሉ ሁነቶች እንደሆኑና፤ የማርቆስን ወንጌል በተመለከተ በእነዚህ ጉዳዬች ዙሪያ ተያያዥነት ያለቸው ሃሳቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ፤ በአእምሮአችን መያዝ በጣም አስፈላጊ ነው።

ሌላኛው ውጫዎ ታሪካዊ ምክንያት፤ የአዳዲስ ክርስትያኖችን እምነት ለማስተካከል የሚጠቅም ታሪክን የመሰበሰብ ፍላጎት በዚሁ ጊዜ የነበረ መሆኑ ነው። በግሪኮ ሮማን ዘመን፤ አለም ከዳር እዳር የክርስትና ሃሳብ የተስፋፋበት ጊዜ መሆኑ፤ ከሶስተኛው ውጫዊ ታሪካዊ ምክንያት ጋር የጠለቀ ግንኙነት አለው። ክርስትና ሲስፋፋ፤ አዳዲስ ክርስትያኖችን መመሪያ የመስጠት ፍላጎት ብቻ ሳይሆን፤ ነገር ግን በተጨማሪም ከአፈ ታሪክ ይልቅ የተፃፈ ታሪክ (ባህል) እንዲኖር የመፈለግ ሁኔታ በወቅቱ ነበር። ይህም በርግጥ ቃላዊ (አፋዊ) ባህል ነበር፤ ነገር ግን በቀደመው የክርስትያን እንቅስቃሴ ውስጥ ዋናው ነጥብ ፤የኢየሱስን ታሪክ መጻፍ አስፈላጊ መሆኑ ነበር።

በዚህ ነጥብ ላይ የተገለፀው፤ የመጨረሻ ውጫዊ ታሪካዊ ምክንያት፤ክርስትያኖችን ከአይሁድ ሃይማኖት የመለየት ፍላጎት ነው። ይህ በተለይ አስፈላጊ ሆኖ የመጣው በቤተ መቅደሱ መፍረስ አቅራቢያ ባለው ጊዜ ነው። ከ 66 ዓ.ም እስከ 70 ዓ.ም በሮማውያን በአይሁድ መካከል የተደረገው ጦርነት፤ ክርስትያኖች በዚህ ጦርነት መካፈል አለባቸው ወይንም የለባቸውም የሚለውን ጥያቄ አስነስቶ ነበር። በአይሁዶች ወገን መቆም ነበረባቸው እናም ሮማውያን በርግጠኛነት ይህንን ማወቅ ይፈልጉ ነበር። የወንጌል መልዕክት በተለይ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ፤ ኢየሱስ በምድር ላይ የጦርነትን ጊዜን ለማመቻቸት እንዳልመጣ፤ እውነቱን አጉልቶ የሚያሳይ ይመስላል። ክርስትያኖችን ከይሁዲዎች የምንለይበት መንገድና መልስ በተወሰነ መልኩ ይህ ሊሆን ይችላል።

ሁኔታው

ሁኔታውን ከሁለቱም፤ ማለትም ከውጫዊ እና ውስጣዊ ባህል (ወግ) አኳያ ልንመለከተው ይገባል። እንደ ውጫዊ ባህል አገላለፅ፤ የማርቆስ ወንጌል የተፃፈው ለሮም ከተማ ነው ይላሉ። ይህ በ1 ጴጥ 5፡13 ውስጥ ይገኛል፡ የሚያወራውም በጴጥሮስና በማርቆስ መካከል ስላለው የተለየ ቅርርብ ነው። ከባቢሎን የተላከ ሰላምታም በዚህ ቦታ አለ፤ ባቢሎን የሚለው ለሮም የተሰጠ ምስላዊ እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል። ይህ ወንጌል፤ በሮም እንደተፃፈ የሚያገናኝ አንዱ ክፍል ነው።አንድ ሰው ይህንን እንዴት ያውቃል? ውስጣዊ ባህል በዚህ ጉዳይ ላይ የተወሰነ ምልከታን ይሰጣል? በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ፤ተደራሲው ከአይሁዳውያን ልማዶች ጋር የተሳሰረ እንደሆነ አውነታን በግልፅ የሚያሳዩ ጥቂት የሚስቡ ነገሮች አሉበት። አዋቂዎች እንደሚሉት፤ የማርቆስ ወንጌል ከማቴዎስ ወንጌል አይሁዶች ባነሰ መልኩ እንደ ተገለፁበት ይናገራሉ። አንድ ሰው ይህንን እንዴት ያውቃል?

ማርቆስ 7፡1–4 ለዚህ ጉዳይ የተወሰነ ማመላከቻን ይሰጣል፤

> ፈሪሳውያንና አንዳንድ የህግ መምህራን፤ ከኢየሩሳሌም የመጡትም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። ከደቀመዛሙርቱም አንዳንድ በርኩስ ማለት ባልታጠበ እጅ እንጀራ ሲበሉ አዩ። ፈሪሳውያንም አይሁድም ሁሉ፤ የሽማግሌዎችን ወግ ሲጠብቁ እጃቸውን ደህና አድርግው ሳይታጠቡ አይበሉምና፤ ከገበያም ተመልሰው ካልታጠቡ አይበሉም፤ ዕዋንም ማድጋንም የናስ ዕቃንም አልጋንም እንደ ማጠብ ሌላ ነገር ሊጠብቁ የተቀበሉት ብዙ አለ።

የቁጥር 3 እና 4 ሃሳብ መያዝ ተገቢ ነው የዚህ ዕሁፍ ተደራሲያን ይሁዲዎች ከሆኑ፤ በርግጠኛነት እጅ ከመታጠብ ባህል ጋር የሚተዋወቁ ናቸው። ነገር ግን፤ የማርቆስ ተደራሲዎች ግን ፤ከዚህ ልምድ ጋር የማይተዋወቁ በመሆናቸው፤ የዚህ ቁጥር ገለፃ በታም አስፈላጊ ነው።

ተደራሲዎቹ

ምናልባት የማርቆስ ተደራሲዎች ሮማውያን ነበሩ። ምክንያቱም ሮማውያን ከአይሁዶች ልማድ ጋር አይተዋወቁም ነበር። ስለ ተደራሲዎች አመላካች የሆነ ሌላኛው አስፈላጊ እውነት ደግሞ፤ ማርቆስ በርከት ያሉትን የአርማይክ ቃላት ወደ ግሪክ መተርጎሙ ነው። ለምሳሌ እነዚህ ክፍሎች ፤ይህንን እውነት ያሳያሉ፤ ማር 3፡17, 5፡41, 15፡22 እና 15፡34።ማርቆስ የኢየሱስን የመስቀል ላይ የመጨረሻ ቃል ዘግቧል። ‹ኤሎሄ

ኤሌሄ ላማ ሰበቅተኒ› ይህንን በመተርጎም ‹አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ› በሚል ዕፎታል (15፡34)። ከአርማይክ ወደ ግሪክ ትርጉም መኖሩ የሚያሳየው፤ የማርቆስ ተደራሲዎች ለአርማይክ ቋንቋ እንግዳ እንደሆኑ የሚነግረን ነገር ነው።

በግልፅ የሚታዩ ጭብጦች

በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ በርከት ያለ ጭብጦች አሉ። ይሁንና ለዚህ ጥናት ዓላማ ሲባል፤ ሁለት ጭብጦች ላይ ብቻ ትኩረት ይደረግባቸዋል። በመጀመርያ፤ በማርቆስ ወንጌል ላይ ፤ በኢየሱስ መከራና ሞት ላይ ትኩረት ይሰጣል። ማርቲን ኬይለር፤ የአዲስ ኪዳን አዋቂ፤ በዚህ ክፍለ ዘመን ፅሁፉን ቀድሞ ፅፏል። የማርቆስ ወንጌል ረዘም ያለ የሚስብ ትረካን የያዘ መግቢያ እንዳለው ተናግሯል። የሚሰበው ትረካ ባጠቃላይ ምዕራፍ 11ን ከግምት ውስጥ ያስገባል። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባና ውጥረቱ ሲጀምር፤በሁሉ መንገድ እስከ ምዕራፍ 16 የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ሁነቶች ይታያሉ። ማርቲን ኬይለር የማርቆስ ወንጌልን የሚስብ ትረካን ለማስተዋቅ አንደሆነ ያሳያል። ሪቻርድ ሄይስ፤ በቅርብ በሰጠው መልስ፤ የማርቲን ኬይለር ሃሳብ በማስፋት፤ የማርቆስ ወንጌል የሚስብ ትረካ ያለው እንደሆነ የራሱን ሃሳብ ያቀርባል። ይህም፤ በኢየበማስረዳትሩሳሌም የተገደበ ብቻ እንዳልሆነ ይገልጻል። ነገር ግን፤ በርግጥ አጠቃላይ የማርቆስ ወንጌል ስለ ኢየሱስ መከራ ያወራል። ይህ የማርቆስ ወንጌል ዋነኛ ጭብጥ ነው። ሁለተኛው፤ በግልፅ የሚታየው ጭብጥ፤ የኢየሱስን መከራና ሞት ከደቀ መዘሙርቱ ጋር የሚያያይዘው ሲሆን፤ የአውነተኛ ደቀ መዛሙርትነት ጉዳይ ነው። በማርቆስ ወንጌል ውስጥ፤ ይህ ጭብጥ ለወንጌል ሲባል፤ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ራስን መስዋእት ማድረግ በሚገባ ሊገለጽ ይችላል። ማርቆስ 8፡34 እና 10፡45 ትኩረት የተሰጠባቸው ሁለት ክፍሎች ናቸው። ‹በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ› የሚለው ነው። ይህ ቁጥር በግልፅ አንደሚያሳየው፤ ደቀ መዛሙርትነት ከመከራ ጋር የጠለቀ ግንኙነት እንዳለው ነው።‹እንግዲህ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲገለግሉት አልመታም›፡(10፡45) የሚለው ክፍልም፤ የኢየሱስ ህይወት ራሱ ቤዛ ለሆን የመጣ እንደሆነ ያሳያል። አጠቃላይ የመከራው ጉዳይ ፤ከኢየሱስ ህይወትና ለደቀ መዛሙርቱ ከሰጣቸው ጉዳይ ጋር የጠለቀ ግንኙነት አለው።

የማርቆስ መፅሃፍ ማውጫ (ቅደም ተከተል/መመሪያ)

የማርቆስ ወንጌል አራት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። በመጀመርያ ማርቆስ 1፡1–15 ሲሆን፤ ይህም መግቢያ ነው። በዚህ መግቢያ ውስጥ፤ ማርቆስ በቀሩት የማርቆስ ወንጌል አጠቃላይ ክፍል ውስጥ በድጋሚ የሚታዩትን ብዙ ዋነኛ ጭብጦችን ያስቀምጣል። ይህ መግቢያ የኢየሱስ በአለም ውስጥ ያለ አገልግሎት መጀመርያ ተብሎ ሊጠራ ይችላል።ከ ማርቆስ 1፡16 ተያይዞ እስከ 8፡21፤ ሁለተኛው ዋነኛ ክፍል ነው። ይህ ክፍል የወንጌል ሃይል ተብሎ ሊጠራ ይችላል።በዚህ ክፍል ውስጥ፤ ኢየሱስ ብዙ ተግዳሮት የነበረበትና ጠላትን የተቃወመበትን ቦታ ነው። ሶስተኛው ዋነኛው የማርቆስ ወንጌል ክፍል ከ8፡22 እስከ 15፡47 ያለው ነው። ይህ ክፍል የመከራው ሃይል ፤ (ኢያሱስ ደቀመዛሙርቱን ማረከበት) ተብሎ ሊጠራ ይችላል። በመጨረሻም፤ የመጨረሻው ክፍል ምዕራፍ 16 ቀጣይነት ያለው ነው። የመጨረሻው መጀመርያው ብቻ ነው ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

መግቢያ

ማርቆስ 1፡1–15 የዚህን ወንጌል ‹የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ወንጌል መጀመርያ›የሚለውን መግቢያ ይዟል። በትንቢተ ኢሳያስ ውስጥ እንዲህ ተጽፏል፤ ‹እነሆ መንገድን የሚጠርግ መልዕክተኛን በፊትህ እልካለሁ፤የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ›። እናም ዮሐንስም በምድረ በዳ እያጠመቀ የንስሃንም ጥምቀት ለሃጢያት ስርየት እየሰበከ መጣ።የይሁዳም አገር ሁሉ የኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር። ሃጥያታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስም ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር። ዮሐንስም የግመል ጠጉር ለብሶ፤ በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ የበርሃ ማርም ይበላ ነበር። ተጎንብሼ ጫማውን ጠፍር መፍታት የማይገባን ከእኔ የሚበረታ በኋላዬ ይመጣል። እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል፡

> በዚያም ወራት ኢየሱስ ከገሊላ ናዝሬት መጥቶ ከዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። ወዲያውም ከውሃ በወጣ ጊዜ ሰማያት ሲቀደዱ መንፈስም እንደ እርግብ ሲወርድበት አየና የምወደው ልጄ አንተ ነህ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምጽ ከሰማያት መጣ። ወዲያው መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው። በምድር በዳም በሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ ከአራዊትም ጋር ነበረ፤ መላዕክቱም አገለገሉት። ዮሃንስም አልፎ ከተሰጠ በኋል ኢየሱስ የእግዚአብሄርን መንግስት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም አመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ።

በርከት ያሉ ጠቃሚ ጭብጦች በዚህ በማርቆስ ወንጌል መግቢያ ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ጭብጦች በጥቂቱ ‹ወንጌል› የሚለው ስያሜ፤ ስያሜዎቹ ‹የሰው ልጅ› እና ‹የእግዚአብሔር ልጅ›፤ አጠቃላይ ‹የጥምቀት ጭብጥ›፤ እና ‹የእግዚአብሔር መንግስት› ጭብጥ በግልፅ ተዕፊው ይገኛሉ፡፡

ወንጌል

ወንጌል የሚለው ስያሜ ከግሪክ የመጣ ቃል ሲሆን፤ ኢዋንጀሊዮን በሚል ተገልጧል፡፡ ትረጓሜውም ፤ቃል በቃልም ‹መልካም ዜና› ማለት ነው፡፡ በአንዳንድ መንገድ፤ ማርቆስ 1፡1 ‹የእግዚአብሔር ልጅ፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመርያ› የሚለው ቅጥር የማርቆስ ወንጌል ርዕስ አንደሆነ እግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ ይህ ርዕስ ከሆነ፤ ማርቆስ ትረካውን ‹ወንጌል› የሚለውን ቃል የተጠቀመ ብቸኛ ሰው ነው፡፡ በተጨማሪም፤ ወንጌል የሚለው ስያሜ፤ በመፅሃፉ ሌሎች ክፍሎች፤ ሁሉ ላይ ይታያል፤ እምነት (1፡15) እና አጠቃላይ ዝግጁነትን (10፡29፣30) ይጠይቃል፡፡ ማርቆስ 10፡29፣30

> እውነት እላችኋለው፤ስለ እኔና ስለ ወንጌል ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እህቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንም እህቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ በሚመጣው አለም የዘላለም ህይወት የማይቀበል ማንም የለም፡፡

ስለ ወንጌል ብሎ ሁሉን ነገር መስጠት ይገባል፡፡

የእግዚአብሔር ልጅ

የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው ስያሜ፤ አንደሚታወቀው ለኢየሱስም ለአማኞች ሁሉ ተጠቅሚበታል፡፡ በክርስቶስና በአማኞች **ልጅነት** መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምን እንደሆን ታስባለህ?

_____

_____

ሁለተኛው ዋነኛው ጭብጥ በመግቢያ ውስጥ የተገለፀው የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው ስያሜ ነው፡፡ ስያሜው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው፤ በሁለተኛው ወንጌል ውስጥ ድራማዊ ስያሜ ነው፡፡ ከመግቢያው በተጨማሪም፤ እንደ ማርቆስ ስያሜ ፤ በወንጌሉም ታሪክ ውስጥ ሁሉ እንደ ስያሜ ታይቷል፤ ይህንንም እግዚአብሔር ብቻ ወይም ሌላ መንፈሳዊ ፍጥረት ተረድቶታል(1፡11 እና 9፡7 ተመልከት)፡፡ ከሰማይ የመጣው ድምጽ፤ ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በግልፅ አሳውቋል፡፡ ከዚያም በኋላ፡ ርኩሳን መናፍስት በ 3፡11 እና 5፡7 ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አውቀውታል፡፡ ‹የእግዚአብሔር ልጅ› የሚለው ስያሜ፤ እስከ ምዕራፍ 14፡61,62 ድረስ ታውቆ የነበረው በመንፈሳዊ ፍጥረት ብቻ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር ሊቀ ካህኑ ኢየሱስን የጠየቀው፡፡ ‹ደግሞም ሊቀ ካህናቱ ጠየቀውና የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን አለው፡፡ ኢየሱስም እኔ ነኝ›፡፡ በዚያ እንኳን፤ የሊቀ ካህኑ ጥያቄ ምፀታዊ ነበር፡፡ በርግጥም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብሎ አላመነም ነበር፡፡ ከዚያም፤ ኢየሱስ ስያሜ (መጠሪያ) የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በመጨረሻ የተገለፀው፤ የመቶ አለቃው ባደረገው ምስክርነት ነበር፡፡ (15፡39) መቶ አለቃውም እንዲህ አለ፤ ‹ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበር አለ›፡፡

ማርቆስ ይህንን ጭብጥ በወንጌሉ ሁሉ በመያዝ የሄደው ምን ለማስጨበጥ ሞክሮ ነው? ምናልባት፤ማርቆስ የኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅነት ፤ ፍጥረት በርግጥ የሚረዳበት ብቸኛው መንገድ ፤ ኢየሱስን በሞቱ ውስጥ ሲያየው ነበር ብሎ ይሰማው ነበር?

የእግዚአብሔር መንግስት

በማርቆስ 1፡15 ላይ ኢየሱስ አለ ‹የእግዚአብሄር መንግስት ቀርባች፤ ንስሃ ግቡ በወንጌልም እመኑ›፡፡ ከሁሉ በፊት፤ በቅድሚያ ‹የእግዚአብሔር መንግስት› ማለት፤ እግዚአብሔር የሚገዛበት ወይም የሚነግስበት ነው፡፡ የግድ የተወሰነ ግዛት ወይንም ቦታ ላይሆን ይችላል፡፡ (የት አንደሆነ የሚገልፁ ቁጥሮች አሉ)፡፡ ነገር ግን በቅድሚያ ንግስናን ያሳያል፡፡ ያም፤ አግዚአብሔር ያለበት፤ መንግስቱ ነው፡፡ የእግዚአብሄር መንግስት እግዚአብሔር የሚሰጥበት ወይንም ከእግዚአብሔር የሆነ ነገር ነው፡፡ሰዎች ሊገነቡት ወይም ሊሰጡት የሚችሉት ነገር አይደለም፡፡ ያለ እግዚአብሔር ሚና እና ያለ እግዚአብሔር እቅድ፤ ፍጥረታት የእግዚአብሔርን መንግስት በተመለከተ ምንም ነገር ሊያደርጉ አይችሉም፡፡ እናም በመጨረሻ፤ የእግዚአብሔር መንግስት ፤የኢየሱስ ትምህርት ማዕከላዊ ሃሳብ ነው፡፡ (1፡14,15 ተመልከት)

በኢየሱስ ምሳሌዎች ውስጥ፤ በብዙ የትምህርቱ ክስተት ውስጥ፤ የሚጀምረው የእግዚአብሄር መንግስት ምን እንደምትመስል በመግለፅ ነው። መንግስቱን በግልጽ ለማወጅ ነው ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው። ይህ ምዕራፍ፤ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ያለውን ጉዞ ይቀጥላል። በምዕራፍ 10 ውስጥ፤ መግቢያውን እና በመጀመርው 15 ቁጥሮች ውስጥ ከዳሰሳቸው፤ ከብዙ ጭብጦች መካከል ሶስቱን በጥልቀት ያብራራል። ወንጌሉ፤ ስያሜው(መጠሪያው) (የእግዚአብሔር ልጅ) እና የእግዚአብሄር መንግስት የሚለው ሐረግ። ይህ ምዕራፍ፤ የሁኔታዎችን ቅደም ተከተልንና ወደ ሁለተኛው ወንጌል የሚወስደውን ጉዞ በማመላከት ይቀጥላል።

ውድ ተማሪዎች፤ ስለ እግዚአብሄር መንግስት ፤በጣም አስፈላጊ ስለሆነው ስለዚህ ቃል፤ ሰፋ ያለ አውቀት እንዲኖራችሁ፤ የራሳችሁን ቀጣይ ጥናት አድርጉ።

የወንጌሉ ሃይል፤ ኢያሱስ ተቃዋሚዎቹን ተቃወመ

የቅደም ተከተሉ ሁለተኛ ክፍል ከማርቆስ 1፡16 እስከ 8፡21 ድረስ ነው። ይህ ክፍል በጣም ታወቂ በሆነው አንቀጽ ይጀምራል። ከማርቆስ 1፡16–20፤ ይህ ክፍል የደቀ መዛሙርቱን መጠራት ይገልጻል።‹ በገሊላ ባህር አጠገብ ኢየስስ ሲያልፍ፤ ስምዖንና ወንድሙን እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባህር ሲጥሉ አየ፤ አሳ አጥማጆች ነበሩና። በኋላዬ ኑና ሰዎች አጥማጅ አደርጋችኋለሁ አላቸው።ወዲያውም መረባቸውን ጥለው ተከተሉት። ከዚያም ጥቂት አለፍ ብሎ፤ የዘብዲዮስ ልጅ ያዕቆብንና ወንድሙንም ዮሐንስን ደግሞ በታንኳ ላይ መረባቸውን ሲያዘጋጁ አየ። ወዲያውም ጠራቸው፤ አባታቸውንም ዘብዲዎስን ከሞያተኞች ጋር በታንኳ ላይ ትተው ተከትለውት ሄዱ›። በርግጥ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለምን ጠራቸው? ሰውን አጥማጆች ሊያደርጋቸው ነው ?ነገር ግን ሌላ ምክንያት ይኖር ይሆን? በምዕራፍ 3 ውስጥ፤ አንባቢዎች የተለየ ግንዛቤ ያገኛሉ። በማርቆስ 3፡13–19፤ ‹ኢየሱስ ወደ ተራራም ወጣ፤ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፤ እና....ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክም እንዲልካቸው፤ ድውችንም ሊፈውሱ ፤ አጋንንትንም ሊያወጡ ስልታን ሆንላቸው ዘንድ አስራ ሁለት አደረገ።› (ቁጥር 14) ስለሆንም በማርቆስ 3፡13–19፤ኢየሱስ ለምን ደቀመዛሙርቱን እንደጠራቸው፤ ሶስት የተለያዩ ተግባረት ወይንም ምክንያትን አስቀምጧል፤ ይህም መንግስቱን እንዲሰብኩ፤ አጋንንትን እንዲያስወጡ እና ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ። የመጀመሪያዎች ሁለት ምክንቶች የኢየሱስን በጠላት ላይ ያለውን ተቃውሞ ጠብቆ ማስቀጠል እንደሚፈልግ ለማሳየት ነው፤ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን የጠራበት ሶስተኛው ምክንያት በቀላሉ አብረውት እንዲሆን ነበር። ተመልካች እንዲሆኑ ብቻ አልተጠሩም ፤ ተካፋይ እንዲሆኑና አብረውት እንዲሆኑ ነበር።

ተዓምራቶች

ማርቆስ ፈውሶችን፤ ክፉ መንፈስ ማስወጣትንና ሌሎች ተዓምራቶችን በተከታታይ ዘግቧል ይህም አግዚአብሔርን ፍጥረትን ወደራሱ ለመመለስ ያለውን ፍላጎት ይገልፃል።ለምሳሌ የጴጥሮስ አማት በንዳድ ታማ እንደነበር ይገልፃል። በ ማር 1፡29–31 ውስጥ ኢየሱስ እንዴት ቤቷ ገብቶ እንደፈወሳትና አሷም ወዲያውኑ እንደተፈወሰችና አንዳገለገለቻቸው ማርቆስ ይነግረናል።። የኢየሱስ ሰዎችን የመመለስ ሃይሉን በሌላ ምሳሌ በምዕራፍ 15 ላይ እናገኛለን። ኢየሱስ በጌርጌሴኖን በርኩስ መንፈስ ከተያዘው ሰው ውስጥ ርኩስ መንፈስ አስወጥቷል። በታሪኩ መጨረሻ ላይ፤ኢየሱስ ሊሄድ ሲሞክር፤አጋንንት አድረውበት የነበረው ሰው፤ ከእርሱ ጋር እንዲኖር ለመነው፤ ኢየሱስም አልፈቀደለትም፤ ይልቁንም ወደ ቤትህ፤ በቤተሰቦችህ ዘንድ ሄደህ ጌታ እንዴት ያለ ነገር እንዳደረገልህ አውራላቸው አለው(ቁጥር 19) ። ከዚያም ለየት ያለ ተዓምራት ፤ አምስት ሺ ሰዎች በመመገብ ተከስቷል። አብረውት የቆዩትን ሰዎች ደቀ መዘሙርቱ ማሰናበት ፈልገው ነበር፤ ይሁንና ኢየሱስ ያለውን ነገር በመባረክ፤ እነሱን በመመገብ ተጠንቅቆላቸዋል።ከ1፡16 አስከ 8፡21 ባሉት መካከለኛ ክፍሎች ውስጥ የሚታዩት የኢየሱስ ተዓምራቶች የሚጠቁሙት፤ እግዚአብሔር ፍጥረትን ለመታደግ ያለውን ፍላጎት ነው። በዚሁ ክፍል ጠላትን ድል ማድረግ ተጀምሯል።

ምሳሌዎቹ

በኢየሱስ ድርጊቶች መሃል የእግዚአብሔርን መንግስት ይወክላል። የዘሪውን ምሳሌም ይነግረናል።ይህ ምሳሌ ቢያንስ ሁለት ዋና ነጥቦችን ግልፅ አድርጎ ያሳየናል። በምሳሌ ብዙ ያስተምራቸው ነበር፤በትምህርቱም አላቸው፤‹ ስሙ እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ። ሲዘራም አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀና ወፎች መጥተው በሉት ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀና ጥልቅ መሬት ስላልነበረው ደረቀ። ሌላው በእሾህ መካከል ወደቀ እሾሁም ወጣና አነቀው ፍሬም አልሰጠም። ሌላው በመልካም መሬት ላይ ወደቀና ወጥቶ አድጎ ፍሬ ሰጠ አንዱም ሰላሳ አንዱም ስድሳ አንዱም መቶ አፈራ። ጆር ያለው ይስማ

በኢየሱስ የዘረው ምሳሌ ውስጥ ሊሰመርባቸው የሚገቡ ሁለት አበይት ጉዳዮች ያሉ ይመስላል፡ የእግዚአብሔር ፀጋ እና ከእግዚአብሔር የሆነ መገለጥ። ዘሩ በሁሉ ቦታ በጭንጫና በእሾህ መሃል ሳይቀር ተዘርቷል። በባህላዊ አነጋገር፤ ይህ ምሳሌ በተነረበት ጊዜ፤ መሬት ውድ ነበር። ስለዚህም፤ በዚያ ጊዜ የነሩ

ገበሬዎች በእሾህና በጭንጫ ላይ ሳይቀር ለመዝራት አንደሚሞክሩ ያልተለመደ ነገር እንዳልነበረና፤ ዘርም በዚያ ቦታ ለማብቀል እንደማይቻል አያስቡም ነበር። ይህንንም የኢየሱስ ምሳሌ ግልጽ ያደርጋል። እናም በዚህ መንገድ የእግዚአብሔር ፀጋ በሁሉ ቦታ ይሆናል። የወንጌል ዘር በእሾኅና በጭንጫ መኃል ሳይቀር ይበቅላል። የዚህ የሁለተኛው ዋነኛ ምሳሌ ጭብጥ ከእግዚአብሔር የሆነ መገለጥ አስፈላጊ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል። ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ መጥተው፤ ለምን በምሳሌ እንደሚናገር ጠይቁት፤ እንዲህም አላቸው ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግስት ሚስጥር ማወቅ ተሰጥቶኃል፤ በውጭ ላሉት ግን ሁሉም ነገር በምሳሌ ይሆንባቸዋል። (4፡11) ስለሆነም፤ ይህንን ለመረዳት ከእግዚአብሔር የሆነ መገለጥ አስፈላጊ ነው ማለት ነው።

የመከራው ሃይል፤ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማረከ

ሶስተኛው የማርቆስ ወንጌል ዋነኛ ጭብጥ ክፍል፤ ከማርቆስ 8፡22 በመጀመር እስከ 15፡47 ድረስ ይቀጥላል። በዚህ ክፍል ውስጥ፤ ኢየሱስ በመከራው ሃይል ውስጥ ደቀ መዘሙርቱን እንደ አሸነፋቸው አንባቢው መመልከት ይችላል። በዚህ ሶስተኛው የወንጌል ክፍል ውስጥ፤ ኢየሱስ ሌላኛውን የሃይል ገፅታ ገልጧል። ክፉ መንፈስን የሚያወጣ፤ በተፈጥሮ ላይ ሳይቀር አስደናቂ ተዓምራትን የሚያደርግ እና በሰዎች አካላዊ ህይወት ላይ ፈወስ የሚያመጣ ተደርጎ ብቻ የተወሰደ ሰው ሳሆን፤ ነገር ግን ይህ ክፍል፤ ሌላኛውን የሃይሉን ገፅታ ማለትም በመከራው ሃይል ደቀመዛሙርቱን ያሸነፈበትን ያሳየበት ነው። ኢየሱስ ሞቱን በተመለከተ ሶስት ዋና ቅድመ ትንበያዎችን ሰጥቷል። በተለያዩ ሶስት ጊዜያት ውስጥ፤ በማርቆስ 8፡27 ጀምሮ እስከ 9፡1 ይዘልቃል። ኢየሱስ ለዓላማ እንደመጣና ይህም ዓላማ ለመሞት እንደነበር በግልፅ ይተነብያል።

1. ኢየሱስ ክርስቶስ አንደነበር የጴጥሮስ ምስክርነት

ማርቆስ 8፡27 ስለሚከተሉት ሁነቶች ይነግረናል፤ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም በፊልጶስዩስ ቂሳርያ ወዳሉ መንደሮች ወጡ። በመንገድም ሰዎች እኔ ማን እንደሆንሁ ይላሉ ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው። እነርሱም መጥመቁ ዮሀንስ ሌሎቹም ኤልያስ ሌሎችም ከነቢያት አንዱ ብለው ነገሩት። እናንተስ እኔ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ ብሎ ጠየቃቸው፤ ጴጥሮስም አንተ ክርስቶስ ነህ ብሎ መለሰለት። ስለ እርሱም ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው። የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል፤ከሽማግሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጻፎችም ሊጣል፤ ሊገደልም ከሶስተኛ ቀንም በኋላ ሊነሳ ፤እንዲገባው ያስተምራቸው ጀመር። ቃሉንም ገልጦ ይናገር ነበር። ጴጥሮስም ወድ እርሱ ወስዶ ይገስጸው ጀመር። እርሱ ግን ዘወር አለ፤ ደቀ መዛሙርቱንም አይቶ ጴጥሮስን አይቶ ገሰፀውና፤ ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብም አለው። ይህ ስለሚመጣው ሞት የመጀመርያ ቅድመ ትንበያው ነው። የጴጥሮስ ምስክርነት ያልተለመደ አልነበረም። ለምሳሌ በመጀመርያው ክፍለ ዘመን አይሁዶች መሲሁን የሚጠብቁበትን መንገድ ማዕከል ያደረጉ ጥቂት መሰረታዊ ነጥቦችን እንመልከት። ከሁሉ በፊት፤ ባጠቃላይ በጁዲዝም መሰረታዊ የመሲሁ ተስፋ ነበራቸው። አብዛኛው አይሁዳውን ስለ መሲሁ መምጣት ያምናሉ። ነገር ግን፤ በሁለተኛ ደረጃ፤ ይህም ብሄራዊ መሲህ፤ የንጉስ ዳዊት ወራሽ የሆነ፤ ፖለቲካዊ እንድምታ ያለው መሲህ እንደሆነ ተስፋ ያደርጋሉ። በሶስተኛ ደረጃም፤ የአብዘኞቹ አይሁዶች መሰረታዊ ተስፋ፤ ፖለቲካዊ አንድምታ ያለው ብቻ ሳሆን፤ ከመሲሁ የሚጠብቁት አንዳንድ ጉዳዮች እንደሚኖሩም ይህን ሃሳብም በመያዝ ጭምር ነው። የእስራኤልን የፖለቲካ ጠላቶች አሸቀንጥሮ የሚጥል እንደሆነ ያስባሉ። የተመረጡትን ህዝቦች በአዲሱ ፤የዳዊት መንግስት ውስጥ ሊመሰርታቸው እንደሆነ ያስባሉ። የእግዚአብሔርን መንግስት የሚያስተዋውቅ እንደ ሆነ ይጠብቃሉ። እንደዚህ ያለ መሲህ ነው፤ አብዛኞቹ አይሁዳውያን ይጠብቁ የነበረው። ጴጥሮስም ምስክርነት የሰጠው ፤እንደዚህ አይነቱን መሲህ ስለሚጠብቅ ይመስላል። ስለሆነም፤ ኢየሱስ የመጀመርያውን ቅድመ ትንበያ ሲያቀርብ ፤ በኢየሱስና በደቀ መዘሙርቱ መካከል ውጥረት ተፈጥሮ ነበር።

2. ህፃኑ ታላቅ ነው

የሁለተኛው የኢየሱስ ሞት ዋነኛው ትንበያ በማርቆስ 9፡30–37 ይገኛል። ያንን ቦታ በመተው በገሊላ በኩል አለፉ።

> ኢየሱስ ማንም ያውቅ ዘንድ አልወደደም፤ ምክንያቱም ደቀ መዛሙርቱንም ያስተምር ስለ ነበር፤ ለአነርሱም- የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አሳልፎ የሰጣል ይገድሉትማል ተገድሎም በሶስተኛው ቀን ይነሳል ይላቸው ነበር። እነርሱም ነገሩን አላስተዋሉም፤እንዳይጠይቁትም ፈሩ። ወደ ቅፍርናሆም መጣ። በቤትም ሆኖ ፤በመንገድ እርስ በርሳቸው ምን ተነጋገራችሁ ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱ ግን በመንገድ ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን ተባብለው ነበርና ዝም አሉ። ተቀምጦም አስራ ሁለቱን ጠርቶ ሰው ፊተኛ ሊሆን ቢወድ ከሁሉ በኋላ የሁሉም አገልጋይ ይሁን፡ ህፃንም ይዞ በመካከላቸው አቆመው፤ አቅፎም እንደዚህ ካሉ ህፃናት አንዱን

> በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ የሚቀበለኝም ሁሉ የላከኝን እንጂ እኔን አይቀበልም አላቸው።

በዚህ ሁለተኛ የኢየሱስ ሞት ቅድመ ትንበያ፤ ማንም ታላቅ ሊሆን የሚወድ ቢኖር እንደ ህፃን መሆን እንዳለበት አንባቢው መረዳት ይችላል።

3. ፊተኛ ሊሆን ቢወድ የሁሉ አገልጋይ ይሁን

የኢየሱስ ሞት ሶስተኛው ቅድመ ትንበያ፤ የኢየሱስን ሌላኛ ሃይል ላይ፤ (የመከራው ሃይል) ያተኩራል። ይህ በማርቆስ 10፡32–45 ውስጥ ይገኛል። ድርጊቱ ከቁጥር 32 ይጀምራል።

> ወደ ኢየሩሳሌም ሊወጡ በመንገድ ነበሩ፤ ኢየሱስም ይቀድማቸው ነበርና ተደነቁ፤ የተከተሉትም ይፈሩት ነበር። ደግሞም አስራ ሁለቱን ወደ እርሱ አቅርቦ ይደርስበት ዘንድ ያለውን ይነግራቸው ጀመር። እነሆ ወደ እየሩሳሌም እንወጣለን የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለፃፎች አልፎ ይሰጣል የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፤ ለአህዛብ ኣሳልፈው ይሰጡታል፤ ይዘብቱበታል ይተፉበትማል፤ ይገርፉትማል፤ ይገድሉትማል በሲሶስተኛውም ቀን ይነሳል አላቸው። የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ወደ እርሱ ቀርበው መምህር ሆይ የምንለምንህን ሁል እንድታደርግልን እንወዳለን አሉት። እርሱም-ምን ላድርግላችሁ ትወዳላችሁ አላቸው። እነርሱም በክብርህ ጊዜ አንዳችንን በቀኝ አአንዳችንንም በግራ መቀመጥ ስጠን አሉት። ኢየሱስ ግን የምትለምኑትን አታውቅም። እኔ የምጠጣውን ፅዋ ትጠጣላችሁ እኔ የምጠመቀውን ጥምቀት ትጠመቃላችሁ፤ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ የምሰጥ እኔ አይደለሁም አላቸው። አስሩም ሰምተው በያዕቆብና በዮሐንስ ይቆጡ ጀመር። እየሱስም ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ የአሕዛብ አለቆች ተብሎ የምታስቡት እንዲገዙዓቸው ታላላቆቻቸውም በላዮቻቸው ላይ እንዲሰለጥኑ ታውቃላችሁ። በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፤ ከእናንተ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባርያ ይሁን። እንዲህ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።

በኢየሱስ ሶስተኛው ቅድመ ትንበያ ውስጥ፤ ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ አገልጋይ መሆን እንዳለበት ነግሯቸዋል። በመጀመሪያው ቅድመ ትንበያ፤ አብዛኞቹ አይሁዳውያን እንደሚጠብቁት፤ መሲሁ ዓለማዊ በሆነው ሃይል ወይም በፖለቲካዊ ሃይል አልመጣም። ነገር ግን የመጣው ለመሞት ነበር። በሁለተኛው ቅድመ ትንበያ ፤በማርቆስ 9፡30–37 ውስጥ፤ህጻኑ የሁሉ የበላይ እንደሆነ አንባቢው እንዲገነዘብ ያደርጋል። በመጨረሻም፤ በሶስተኛው ቅድመ ትንበያ፤ ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ አገልጋይ መሆን እንዳለበት አንባቢው ይማራል።ደቀ መዛሙርትንት የመስቀሉን ሃይል መረዳትን ያካትታል፤ እንጂ የአለምን ሃይል አይደለም።በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የተገለጸውም ከልብ የሆነ እውነተኛ ደቀ መዛሙርትነት በዚህ መልክ መገለፅ እንዳለበት ማርቆስ ያሳያል።

ትኩረት ያለው ትረካ

በማርቆስ 11 ውስጥ፤ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ። ኢየሩሳሌም ሲገባ፤ በኢየሱስ አስተምህሮና በማንነቱ ላይ በቤተ መቅደስ ውጥረት ነግሷል። ከማርቆስ 11፡1, 13፡37፤ በኢየሱስ ትምህርትና በስልጣኑ ላይ ቁጣ እደተቀሰቀሰ ያሳያል። በማርቆስ 14፡1 15፡47 ውስጥ ሲጀምር የኢየሱስን መከራ፤ የሃይሉን እውነተኛ ትርጉም ይሳያል። ማርቆስ 10፡45 ኢየሱስ ለብዙዎች መስዋእት ሊሆን እንደመጣ ለአንባቢ ይነግራል። ከዚህ ትኩረት ያለው ትረካ በተጨማሪ፤ እውነተኛ መከራ ፍጹም ብቸኛነትን ያስከትላል። በማርቆስ ወንጌል ውስጥ እንደ ማርቆስ 15፡34 ያለ ሐይል ያለው ቁጥር የለም። ኢየሱስ ብቻውን በመስቀል ላይ እያለ፤ አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ ብሏል። ኢየሱስ ፍፁም በሆነ መለየት ውስጥ እንደነበር የሚያሳይ ቁጥር ነው። አባቱን እግዚአብሔርን ጨምሮ እንደተተወም ወንጌሉ ይገልፃል። ነገር ግን ታሪኩ እዚህ ላይ አያበቃም።ፍፁም በሆነ ስቃይ ውስጥ፤ ሙሉ በሆነ መለየት ውስጥ፤ እግዚአብሔር የማስታረቅ ፤የመዋጀት አቅዱን፤እና ደህንነት እቅዱን በእሱ ብቸኝነቱን ገልጧል። በማርቆስ 15፡38,39 ውስጥ፤ልክ ኢየሱስ በሞተበት ጊዜ፤ሁለት ቁልፍ ኩነቶች ተከስተዋል። የቤተመቅደስ መጋረጃዎች አኩል ለኩል ከላይ ወደ ታች መቀደዳቸውና፤ በኢየሱስ ፊት ቆሞ የነበረው መቶ አለቃ፤ ስቃዩን የሰማና እንዴት እንደሞተ ያየው ይህ መቶ አለቃ ምስክርነት መስጠቱ ነው። ይህ ሰው በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ ነው አለ(ቁ 39)። አንደኛው ዋነኛው ሁነት (ክስተት) የመሸፈኛው መቀደድ ነበር። የዚህ መሸፈኛ ዋነኛ ዓለማው የነበረው፤ ቅድስተ ቅዱሳኑን ከውጭው ቤተመቅደስ (ከመቅደሱ) መለየት ነበር። የመሸፈኛው መቀደድ በትክክል የሚያሳየው ጉዳይ ምን ነበር? ይወክል የነበረው በክርስቶስ ሞት በኩል፤ ወደ እግዚአብሄር መግባት እንደተቻለ ነው። የዚህ መሸፈኛ መቀደድ በርግጥ አንድ

የሚያመለክተው ጉዳይ፤ ይህንን ሊሆን ይችላል ፤ነገር ግን ሌላም ሃሳብ ሊኖር ይችላል፡፡ እስከ አምስተኛው ክፍለ ዘመን፤የሴርያው ኤፍሬም፤ በቀደመው ቤተክርስትን ውስጥ የነበረ ዋናኛ የክርስትያን ስነ መለኮት ምሁር ፤ የመሸፈኛው መቀደድ እግዚአብሔር ከቤተ መቅደሱ እንደተለየ እና ፤ የእስራኤልንም ፍርድ እየመጣ እንደሆነ የሚያመላክት መሆኑን የራሱን ሃሳብ ይሰጣል፡፡ ይህ በኢየሱስ ሞት የተከወነ የመዋጀትና የደህንነት ዕቅድ የመጀመርያ ምልክት ነው፡፡ ሌላኛው ምልክት የመቶ አለቃው ምስክርነት ነው፡፡ ልክ ኢየሱስ በመስቀል በሞተበት ጊዜ፤ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መረዳቱ ነው፡፡የመስቀሉ መከራ ከመዋጀት ጋር በርግጥም የተገናኘ እንደሆነ፤ የሚያሳየ ሁለት ምልክቶች ናቸው፡፡

መጨረሻው መጀመሪያው ብቻ ነው

ይህ ክፍል የማርቆስን የመጨረሻ ምአራፍ መሰረት አድሮ ይጀምራል፡፡ ይሁንና፤ ታሪኩ እዚህ ላይ ብቻ አያበቃም፤ ለዚህ ነው መጨረሻው መጀመሪው ብቻ ነው የሚል ርዕስ የተሰጠው፡፡ አንዳንድ መፅሃፍ ቅድሶች ቁጥር 8 ላይ አስተማማኝ የነበረ፤ የቀደሞ ዕሁፍ እንደሆነና አንዳንድ ቀደምት ምስክሮች ማርቆስ 16፡9–20 እንደሌላቸው የሚጠቁም ማስታወሻን ይይዛሉ፡፡ ለምን ይህንን ማስታወሻ አዘጋጁ የማርቆስ ወንጌል ፍጻሜ ቁጥር 8 ነው ብለው የራሳቸውን ሃሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ ከማርቆስ ወንጌል ጋር ተያያዥነት ያለው የቀድሞ የታሪካ ዕሁፍ አዋቂዎች፤ አጠቃላይ በታሪኩ ውስጥ ሶስት ፍጻሜዎች እንደነበሩ፤ ያመላክታሉ፡፡

- በመጀመርያ ቀኖናዊ ዕሁፉ ቁጥር 8 ላይ ያበቃል፡፡
- በሁለተኛ ደረጃ፤ የማርቆስ ወንጌል አጭር ፍፃሜ ነበረው፡፡

እናም ይህ አጭር ፍፀሜ፤ በአራተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ የመጣው ተሰንዱ የሚገኘው፤ እንደዚህ ይላል፤ እነርሱም ያዘዛቸውን ሁሉ ለጴጥሮስና ከእርሱ ጋር ላሉት በአጭሩ ተናገሩ፡፡ ከዚህም በኋላ፤ ኢየሱስም ራሱ ለላምና ደህንነት የሆነውን የማይለወጠውን ቅዱስ ወንጌል ከምስራቅ እስከ ምእራብ ድረስ በእጃቸው ላከው፡፡ ሶስተኛውና መጨረሻው ወይም አንዳንዶች ለስሙ መጨረሻ ብለው እንደሚጠሩት፤ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ይህ ቁጥር በግልፅ የማርቆስ ወንጌል ክፍል አንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡ ይህንን ቁጥር በርግጥ የያዘው ክፍል በዚህ ክፍል ዘመን፤ ቀድሞ በተፃፈው ዕሁፍ ውስጥ ይገኛል፡፡ የክፍሉን ዋና ሃሰብ የሚራዳ ማንም ሰው ይህ ቁጥር በዚህ ክፍል ውስጥ መካቱቱ ሊያስደንቀው አይገባም፡፡ እነዚህን ቁጥሮች በተመለከተ፤ እንደ አንዳንዶች አባባል፤ አንድ ሰው የተለየ ነገር ሊመለከት ይችላል፡፡ ነገር ግን ከሌላው አዲስ ኪዳን ክፍል ጋር ሲነፃጸር ምንም የተለየ ጉዳይ እንዳልያዘ ይሳያል፡፡ ይህ ክፍል የተለዩ፤ ጉዳዮችን ለምሳሌ አማኞችን ምልክቶች እንደሚከተሉዋቸው ይሟል፡፡ ይሁንና እነዚህ ሃሳቦች በዮሐንስ 2፡23 , 4፡48 እና ማርቆስ 8፡11,12 ውስጥ በመገኘታቸው አማኞች እነዚህ ሃሳቦች እውነት እንደሆኑ ያውቃሉ፡፡ በተጨማሪም፤ 9-20 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ፤ ሰዎች በልዩ ቋንቋ እንደሚናገሩ ይገልፃል፡፡ ነገር ግን፤ ይህም በቀሩት አዲስ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ ያልተለመዱ ሁነቶች አይደሉም፡፡ ይህ ሃሳብ በሐዋ 2፡4–11 እና 10፡46 ላይም በተጨማሪ ይገኛሉ፡፡ ሌላኛው በዚህ ቁጥር ውስጥ የሚታየው ያለተለመደው ጉዳይ አማኞች እባብን የመያዛቸው ወይንም እንደማይጎዳቸው ይገኝበታል፡፡ ይሁንና፤ ይህም ያልተለመደ ሃሳብ አይደለም፡፡ አንድ ሰው በሉቃ 10፡39 አማኞች እባቦች የመርገጥ ሃይል እንዳላቸው ከሚገልፀው ከዚህ ክፍል ጋር ሊያነፃፅረው ይችላል፡፡ ይኸውም እንደገና በሐዋ 28፡3-6 ጳውሎስ በእባብ በተነደፈ ጊዜ ያለውን ሃሳብ በማቅረብ ከቁጥር 9-20 ያሉትን ሃሳቦች ውድቅ ላለማረግ እንደ ምክንያት ሊጠቀሱት ይችላል፡፡ በርግጥ፤ በዚህ ቦታ ያለው ጉዳይ ያ አይደለም፡፡ የድሮው እና በጣም ተአማኒነት ያለው ዕሁፍ በግልጽ አንዳቆመው ማርቆስም በቁጥር 8 ላይ ቢያቆም ኖሮ፤ እነዚህ ቁጥሮች እንዴት ተብለው ይነበቡ እንደነበር ማርቆስ ሊገልፀው የሞከረው ስነ መለኮታዊ አበርክቶው ፤ ምናልባትም ከ6 እስከ 8 ያሉትን ቁጥሮች በጥንቃቄ በማነበብ ፤ ሊያገኙ ይችሉ ነበር፡፡ማርያምና ሌሎቹም ወደ መቃብሩ መጡ፤ መቃብሩም ባዶ ሆኖ አገኙት፡ ነጭ ልብስ የተጎናፀፈ ጎልማሳ ተቀምጦ አዩ፡ (ቁጥረ 5ን ተመልከት)፡፡

አትደንግጡ የተሰቀለውን የናዝሬቱ ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ፤ተነስቷል በዚህ የለም እነሆ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ በማለት ይነግራቸዋል፡፡ በመቀጠልም ነገር ግን ሄዳችሁ ፤ ለደቀ መዛሙርቱ ለጴጥሮስም ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤ እንደ ነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሩአቸው አላቸው፡፡ መንቀጥቀጥና መደንገጥ ይዞአቸው ነበርና ወጥተው ከመቃብር ሸሹ፤ ይፈሩ ነበርና ለማንም አንዳች አልተናገሩም በማለት ቁጥር 6 ይጀምራል፡፡ የወንጌሉ ታሪክ ማለትም፤ የማርቆስ ወንጌል በነዚህ ቁጥሮች ሊያበቃ ይችል ነበር፡፡ የቀደሙት ዕጉፎች እንደሚያመለክቱት ቁጥር 8 ላይ ሊያበቃ ይችል ነበር፡፡ በርግጥ በይዘት ውስጥ የቀረበው ምን ነበር? ምእራፉ የጌታን ትንሳኤ በግልፅ ሳያስቀምጥ፤ በባዶ መቃብር ባበቃ ነበር፡፡ ይዘቱ የሴቲቱን የመጀመርያ የሆነውን የዚሁ ክስተት እማኝነት ያጠቃልላል፡፡ ይህም በሌሎቹ ወንጌላት መገለፀ እውነት መሆኑን የሚያሳይ ነበር፡፡ ለእነዚህ ሶስት ሴቶች ነበር፤ የጌታ ትንሳኤ መልእክት የተገለጸላቸው ለእነሱ ነው ኢየሱስ በገሊላ እንደሚያገኛቸው መልዕክት አንዲናገሩ የተደረጉት ፡፡ ስለዚህ ቁጥር 8 ላይ ማቆሙ ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው? ማርቆስ ቁጥር 8 ላይ የማቆም ስነመለኮታዊ ሃሳብ ነበረው ማለት ይቻላል? ለማንም ምንም አልተናገሩም ስለፈሩ፡፡ ፀሃፊው ወንጌሉን ቁጥር 8 ላይ ቢያቆም ኖሮ፤ የማርቆስ ወንጌል የምርጫ መልዕክት

ማለትም፤ የፍርሃት ወይም የእምነት በመሆን ያበቃ ነበር፡፡ በወንጌሉ ውስጥ ሁሉ፤ ደቀመዛሙርቱ የማመንና ያለማመን ምርጫ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ የማርቆስ ወንጌል ሁለተኛው ዋና ክፍል ገና አላስተዋላችሁምን በሚለው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ባቀረበው ጥያቄ ተጠናቋል፡፡ (8፡21) ስለዚህ፤ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ሁሉ፤ደቀመዛሙርቱ ምርጫን እንዲያደርጉ ተጠርተው ነበር፡፡ አሁን በዚህ የወንጌሉ መጨረሻ ላይ አንድ ሰው ከፍርሃት የተነሳ በታሪክ ውስጥ የተከወነውን እጅግ አስደናቂ የሆነውን ጉዳይ ያለመዘገብ ወይም አንድ ሰው ይህንን ታሪክ ከሌሎች ታሪኮች ጋር በማቆራኘት፤ ሌሎችን በመከራ ወንጌል ውስጥ ብዙዎችን ደቀመዛሙረት የማድረግ ሂደትን መጀመር የመጨረሻ ምርጫ ነው፡፡

4. የኢየሱስ የምድር ላይ የመጀመርያ አገልግሎት

እጅግ ብዙ ጠቃሚ የሆኑ ጭብጦች በማርቆስ ወንጌል መግቢያ ላይ ተገልጸው ይገኛሉ፡፡

1. ወንጌል (በትርጉም መልካም ዜና)
    - ማርቆስ አንዱና ብቸኛው ወንጌል ነው ‹ወንጌል› ተብሎ ሊጠራ፡ (1፡1 ተመልከት)
    - ይህ ወንጌል እምነትንና (1፡5) ራስን መስጠት (መካድ) ይጠይቃል፤ (10፡29)
2. የእግዚአብሔር ልጅ
    - ይህ ስያሜ እግዚአብሔር ወይም መንፈሳዊ ፍጥረታት ብቻ እንደሚረዳው በታሪኩ ውስጥ ሁሉ እንደ ስያሜ እንደሆነ ታይቷል፡፡ (1፡11, 9፡7,3፡11,5፡7)
    - ሊቀ ካህኑ ኢያሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መጠየቁ፤ (14፡61,62)
    - በርግጥ ይህ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር ብሎ፤ እመስቀሉ ጋር የነበረው መቶ አለቃ ምስክርነት መስጠቱ፤ (15፡39)
3. የእግዚአብሄር መንግስት (1፡14,15)
    - የእግዚአብሔር መንግስት እግዚአብሄር ብቻ ሊሰጥ የሚችለው ፤ ሰዎች ለገነቡት የማይችሉት እንደሆነ፤
    - መንግስቱ የኢየሱስ ትምህርት ማዕከል እንደነበር የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ትኩረት የሚሹ ነጥቦች፡

- የማርቆስ ወንጌል በኢየሱስ መከራና ሞት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡
- ማርቆስ ተከታታይነት ያላቸውን ፈውሶች፤ ክፉ መንፈስ ማስወጣትን፤ እና የተለያዩ ተዓምራትን መዝግቧል፤ ይህም የሚያሳው የሰው ልጆችን ለመዋጀት እግዚአብሔር ያለውን ፍላጎት ያሳያል፡፡
- በኢየሱስ የተነገረው የዘሪው ምሳሌ ሁለት ዋነኛ ጭብጦች እንዳሉት የሚያመላክት ነው፤ ይህም የእግዚአብሔርን ፀጋ እና ከእግዚአብሔር የሆነ መገለጥ፡፡
- ማርቆስ ‹ወንጌል› የሚለው ቃል የተፃፈበት ብቸኛው ወንጌል ነው፡፡

ማገናዘቢያ

ይህ ጥናት የማርቆስ ወንጌልን በጥልቀት ስታጠኑ የሚነሱትን ዋና ዋና ነጥቦችን አስተዋውቋል፡፡ ስለሆነም፤ ከዚህ ክፍል መጨረሻ በኋላ፤ ተማሪዎች

- የመፅሃፉን ፀሃፊ የሚለዩበትን መንገድ ያውቃሉ፤
- ጊዜውን፣ ቦታውን፣ ሁኔታውንና የማርቆስ ወንጌል ላይ ያሉትን ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ያውቃሉ፤
- የማርቆስ ወንጌልን ትርጓሜና ስነ መለኮታዊ ጭብጡን ይረዳሉ፤

መመዘኛ መልመጃዎች

መመሪያ አንድ: የሚከተሉትን አርፍተ ነገር በጥንቃቄ በማንበብ ፤ጥያቄዎችን መልስ፡፡

1. የማርቆስ ወንጌል በሚከተሉት ሃሳቦች ተዋቅሮ ሊከፋፈል ይችላል፡ መግቢያ፤ የወንጌሉ ሃይል ፤ የመከራውን ሃይልና ተጨማሪ ሃሳቦች፡፡
2. አራተኛው የማርቆስ ወንጌል ክፍል፤ መጀመርያው መጨረሻ ብቻ ነው፤ ጥልቅ ትረካን ይይዛል፡፡
3. ማርቆስ ረጅሙ ወንጌል ነው፡፡
4. የመፅሃፍ ቅዱስ አዋቂዎች የማርቆስ ወንጌል ከማትዮስ ወንጌል ያነሰ ይሁዲዎችን የያዘ ነው ብለው ይናገራሉ፡፡
5. ---------- ጭብጥ ስለ ወንጌል ራስን ለእግዚአብሔር አገልግሎት አሳልፎ እንደ መስጠት እንደሆነ የሚገልፅ ለሆን ይችላል፡፡
6. ---------- የማርቆስ ወንጌል ጥልቅ ትረካን፤ ረዘም ባለ መግቢያ የያዘ ነው ብሎ ይናገራል፡፡

7. የወንጌሉን ሃይል ሊናገር የቻለው የማርቆስ ክፍል የትኛው ነው፡፡
8. የመከራውን ሃይል ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን የማረከበት ቦታን፤ ሊናገር የቻለው የማርቆስ ክፍል የትኛው ነው፡፡
9. የመጨረሻው የማርቆስ ወንጌል ክፍል ቀጣይነት ያለው ነው፡ ምዕራፍ 16 ምን ተብሎ ይጠራል፡፡
10. ---------- የማርቆስ ወንጌል ርዕስ ነው፡፡
11. ---------- የማርቆስ ወንጌል ድራማዊ (አስደናቂ) ርዕስ ነው፡፡
12. ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን አሳ አጥማጆች አንዲሆኑ ጠርቷቸዋል፡፡
13. ሶስቱ የኢየሱስን ሞት አመላካች የሆኑት ሃሳቦች የትኞቹ ነበሩ፡፡

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>ጭብጦቹን በስፋት ማየት</u>

<u>መግቢያ</u>

ይህ የሞጁሉ ክፍል በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙትን ዋነኛ እና ጠቃሚ የሆኑትን ስነመለኮታዊ ጭብጥ ይመረምራል፡፡ አነዚህን ስነመለኮታዊ ጭብጥ ከማግኘት በተጨማሪ፤ ተማሪዎች እነዚህን ስነ-መለኮታዊ ጭብጦች እንዴት መተግበር ወይም ስነስብከታዊ እንድምታቸውን ምን እንደሆነ ያያሉ፡፡

ዓላማው

ይህንን ክፍል በብቃት ካጠናቀቁ፤ ተማሪዎች

- በማርቆስ ወንጌል ውሰጥ ያለውን ስነመለኮታዊ ጭብጥ ያውቃሉ፤
- በማርቆስ ወንጌል ውስጥ በጥልቀት ትኩረት የተሰጠባቸውን ስነ-መለኮታዊ አከራካሪ ጉዳዮች ይረዳ፤
- በደቀመዛሙርቱ የአሁን ህይወት ውስጥ ስነ-መለኮታዊ ጭብጡ ያለውን ጠቀሜታ ይለያሉ፤

ውድ ተማሪዎች በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙትን ዋና ጭብጦች ምን እነደሚሆን ታስባላችሁ?በዚህ ወንጌል ውስጥ ካሉት ጭብጦች ጋር በተገናኘ ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣውን ማንኛውም ሃሳብ ፃፉ፡፡

ትኩረት የሚሹ ነጥቦች፡

- ኢየሱስ እውነተኛ መሲህ ነው፡፡
- የኢየሱስ ማንነት ከፍፃሜው የማይለይ ነው፡፡

ሀ. ክብርና መከራ

ውድ ተማሪዎች እነዚህን ሁለት ሃሳቦች ለመረዳት ጥቂት ጊዜ ውሰዱ፤ በክብርና በመከራ መካከል ስለአለው ግንኙነት ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣውን ማንኛውንም ሃሳብ ጻፉ፡፡

_____

_____

አንደኛው የማርቆስ ወንጌል ድንቅ መለያ ባህሪው፤ የኢየሱስ በሃይል የተሞሉ ተግባራትን ከምዕራፍ 1-8 በዋናነት የሚገኙትን ያከናወነ ሲሆን፤በተጨማሪም የኢየሱስን መከራና ሞት ከምዕራፍ 9-16 በዋናነት የሚገኙትን ሃሳቦች በጋራ ተራ በተራ ማስኬዱ ነው፡፡ ዋናው ጥያቄ ግን ለምን የሚለው ነው፡፡ ሊሆን የሚችለው፤ ማርቆስ ምክንያቱ ይህ ሊሆን ይችላል ፤ለኢየሱስ መንግስት መምጣት፤ የመከራና የስቃይ እውቀት (ገጠመኝ) የሃይሉ ዕውቀት፤ ለማሳየት ይሞክራል፡፡

የወንጌሉ ሁለቱ አጋማሽ ሁለቱን የኢያሱስ ማንነት ማዕከላዊ መለያ ባህሪያት ትኩረት ያደረገበት ነው፤ ነገር ግን በተለያየ ውጥረት ውስጥ አንዱ በአንዱ ላይ ቆሟል፡፡ እንደዚህ ያለ መጠቅ ያለ ሃይንና ስልጣን ፤

በዚያው ጊዜ ጥልቅ እውቀት ያለው ያው ሰው (ኢየሱስ)፤ በእንደዚህ ያለ ውርደት ስቃይ ውስጥ ሆኗል ብሎ መሳል ይቻላል።

ለ. የመሲህነቱ ሚስጥር

የማርቆስ ወንጌልን ስናጠና፤ አንዱ የውይይቱ ቁልፍ ነጥብ ሊሆን የሚችለው፤ከሌሎቹ ወንጌላት ይልቅ፤ ማርቆስ የተለየ ገዘፍ ያለ አበርክቶውን፤ የኢየሱስ መሲሃዊ ማንነቱን ከማጉላት ጋር የተያያዘ ነበር። ስለሆነም፤ በውጭ ላሉት የመንግስቱን ሚስጥር እንዲያውቁ አልተሰጣቸውም፤(ማር 4፡10-12)፤ ርኩስ መናፍስትም፤ ኢየሱስ ማን እንደሆነ መለኮታዊ በሆነተፈጥሮአቸው ተረድተውት ስለነበር፤ ማንነቱን ሊያውጁ ሲሞክሩ ኢየሱስ ገስጾአቸው ነበር። ማር 1፡25,34 3፡12)፤ ኢየሱስ ተዓምራት ያደረገላቸው ሰዎች ፤ ኢየሱስ ምን እንዳደረገላቸው እንዳይገልጹ የፈቀደና ማን እንደሆነ ግን እንዳይገልፀ ከልክሎዋቸው ነበር። (1፡44, 5፡18,19,43) ጴጥሮስና ደቀመዛሙርቱ ፤ የማቴዎስ ወንጌል፤ ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ማንነት እንደ ደቀመዛሙርትነቱ ምስክርነት ሲሰጥ ፤ ጴጥሮስና ደቀመዛሙርቱ ያለምንም ምስጋና ዝም ብለው ነበር።ሬድ የተባለው ጸሃፊ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ያሉትን እነዚህ መለያ ባህረያቱን ለመጀመርያ ጊዜ ለውይይት ክፍት ያደረገ ሲሆን፤ ኢየሱስ መለኮታዊ መሲህ እንደሆነ ራሱ ኢየሱስ ሳይገልፅ፤ ማርቆስ በራሱ መንገድ የራሱን አምነት ያረጋገጠበት እንደሆነ ይሞግታል።ነገር ግን፤ ሌላ ማብራሪያ መፈልግ ደግሞ ተገቢ ነው። አንድ ሰው ከላይ የተገለጸውን ውጥረት ከኢየሱስ ክብርና መከራ፤ ጋር በቅርበት ያቆራኝዋል። ኢየሱስ ማንነቱን፤ እንደ መለኮታዊ መሲህነቱን፤ ከመከራው በተለየ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ እንዳይገባ ግፊት ያደርግ ነበር።ማንነቱ ከፍፃሜው የማይለይ ነው። በዚህ ምክንያት፤ኢየሱስ እንደ መሲህ የራሱ ማንነት ላመግለፅ ጠንቃቃ የነበረበት ምክንያት፤ እንዳሰበው ሌሎች ላይረዱት ስለሚችሉ እና አገልግሎቱን ሊያደናቅፍበት የሚችል አደጋ ሊገጥመው ስለሚችል ነበር። ኢየሱስ ዝም እንዲሉ ሲያዛቸው አልተቀበሉም ነበር ፤ ይህ በርግጥ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚታየው እውነት ነው። አንባቢው ከማር 1፡11 በመነሳት ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ያውቃል። ነገር ግን የዚህ መጠሪያ እውነተኛ ጠቀሜታው፤ የመቶ አለቃው በመስቀሉ ግሬጌ ቆሞ፤ በርግጥ ይህ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር ብሎ እስከአወጀበት ጊዜ ድረስ ግልጽ አልሆነም ነበር። ስለዚህ፤ ማንነቱ እውን የሆነው፤ ፍፃሜው በታየበት ጊዜ ብቻ ነው። ሁለቱ ባህርያት ፤ ክብሩና መከራው የግድ ተያይዘው መጓዝ አለባቸው። ኢየሱስ ስለራሱ መሲህነት፤ ጴጥሮስ ከሰጠው ምስክርነት ጋር ተያያዥነት ካላቸው፤ ወደፊት ከሚሆኑት መከራና ሞት ጋር ማዕከላዊ ጠቀሜታ ስላለው ጭብጥ ወዲያውኑ ምላሽ ይሰጣል። እናም ጴጥሮስ ይህንን ለመቀበል አለመፈለጉን በገለፀ ጊዜ፤ ፀጥ ማለት እንዳለበት ትእዛዝ መሰጠቱ አስፈላጊ ነበር። በተመሳሳይም፤ በተራራው ላይ መቀየሩ፤ የኢየሱስን ክብር ድራማዊ በሆነ መልኩ የሚያሳይ የቅድመ እይታ ነበር። ነገር ግን ይህ ክብር ኢየሱስ ሞቶ እስኪነሳ ድረስ በሙላት ግንዛቤ ሊያገኝ አልቻለም ነበር (9፡9)። ደቀ መዛሙርቱም የመሲሁ መከራ ሃሳቡ ከብዶባቸው እንደነበር፤እና ከሞት መነሳት ምን ማለት እንደሆነ እንኳን አልተረዱም ነበር። (9፡10) ይህንኑ ሃሳብ፤ ከኤልያስ ጋር በማያያዝ ይወያዩ ነበር። በ ዳንኤል 12 እና ሕዝቅኤል 37 ዕሁፍ ውስጥ የተገለፀውን በማሰብ፤ የሰው ልጅ ከሞት መነሳት ፤ የእስራኤልን ዳግም መመለስ እንደሆነ ግምት ውስጥ ያስገቡ ይመስላል። እስራኤል መመለስ ከትንሳኤው ጋር የሚተሳሰር ነው ከተባለ፤ የኢየሩሳሌም መመለስ እውን የሚሆነው ከትንሳኤ በፊት ከሆነ፤ ከኤልያስ መምጣት ጋር እንዴት ጸሃፊው ይህንን በማለት ሊያይዘው ቻለ። ነገር ግን ሁለቱን የማርቆስ አጋማሽ ክፍሎች እውነት በመገንዘብ፤ ስለኢየሱስ ማንነት በሚገባ መረዳት ይቻላል። ሁለቱን የማርቆስ ወንጌልን በማጣመር መመልከት፤ የኢየሱስን ማንነት ለማወቅ ብቻ የሚረዳ አይደለም። በሌላ በኩል፤ በወንጌሉ የመጀመርያ አጋማሽ ውስጥ የተነገረው ሃይሉና ስልጣኑ፤ ለሁለተኛው የወንጌሉ ክፍል ፍቺ እንደሚሰጥ መረዳት የግድ ነው። በሌላ አባባል፤ የኢየሱስ እና የመንግስቱ ሃይል ፤ የሃይሉ ክህደት ሃይል ነው። ይህም እንደማረጋገጫ በመጀመርያው የወንጌሉ አጋማሽ ክፍል ውስጥ፤ በኢየሱስ የመጣው መንግስት ፤ባልተጠበቀ መንገድ እንደመጣ ምልክት ነው። ለምሳሌ፤ የሚበቅለው ዘር ሃይል እና አስቀድሞ የነበረው ኢየሱስን ተቃውሞ መመልከት ይቻላል።

ሐ. ደቀ መዛሙርትነት

አሁን እኛ ባለንበት በዚህ ዘመን፤ የክርስቶስ ደቀመዛሙርትን ለማብዛት መሰረታዊ የሆነው ተግዳሮት ምንድን ናችው? ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣውን ማንኛውንም ሃሳብ ጻፉ።

_____

_____

_____

1. **የማርቆስ የደቀመዝሙርነት ገለፃ**

በኢየሱስ ክብርና መከራ መካከል ያለው ውጥረት ለኢየሱስ የተለየ ነው። ሃይል ያለው ስራው ። ስልጣኑም በተለየ ሁኔታ የመሲህነት ማንነት ክፍሉ እንደሆነ ግልጽ ነው። ለምሳሌ ሰንበትን ከመጠበቅ ጋር ተያያዥነት ካለው ከሙሴ ህግ በላይ አንኳን ስልጣን እንዳለው ይናገራል(2፡28)። ማር 14፡24 እና 10፡45 በተጨማሪ መከራው የተለየ እንደሆነ ይገልጻሉ። የማርቆስ ደቀመዛሙርትንት ግንዛቤ እነዚህ ሁለቱ ውጥረቶች ማለትም ክብር እና መከራ እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆኑ በግልጽ ያስቀምጣል። በማር 10፡45 ውስጥ የክብር የመናገርንና የመሪነት ዋና ሃሳብን በመያዝ ያብራራል። ራስን ለእግዚአብሔር የማቅረብ ጉዳዩን በማንሳት፤ ኢየሱስ ራሱን በማቅረብ፤ እንዴት እንደሚሰራ ደቀመዛሙርቱ እንዲረዱ እንደ ያደርጋል። ሌሎችን የሚያገለግልበት ክፍል መከራን ያጠቃልላል። በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ደቀ መዛሙርቱ፤ የእግዚአብሔርንም የሰውንም ነገር የሚያስቡ እንደሆነ ቀርበዋል። ደቀመዛሙርቱ የማያስተውሉ ነገር ግን ታማኞች እንደሆኑ ተገልጸዋል። ማስተዋል ያለመቻላቸው፤ የሰውን ነገር ብቻ እንዲያስቡና ታማኝነታቸው እንዳይጠፋ በእርግጥ ምክንያት ሆኗል። የደቀ መዛሙርቱ እንዴት እንደተነሱ፤ በዚህ ቦታ በሚሰብ መንገድ ተገልፆአል። ለኢየሱስ ሙሉ ታማኝንትን፤ ሙሉ በሙሉ ራስን መስጠትና ከኢየሱስ ጋር ለመሆን የወሰኑና፤ እስራኤል ውስጥ የነበረውን ተልዕኮ ከኢየሱስ ጋር ለመፈፀም ለተባበሩት ተጠርተዋል። የእግዚአብሔርን የመጨረሻው መንግስት ሚስጥር እና ለአገልግሎት መሾማቸውን ታይቷል። ነገር ግን፤በሁለተኛው አጋማሽ መካከለኛ የወንጌሉ ክፍል ውስጥ ያለው ገለፃ፤ ደቀመዛሙርቱን እንደማያስተውሉ ሆነው በማሳየት እጅግ አሉታዊ በሆነ መልኩ ያስቀምጣቸዋል። ብዙዎችን ሁለት ጊዜ በመገበበት ተዓምራትና በሶስቱ ጀልባዎች ቦታ፤ የኢየሱስን ስልጣን ባህሪና ለእነርሱ የተሰጣቸውን ስልጣን መረዳት አለመቻላቸው እንደ ዋነኛ ማስረጃ ሊያዝ ይችላል።

ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ያለው ግጭት ።በማርቆስ ወንጌል መጨረሻ ከፍ ያለ ሆኗል (8፡27–16፡8) የኢየሱስን አገልግሎት፤ ከመሰቀሉና ከትንሳኤው ጋር በማያያዝ ይወያዩበት ነበር፡ ይሁንና የመስቀሉንና የትንሳኤውን ሃሳብ በተደጋጋሚ አይረዱትም ነበር። በያንዳንዱ ጊዜ የኢየሱስን የአገልግሎቱን ባህሪ ።መከራን እንደሚቀበል አገልጋይ፤ እና በጣም አስፈላጊ የደቀ መዛሙረትንትን ባህሪ መሆን ስላለባቸው ጉዳዮች መመሪያ ተሰትቷቸዋል። ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ ያሉበትን ሁኔታ መከራውንና ሞቱን ከማሰብ ይልቅ፤ስለ ታላቅንት፤ ስለ ሃብት ። ስለ ሃይል ። የወደፊቱን ስለማሰብና መከራ የሌለበት ህይወት ስለመኖር በማሰብ ቀጥለው ነበር። በመጨረሻም፤ ይህንን ሃሳብ ለመረዳት አለመቻል ዝግጁነትን ያሳጣል።ከዚህ ሁሉ ጉዳይ ውስጥ የሚታየው፤ አንድ ሰው እንዴት ወደ እምነት እንደሚመጣ፤ የደቀመዛሙርቱ ገለፃ እንደ ሞዴል ሊወሰደ የማይችል ነው። ነገር ግን ለኢየሱስ የደቀ መዛሙርትንት ትርጉም ማረጋገጫ፤ ከመከራ የተለየ ግንዛቤ ሊሰጠው አይችልም። በሌላ አባባል፡ የደቀ መዛሙርቱ የማርቆስ አገላለጽ (በዚህ አኳኋን ውስጥ ስለ ደቀመዝሙርነት ያለው ትምህርት የሚሄደው)፤ የኢየሱስን ባህሪ ከሚገምቱት በላይ ሃይል እና ስልጣናዊ እንደሆነ ለመረዳት ካለመቸል ጋር የመጣ አለማስተዋል እንደሆነ ያሳያል፤ ምክንያቱም ከመከራው ሂደት ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ነው። ነገር ግን የደቀ መዛሙርቱ አለመረዳት፤ መከራው የመከሰት እድል እንዳለው ያሳያል። በተለይ በጭፍጨፋው ገሃድ ውስጥ ፍፁም ተቀባይነት የለውም። ይቅር የሚባል ነው።

2. የማርቆስ ትምህርት ስለ ደቀመዛሙርትነት

እንደተገለጸው፤ ስለ ደቀመዛሙርቱ በግልጽ የተጻፈው ትምህርት የሚገኘው በሁለተኛው የወንጌሉ አጋማሽ ክፍል ሲሆን፤ የተቀናጀው በሶስቱ ወደ ፊት ስለሚሆኑት ክንውኖች በማሳየት ነው። በተጨማሪ፤ እነዚህ ትምህርቶች፤ ሁሉ ቦታን (ስልጣንን) በግልፅ ከመተው ጋር በተወሰነ መልኩ ይገናኛል። ይህ ጭብጥ ስለ ወደፊቱ ከሚያሳዩ ከሶስቱ ጥልቅ ጉዳዮች እና የአንድ ነገር ጠቀሜታ ላይ ትኩረት ከሚሰጥ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን፤ ነገር ግን መሪ የመሆንና መሪዎችን ማሳደግ ያለውን እውነት፤ ቦታና ትኩረት ያልሰጠ መሆኑን፤ እንደ ማስረጃ ሊጠቀስ ይችላል።

እንደ ማቴዎስ አገላለፅ የኢየሱስ አገልግሎት ማዕከል ያደረገው፤ የንጉስ አገዛዝና የእግዚአብሔርን መንግስት በማወጅ ነበር። ኢየሱስ የእግዚአብሔር መንግስት የሚመጣበትን ጊዜ ሲገልጽ፤ እያንዳንዱ ሰው እንደሚያውቀው፤ የዓለም አገዛዝን በመሻር፤ እግዚአብሔርን ዓለምን የሚያስተደድርበት መንግስት ሲመሰረት እንደሆነ ይጠቅሳል። ይሁንና ኢየሱስና በጊዜው የነበሩት በዚህ መሰረታዊ እውነት የሚስማሙ ከሆነ፤ ብዙ ያልተነገረ የተለየ ጉዳይ እንዳለ ግልጽ ነበር። ካሉት ልዩነቶች አንዱ፤ አስቀድሞ የሚመጣው መንግስት በመጨረሻ የክብሩ ሙላት እንደሆነ ይታመናል። ይህም መንግስቱ በዓለም ውስጥ መኖሩ ነበር። ይህ አስገራሚና አስደናቂ አዲስ ሃሳብ ነበር።አይሁዶች መንግስቱ እንደ አንድ ነገር በአንድ ጊዜ የሚመጣ፤ ከዚያም የአስራኤል ጠላቶች የሚጠፉና ዕድቅ የሚመሰረትበት ይሆናል ብለው ያምኑ ነበር። ። የእግዚአብሔር መንግስት ጉዳይ ለኢየሱስ ግን እንደዚህ አይደለም። ስለ መንግስቱ ያለው ይህ ፈጣን የሆነ አዲስ የአስተሳሰብ መንገድ፤ አንዱ ውጤት የሆነው፤ የኢየሱስ ያልተጠበቀ መንግስት፤ ባልተጠበቀ መንገድ መምጣቱ ነበር። ግምቱ የነበረው መንግስቱ በክብርና ጠንካራ በሆነ ሃይል እንደሚመጣ ነው። ከዚህ በተቃራኒ፤ መንግስቱ እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ወይም በምድር ላይ እንደሚዘራ አንዲት ዘር መጥቷል፤ እንዴት እንደሆነ ሳይታወቅ ዘሩ በቅሎ በሚያድግበት እና ምድርን በሚሞላበት መንገድ መጣ። በማርቆስ 4፡26–32፤ ይህ አይነቱ መንግስት ጠንካራ በሆነ ሃይል እንደማይመጣ አሳይቷል። ይልቁንም፤ የማርቆስ

ወንጌል በተለየ መንገድ ግልፅ እንደሚያደርገው፤ በዚህ መንግስት መምጣት ውስጥ ወሳኝ የሆነው ጊዜ፤ የመሲሁ መሞት የሚያመጣው ለውጥ ነው። ይህ የሚለየው መንግስት፤ በመሲሁ በተለየ መንገድ የሚስተናገድ ነው። መሲሁ ባህሪው ያልተጠበቀ እንደሆነ፤ እንዲሁ የሚመጣው መንግስት ያልተጠበቀ እንደሆነ ይገልፃል። ይህ የማርቆስ ወንጌልን ለየት የሚያደርገው ወሳኝ ጉዳይ፤ ኢየሱስ በክፋትና በበሽታ ላይ ሁሉ ሃይል እንዳለው የሚያብራራ እንደሆነ እናያለን። ከምዕራፍ 1-8 ይህ ሃይል ግልፅ በሆነ መልኩ፤ በዓለም እንደነበረው እንደ ሮማውያን ሃይል ፤ ከሃይሉ ክህደት አኳያ ከምዕራፍ 9-16 ውስጥ፤አልታየም። ማርቆስ የሚነግረን የኢየሱስ ታሪክ፤ ሃይልን የተቆጣጠረ ነገር ግን በፈቃዱ ሃይሉን አሳልፎ የሰጠን(ያስገዛን) የኢየሱስ ታሪክን ነው። በሚመጣው መንግስት ውስጥ፤ ወሳኝ የሆነው ጊዜ የኢየሱስ ሞት ከሆነ፤ የመንግስቱ ሃይል፤ የሃይሉ ክህደት እንግዳ በሆነ መልኩ የቀረበ ሃይል ነው። ይህ አመለካከት ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ያወጣላቸው፤ የህይወት መንገድ መመርያ ለሆነው ጉዳይ አስደናቂ የሆነ እንድምታ አለው። ኢየሱስ የኖረበትን የህይወት መንገድን ለመቅሰም፤ ለደቀ መዛሙርቱ፤ የመጀመርው እንቅፋት ፤ቦታን የመተው አስቸጋሪነትን፤ ኢየሱስ ለተከታዮቹ ያስረዳው እና አንድን ደቀ መዝሙር ወደ ኢየሱስ እንዳይመጣ አደጋች የሚያደርገው፤ ህይወቱ በኢየሱስ መስቀል የተቀረፀ መሆን ስላለበት እንደሆነ ማርቆስ በታሪኩ ነግሮናል። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን፤ ተከታዮቹ አንዲሆኑ የመረጠበትን ሁኔታ ፤ደቀ መዛሙርቱ በመንግስቱ ውስጥ መሪ እንደሚሆኑ፤ ቦታና ስልጣን ያላቸው እንደሚሆነ እንደ መገለጫ አድርገው ነበር ደቀመዛሙርቱ ደጋግመው የተረዱት። የኢየሱስ የመንግስቱን ሃይል የተረዱት ፤ፍፁም በተሳሳተ መንገድ ነው በማለት ደጋግሞ አሳይቷቸዋል። ይህን በማድረግ፤ የመንግስቱ ሃይል፤ በዓለም ውስጥ ከተቀመጠው መንግስት፤ የተለየ እንደሆነና በመጨረሻም ሁሉን ነገር ወደ ለውጥ የሚያመጣው የመስቀሉ ሃይል እንደሆነ ነግሯቸዋል። የመንግስቱ ሃይል የክህደት ሃይሉ እንግዳ ሃይል ነው። ይህ መመሪያ፤ ኢየሱስ ስለራሱ ማንነት እና ተልዕኮ የራሱን መረዳት ብቻ ሳይሆን፤ ነገር ግን ለደቀ መዛሙርቱ ወደፊት ያኖረላቸው የህይወት መንገድ እንደሆነ በግልፅ ያሳያል። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ያለውን ሃሳብ ማዕከል ካደረገው ጋር ይሄዳል። ለጥቂቶች ብቻ እንደ አንድ መመሪያ፤ መሪዎችን ማሳደግ በሚለው ሃሳብ ላይ ትኩረት ለመስጠት አልፎ አልፎ ያሳያል። የሰብሉን ዋና የሚለውን አባባል ይመርጣል። ምንም ነገር ከእውነቱ የራቀ ሊሆን አይችልም። ደቀመዛሙርቱ የኢየሱስ ምረጦችም ቢሆኑም፤ እንደታሰበው ብሩሆች አይደሉም። ቁጥራቸው አስራ ሁለት መሆኑ፤ ምሳሌያዊ ጠቀሜታ ነበረው። የኢየሱስ ደቀመዛሙር ቁጥር፤ የእስራኤልን መመለስን የሚወክሉ አስራ ሁለቱን ማህበረሰብበመምረጥ እንደሆነ ሃሰቡ ያሳያል። እውነታው ኢየሱስ እንደ መሪ የነሱ ሚና ምን እንደሆነ ያልገለፀላቸው ወይም ስለመሪነት እንኳን ያስተማረው ጉደይ እንዳልነበረ ይታያል። በሁሉም ወንጌሎች ውስጥ፤ ኢየሱስ አንድ ጊዜ እንኳን መሪ ወይንም መሪነት የሚለውን ቃል ለደቀመዛሙርቱ አልገለፀም። ደቀመዛሙርቱ እንዲሆኑት ወይም እንዲያደርጉት የሚፈልገውን፤ ሲናገር መሪ ወይም መሪነት የሚለውን ሃሳብ በፍፁም ተጠቅሞት አያውቅም። በርግጥ፤ ኢየሱስ መሪ የሚለውን ቃል የተጠቀመበት ብቸኛው ጊዜ፤ ለኢየሱስ ለራሱ እና ለተልዕኮው ጥላቻ ያላቸውን ባለስልጣናት ለመጥቀስ ሲፈልግ ብቻ ነው። ምናልባት፤ ኢየሱስ ቃሉን ያልተጠቀመበት ምክንያት፤ በማንኛውም ሰው አእምሮ ውስጥ፤ ደቀ መዛሙርቱን ጨምሮ፤ ቃሉ የተሸከመው ትርጉም፤ የአይሁዶችና የሮማውያን ባለስልጣናት ራሳቸውን፤ ከሚያቀርቡበት መንገድ ጋር በቅርበት የተቆራኘ ስለሆነ ነበር።. ከዚህ ውስጥ ብቸኛው መደምደሚያ ሊሆን የሚችለው፤ ኢየሱስ መሪዎችን የማሰልጠን ሃሳብ እንዳልነበረው ነበር፤ እንደ ታሪክ አገላለፅ ከሆነ፤ በቀደመው ቤተክርስትያን የነበሩት ብዙሃኑ ወይም አብላጫው ቅርበት ያላቸው ተከታዮቹ፤ ይህንን በፍጹም አላወቁትም ነበር። በዓለም ውስጥ ለለውጥ የሚያመጣው፤ ጠንካራው ሃይል መሪነት እንደሆነ ተነግሮናል። ነገር ግን፤ የመንግስቱ ሃይል፤ በዓለም ያለ በጣም ጠንካራ ሃይል ከሆነ፤ በዓለም ያለው በጣም ጠንካራ ሃይል የሃይል ክደት ሃይል ነው ማለት ነው። ያም የመንግስቱ ሃይል ነው። ሁልጊዜ እና የትም ቦታ፤በአፋፍ ላይ ያለ እርባና የሌለው የሚንገዳገዳ ሃይል ነው። ሁልጊዜና የትም ቦታ ከጥቂትዋ ዘር፤ ከጥቂት እርሾ ፤እርባና በሌለው ቦታ ካልተሰጠው ጉዳይ እንኳን የበለጠ ምንም የለም፤ በአጭሩ እርባና በሌለው ጉዳይ ውስጥ ይህን የለውጥ ሃይል ይሏል። የኢየሱስ አገልግሎት ለደቀመዛሙርቱ የመሪነት ስልጠና መስጠት አልነበረም። ያሰለጠናቸው አገልጋይ እንዲሆኑ ነው። በርግጥ፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ራሳቸውን እንደ መሪ፤ እንዲያስቡ በግልፅ አልፈለገም ነበር። ይልቁንም፤ አገልግሎቱን ሁሉ ያሳለፈው፤ ደቀመዛሙርቱ ራሳቸውን እንደ ደቀመዝሙር እንዲያስቡና ደቀመዝሙርነት ምን ማለት እንደሆነ እንዲረዱ፤ ይህን እንዲረዱ ለመርዳት ነበር። ስለራሳቸው መሪነት ባሰቡበት ጊዜ ሁሉ፤ ኢየሱስ ይገስጸቸው ነበር። መሪዎች እንዲሆኑ አይፈልግም ነበር፤ ተከታዮች አንዲሆኑ እንጂ። እንደዚህ አይነቱ አቅጣጫን የሚያሳይ ሃሳብ ለቀደመው ቤተክርስትያን ሊሰጥ የፈለገው ፤የመሪነት አቅጣጫን ሳይሆን የተከታይነትን ሃሳብ ነበረ። የሰጣቸው አቅጣጫ የተከታይነት ብቻ እንደሆነ የሚሳይ ነበር። ደቀ መዝሙር በቀላሉ የክርስቶስን መንገድ የሚማርና የሚከተል ነው። ነገር ግን ይህ መንገድ ምንድን ነው? ማዕከላዊ መገለጫው ምንድን ነው? መንገዱን ካመላከቱን ህይወታችን ምን ሊመስል ይገባል? በርግጥ ማርቆስ በሁለተኛው የወንጌል ክፍል ውስጥ ከኢየሱስ ትምህርት ሊያስጨብጠን የፈለገው ይህ ነው፤ ትኩረቱን በዋነኛነት ችላ በተባለ ፤ኢየሱስ ባስተማረው የህይወት መንገድ አንድ ጉዳይ ላይ አድጓል። ነገር ግን ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ እንደመሪ ማሰብ ሲጀምሩ የሚያተኩረበት ጉዳይ ግልጽ ነበር። በቀላሉ ይረሳል ብሎ ባሰብ የተለየ ነው ምክንያቱም ማዕከላዊ ስለሆነ ነው። ሆኖም፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ምን አይነት የህይወት መንገድ ሊኖራቸው እንደሚገባ እንደሚፈልግ፤ በተደጋጋሚ በተናገረበት ጊዜ፤ ወደ ቦታ ጭብጥ ይመለስ

ነበር፡፡ ለደቀመዛሙርቱ የተገባ የህይወት መመሪያ በሚያስቀምጥላቸው ጊዜ፤ ራሱን ለሌሎች አሳልፎ ለመስጠት ቦታውን እንደተወ ጠቅሷል፡፡ ለማድነቅ አስቸጋሪ የሚያደርገው አንዱ ጉዳይ ይህ ጭብጥ ምን ያህል ዘልቆ እንደሚገባ ፤እንደሚጠቅም እና አንደሚገዳደር፤ በኢየሱስ ትምህርት ውስጥ፤ ይህ የቦታ ጉዳይ በጥልቀት መገለፀ፤ በራሳችን ባህል ውስጥ በተደጋጋሚ የምናያቸው እንኳን ግንዛቤው አለመኖሩን ያመላክታል፡፡ በብልሃት ከኛ በላይ ስልጣን እንደያዙ የምናስባቸውን፤ በብልሃት ክብርና አክብሮት ልንሰጠቸው ይገባል፡፡ ከኛ በታች እንደሆኑ በምናስባቸውም ሰዎች፤ በተመሳሳይ መልኩ እንክብካቤ እንዲደርግ በብልሃት እንጠብቃለን፡፡ እንደተገለፀውም፤ ይህ ቦታና ክብር ጎን ለጎን እንደሚሄዱ እንመለከታለን፡፡ መጽሃፍ ቅዱስ ሌሎችን ማክበር እንዳለብን ያስተምረናል፡፡ ነገር ግን በምን መልክ?.ሌሎችን ማክበር አስፈላጊ ከመሆን ጋር የተያያዙ የአንድ ባህል እሴቶችን ፤ መፅሃፍ ቅዱስ ይሁንታ ከሰጣቸውና ካረጋገጠላቸው፤ የቦታ ጠቀሜታ ጋር ሌሎች የባህል ልማዶችን፤ ለማያያዝ ስንሞክር ችግር ይገጥመናል፡፡ ከዚህም በመነሳት የመጽሃፍ ቅዱስን እይታ ያለመረዳት፤ ጥልቅ ችግር እንዳለበት እንመለከታለን፡፡ ይህንን በማርቆስ ወንጌል ላይ በግልፅ እናያለን፤ ምክንያቱም ማርቆስ የወንጌሉን ክፍል ያዋቀረበት መንገድ ነው፤ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ስለ ደቃመዛሙርቱ የተገለፀው አብዛኛው ትምህርት በሁለተኛው አጋማሽ ውስጥ ይገኛል፡፡ እንዳስተዋልነው፤ በዚህ ትምህርት ውስጥ አንዱ ደማቅ የሆነው ነገር፤ ኢየሱስ ወደ ሞት መቅረቡን በሶስት የተለያየ ክቅድመ ትንበያ አካባቢ መዋቀሩ ነው፡፡ በያንዳንዱ ጉዳይ ውስጥ፤የኢየሱስ ደቀመዘሙርት ወደፊት ሊመጣ የሚችለው ነገር ፤ምን እንደሚሆን መረዳት አልቻሉም፡፡ እናም በእያንዳንዱ ጉዳይ ውስጥ፤ ማርቆስ ኢየሱስ አስቀድሞ ሊሆን ያለውን የመናገሩ ጠቀሜታ፤ ደቀመዛሙርቱ ያለተረዱበት ዋነኛ ምክንያት ኢያሱስ የተለየ መሲህ እንዳልሆነ፤ ከበፊቱ ማንነቱ ጋር በማነፃፀራቸው እንደሆነ አመላክቷል፡፡. በሌላ በኩል፤ እነሱ ራሳቸው ፤ስለ ቦታ ያላቸው መረዳት በመሰረታዊነት ከመከራው ጋር አብሮ የማይሔድ እና የተሰቀለ መሲህ በመስቀል የተቀረጸ እጅግ ያነሰ የህይወት መንገድን ፤እንደሆነ ራሳቸውን መግበውት ነበር፡፡ ስለሆነም፤ስለ ደቀመዝሙርነት የማርቆስ ትምህርት ማዕከል፤ የኢየሱስ መመርያ ቦታን ስለማጣት ነበር፡፡ በሶስቱ ማዕዘናት መመሪያ ውስጥ፤ በመስቀሉ የተቀረጸ ደቀ መዝሙርነት የህይወት መንገድ፤ ስለ ቦታ ሁሉን ነገር አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ ኢየሱስ አስተምሯል፡፡

ሀ. የመጀመርያው ማዕዘን፡ በመሰቀል የተገራ ደቀመዘሙርትነት፤ በአለም እይታ የሚሰጥን ስፍራ ወይም ቦታ መተውን ይጠይቃል፡ ይህ ራስን የመካድ መንገድ ነው፡፡ (ማር 8፡27 —38) የመጀመርያው ጥልቅ ቅድመ ትንበያ፤ በምዕራፍ 8 መጨረሻ፤ ጴጥሮስ ኢየሱስ መሲህ እንደሆነ ከተናገረበት ተከትሎ መጥቷል፡፡ ኢየሱስ ውድ ጊዜን መምረጡ የሚያስደንቅ ነው፤ደቀመዛሙርቱ በመጨረሻ ኢየሱስ ማን እንደሆነ እንዲያዩ እና ሞቱን እንዲካፈሉ ተጠርተዋል፡፡ ጴጥሮስ ኢየሱስን መገሰጹ ፤ ኢየሱስ መሲህ እንደሆነ ፤መንገዱም በእርግጠኛነት ወደላይ እንደሆነ የሚያሳይ ነበር፡፡ ኢየሱስ መሲህ ከሆነ፤ ቦታው(ስልጣኑ) በርግጠኝነት ከህዝቦቹ ፊት የሚሆን አሸናፊ ከሆኑት ወይም ከሚሆኑት እንደ አንዱ ይሆን ነበር፡፡ ኢየሱስ ይህንን መቀበል አይፈልግም፡፡ የመሲህነቱ ማንነት ባጠቃላይ የተለየ ነበር፤ ማንም ያለጠበቀው ነገር ነበር፡፡ ኢየሱስ ጴጥሮስን ሲገስጸው የተመለከተው፤ በጴጥሮስ ግሳጼ ውስጥ የሰይጣንን ሃልንና ቦታን በአስቸጋሪው የመስቀል መንገድ ሳይጓዝ የመቀበል ፈተናን ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ሃሳብ ሳይሆን፤ የሰውን ሃሳብ አንዳሰበ ኢየሱስ ለጴጥሮስ በግልፅ ነግሮታል፡፡ የሰው ሃሳብ ስለ ታላቅነትና ክብርን ፍለጋ ፤ኢየሱስን የተናገረበትን መንገድ ሳይሆን ቦታን በመከተል ውስጥ ነበር፡፡ ይህ ነው ራስን የመክዳት መንገድ፡፡ መስቀሉ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ መመሪያ ነበር፡፡ ራስን መተው፣ እንደ ራስን መካድ፣ ራስን መስቀል፣ ራስን ማጣት፡፡

ሀ. ራስን መካድ ማለት፤ አለም የምታስቀምጠውን መተማመን መካድ ማለት ነው፡፡

ራስን መካድ ማለት ምን ማለት ነው? የራስን ስጦታ፤ የራስን ችሎታ፤ የራስን ተስጦ መካድ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ራስን መካድ ማለት ትክክለኛ ያልሆነን፤ ትህትና ማንሳት ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን አጋጣሚዎችን፤ ወደ ከፍታ መቀየር ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ የመፅሃፍ ቅዱሳዊ መሪነት የሚያሳየው፤በብቃት ሌሎችን መምራት የሚቻለው የመሪነትን ቦታ በመቀይር ወይንም በመተው ነው፡፡ በዓለም አመለካከት ይህ የመጨረሻ ሞኝነት የሆነ ነገር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እንደ አለም አመለካከት ሃይልን (ስልጣንን) ማገኘት ወይንም ማቆየት በርግጥ የስኬት መንገድ ነው፡፡እግዚአብሔር አንዳንዶቻችሁን፤ ከመሪነት ቦታ ወደ ታች ዝቅ በማለት እንድትመሩ፤ በዝቅተኛ ክፍያ ከባድ በሆኑ ቦታዎች እንድትሄዱና እንድትሰሩ ይጠይቃችኋል፡፡ ብትቀበሉትም ባትቀበሉትም ይህ ለእናንተ ራስን መካድ ሊመስላችሁ ይችላል፡፡ አጋጣሚዎችን ሁልጊዜ ራስን ከማስተዋወቅ ጋር መለወጥ ማለት ነው፡፡ ባለፈው ምሽት፤ ሃሳቡን እጅግ ዋጋ የምሰጠው ሰውን ኢሜይል መልሼ ነበር፡፡ በምላሼ ውስጥ፤ ከቀናቶች በኋላ 4000 ቤተክሰርስትያን በስሯ ላሏት፤ የቃለ ህይወት ቤተክርስትያን የበላይ ጠባቂዎች ንግግር ለማድረግ ሄጂ እንደነበር ገለጩ ነበር፡፡ ይህም ጉዳይ ራስን ማስተዋወቅ እንደነበረ ተገነዘብኩ፡፡ በዚያን ጊዜ፤ ራስን መካድ፤ ማለት በኮምፒውተሬ ላይ ያለውን የማጥፊያ ቁልፍ እንደመጫን ነበር፡፡ ሁልጊዜ፤ ነገሮችን ለመግለፅ አጋጣሚዎችን እናገኛለን፤ ይህም ሌሎች ስለእኛ ከፍተኛ ግምት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ራስን መካድ ለነሱ ለመናገር እምቢ ማለት ነው፡፡

1. **ራስን አሳልፎ መስጠት ማለት አለም ለናቀቸው፤ ነገር ቦታ መስጠት ማለት ነው፡፡**

መስቀሉ በኢትዮጲያ አሁን ባለው ባህል ውስጥ፤ የትም የሚገኝ ምልክት ነው፡፡ ሁሉንም የቤተ ክርስትያን ሁነቶችን አስጊጧል፡፡ በእጅ እና ጆሮ ላይ፤ በአንገት አካባቢ የሚደረግ ጌጥ ነው፡፡ ቀሳውስት በእጃቸው በመያዝ፤ ሰዎችን ያሳልሙታል፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች፤ የመስቀሉን ምልክት በራሳቸው ላይ በየቀኑ ይነቀሱታል፡፡ ነገር ግን በቀደመው ዓለም፤ መስቀሉ የቁንጅናና የበረከት ወይም አንድን ጉዳይ የሚገልጽ ምልክት አልነበረም፡፡ እስከ ጭራሹ ምልክት አልነበረም፡፡ ስለ መስቀሉ ማሰብ እንዲያውም አስቀያሚ እና ቀፋፊ ጉዳይ ነበር፡፡ የሰለጠኑ ህዝቦች ስለመስቀሉ አያወሩም ነበር፡፡ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞት ፤ በቀላሉ አሳማኝ የሞት ቅጣት አልነበረም፡፡ የሮማውያን ስልጣንና አገዛዝ ላይ ለሚያምፅ ሰው፤ በሮማውያን ሆነ ብሎ የተዘጋጀ ሰውን የማዋረጃ ክፍል ነበር፡፡ የተሰቀለ ማንም ሰው የተናቀ እንደሆነ ለህዝብ ማሳያ ነበር፡፡ የመጨረሻው የተናቀና የተጠላ ዝቅተኛ ቦታ፤ በዓለም ፊት አንደተሰጠው የሚገልፅ ነበር፡፡ በዓለም ዓይኖች ፊት የተናቀውን ይህንን ስፍራ(ቦታ)፤ ደቀ መዛሙርቱ ለራሳቸው መውሰድ እንዳለባቸው ኢየሱስ ነግሯቸዋል፡፡ በዓለም አይኖች ፊት ካነሰው ፤ማንኛውም ዓይነት ስፍራን፤ በፍፁም መከተል ማለት ነው፡፡

ሐ. ራስን መተው ማለት የራስን ፍላጎት ማስቀደምን ፤ ከፍታን፤ መብትን ወይም ጥቅምን ምንም ነገር አለማስቀደም (አለመቀበል) ማለት ነው፡፡

ለ. ሁለተኛው ማዕዘን፡- በመስቀሉ የተገራ ደቀ መዝሙርነት ቦታን ባጡ ሰዎች ፊት ቦታን መተውን ይጠይቃል፡፡ ይህ የአገልጋይነት መንገድ ነው፡፡ ሁለተኛው የኢየሱስ ጥልቅ ቅድመ ትንበያ የሚመጣው በ9፡30-31 ውስጥ ነው፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ድጋሚ አልተረዱትም ነበር፡፡ የሚያስደንቅ ነበር፤ በርግጥ የኢየሱስን መሞት አስፈላጊነት ለመመልከት አልቻሉም ነበር፤ የሞቱ አስፈላጊነት ፤ምን ማለት እንደሆነ እንኳን ለመጠየቅ ፈርተው ነበር፡፡ ሞቱ አጠቃላ አመለካከታቸው ላይ ተፅእኖ አሳድሮባቸው ነበር፡፡ የመሲሁ መንገድ መከራና ሞትን እንደሚወርሱ ፤ዓለማዊ አመለካከታቸው ይህን እንዳያሰላስሉ እንኳን አድረጓቸው ነበር፡፡ እንደ ባልዋ እንደሞተ ፤መልዕክት ላመጡላት እንኳን በሯን ለመክፈት ፈቃደኛ እንዳልሆነችው ባልቴት፤ ዜናው ዓለሟን የሚያጨልምባት፤ ማሰላሰል አንኳን እንዳትችል አድርጓታል፡፡ ደቀመዛሙርቱ የመሲሁን መከራ ሃሳብ እንኳን ማሰላሰል ያልቻሉበት ምን እንደሆነ ለማሳይት፤ ማርቆስ ወዲያውኑ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ታላቅ ማን እንደሆነ ክርክር ያስነሱበትን ዘግቧል፡፡ ክርክሩ የኢየሱስ መሞትን ቅድመ ትንበያ ደቀመዛሙርቱ እንዳይረዱት ያደረጋቸው ምክንያት እንደነበር፤ ማርቆስ በግልፅ እንድንረዳው የፈለገው ጉዳይ ይህንን ነው፡፡ ታላቅ የመሆን ጥማታቸው ማየት እንዳይችሉ እንዳደረጋቸው፤ መሲሁ ራሱን የመጨረሻ ማድረጉ እንኳን ለመረዳት አድል አልነበራቸውም፡፡

ሀ. አገልጋዮች በማህበረሰብ ውስጥ አነስተኛ ቦታ ያላቸውን አገልግለዋል

9፡33-37ን አብራራ፤ ኢየሱስ መሰረታዊ ዋጋ ያለውን መንግስት በማስታወስ ነው የመለሰው፡፡ የማለዋወጥ ዋጋ፡፡ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ ኋለኛ ይሁን፤ የሁሉ አገልጋይ ሊሆን እንኳን ይገባል፡፡ በጥንቃቄ አስተውሉ፤ ኢየሱስ በዚህ ቦታ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን አልተናገረም፡፡ ደቀመዛሙርቱ ራሳቸውን፤ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደሆኑ ቆጥረው ነበር፡፡ በሺ የሚቆጠሩ አገልጋዮች በዙሪያችን ይኖራሉ፡፡ ማናችን ነን የእግዚአብሄር አገልጋዮች እንዳልነበሩ የቆጠርነው፡ ይህ አይደለም ችግሩ፤ ጥቂት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሲኖሩ፤ ጥቂቶቹ የሰዎች አገልጋዮች ነበሩ፡፡ ይህንን ሃሳብ ለማብራራት፤ ኢየሱስ አንድን ህፃን በደቀመዛሙርቱ ፊት አቁሟል፡፡ በኢየሱስ ቀን ውስጥ፤ልክ እንደኛ ጊዜ፤ አንድ ህፃን የብዙዎችን ሃሳብ ሊሰብ ችሏል፤ ነገር ግን ከማህበራዊ ቦታ አንጻር፤ ህፃናት የመጨረሻ ናቸው፡፡ ኢየሱስ ደቀመዘሙርቱ ህጻናትን ሳይቀር፤ እንዲቀበሉ ተናግሯቸዋል፡፡ ስለ መቀበል የተናገረው የኢየሱስ ቃላት፤ ትህትና ግዴታ በሆነበት የባህል እሳቤ ውስጥ በሚገባ ለረዱት እንደሚገባ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጲያዊ፤ አንግዳን መቀበል ማለት፤ አንግዳውን የግድ ማገልገል ማለት ነው፡፡ የኢየሱስ ቃለት ነጥቡ፤ ከኛ በታች የሆኑ የሚመስሉ ፤ሰራተኛ ማግኘት ሳይሆን ፤ነገር ግን እኛ ራሳችን በማህበረሰቡ ውስጥ አነስተኛ ቦታ ያላቸውን ሰዎች ማገልግለ ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ርቆ በመሄድ፤ በማህበረሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ቦታ ያላቸውን ማገልግል እሱን ማገልግል እንደሆነ ፤እሱን ማገልገል ደግሞ፤ እግዚአብሔርን ማገልገል እንደሆነ ተናግሯል፡፡ በሌላ አባባል፤ የእግዚአብሄር እውነተኛ አገልጋይ ሌሎችን፤ የሚያገለግሉ እንዲያውም በማህበረሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ስፍራ ያላቸውን ማገልገል፤ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ ለምሳሌ፤ በቀደመችው ቤተ ክርስትያን፤ ባልዋ የሞተባትን ባልቴት ያገለግላት የነበረው ማን ነበር? ሐዋርያቶች ራሳቸው ነበሩ፡፡ ለማን ይህንን አቆሙ? ምክንያቱ ባልቴትን ማገልገል ስላስከፋቸው አልነበረም፡፡ ምክንያቱም በሚገባ ባለመያዛቸው ነበር፡፡ ማን እነሱን ተካቸው? ለሌላ ሰው ከነሱ በተሸለ ሁኔታ ሊሰራው ስለማይችል፤ ይህንን ስራ እንስጠው ብለው ነበር፤ አላሉም አገልግሎቱን እንደ ፊሊጵሲየስ እና እስጢፋኖስ ላሉ በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ ለተሞሉ እና ከፍተኛ ወንጌላዊነት ፍላጎት ለነበራቸው ነው የሰጡት፡፡ በመጨረሻም፤ ይህ የሚያሳየን በአገልግሎት ውስጥ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባው ጉዳይ የተገላቢጦሽ ሊሆን እንደሚገባ ነው፡፡ ጊዜ የወለደው አቀራረብ ለአገልግሎት ፤ለህፃናት፤ ከቦታ (ስታተስ) ጋር በተያያዘ ጉዳይ ፤ እንደ ዓለም ሃሳብ እናስባልን እንጂ ፤እንደ ኢየሱስ ቃል አይደለም፤ ይህም እውነታውን ይክዳል፡፡

ለ. አገልጋዮቹ ማንነታቸውን የሚገልፀውን ጉዳይ ሁሉ ትተዋል

9፡38–40 ግለጽ፤ እዚህ *ጋር* ደቀመዛሙርቱ በተለየ መንገድ ለአገልግሉት የወጣን ሰው ሲቃወሙ ነበር፡፡ ከእኛ እንደ አንዱ አይደለም፡ እኛ በምናደርግበት መንገድ አያደርግም፡፡ በስምህ አጋንንትን ያስወጣል፤ ነገር ግን የኢየሱስን ህጋዊ፤ የናዝሬት አገልግሎት አባልነት ካርድ ለማየት ስንጠይቀው፤ አንድ እንኳን የለውም፡፡

ማሰብ ትችላለህ

እግዚአብሔር ስህተት የሆነውን አመለካከታችንን፤ አልፎ የተገኘበት ቦታ ሁሉ እንደሚሰራ የምንገነዘበው፤ እኛ በተለየ ሁኔታ አስፈላጊ ነን ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር አንቅስቃሴ ትኩረቱ ስለሆንን የሚል፤ እንደዚህ ያለ አመለካካት ከአውነተኛው የአገልጋይነት ሃሳብ እንደሌት አንደራቅን ያሳያል፡፡ ትልቅነት ፤ ትልቅ ዝና ስለመገንባት አይደለም፡፡ የኛ አገልግሎት ሰዎችን ስለ ማገልገል ነው፡፡ እናም ጥማታችን ይህ ሊሆን ነው የሚገባው በማንኛውም መንገድ በማንኛወም ሁኔታ የእግዚአብሔር ሃይል ፤የሰዎችን ህይወት ሊነካ ይገባል፡፡ ቁጥር 41 ላይ የሚያገኛኘን ጉዳይ ምን ያህል ትንሽ እንደሆነ ያሳያል፤ በመንግስቱ ውስጥ እኛን ከሌሎች የሚያስተሳስረን፤ በስሜ ዕዋ ውሃ የሚያጠጣችሁ፤ ስለተጠረጠረው የበግ ስርቆት ጉዳይ በጣም ስንበሳጭ እንገኛለን፡፡ አብዛኛውን ጊዜ፤ ስላልጠፋው በግ የተሟላ መንፈሳዊ ህይወት ግድ የላቸውም፤ ነገር ግን ሌሎች ቤተክርስያኖችን ለማገዝ ፈቃደኛነትን ሲያሳይ ይታያል፡፡ እኛን የሚያሳስበን፤ የአባላቶቻችን ቁጥር መቀነስ ፤ቦታችንን የማጣት ፍርሃት እና ተፅዕኗችን ይጠፋል ብለን ነው፡፡ እግዚአብሔር በርግጥ መካነ የሱስን ወይም ሙሉ ወንጌልን በሚቀጥሉት ዓመታት ውስጥ በአባላትና በቤተክርስትያን ቁጥር ከቃለ ህይወት ይልቅ ቢባርካቸው ምን ይሰማሃል፡፡ቃለ ህይወት ትልቁ የወንጌላውያን ተዕእኖ ቢኖራት ፤ ምን ያህል ኩራት ይሰማሃል በመስቀል የተቀረጸ ደቀ መዛሙርትንት በሌሎች ደቀ መዛሙርቱ ፊት የራስን ነገር መተውን ይጠይቃል፡፡ይህ ራስን የማቅረብ መንገድ ነው፡፡ (10፡32-45) በቁጥር 42 ላይ ያለውን ፅሁፉ አብራራ፤ ስነጽሁፋዊ በሆነ መልኩ በሌሎች ላይ ገገር ለመሆን ስለሚፈልጉ ሰዎች አብራራ፡፡ አንተን መሪ ያደረገህ አንድ ነገር ቢኖር፤ ተከታይ የመኖርህና ያለመኖርህ ጉዳይ አይደለም፡፡

ሀ. ቦታ የራስን ፍላጎት በመግለጽ፤ ማዕረግ በመቀበል ሳይሆን ፤ራስን አሳልፎ በመስጠት ነው፡፡ አብዛኞቻችሁ እንዳላችሁበት፤ ለእግዚአብሔር መከራን መቀበል አንድ ጉዳይ ነው ፡፡ ስለ ሌሎች መከራን መቀበል ግን ሌላ ጉዳይ ነው፡፡

ለ. ቦታ ራስን በማስተዋወቅ ማዕረግ በመቀበል ሳይሆን፤ ነገር ግን በመለኮታዊ መብት ውስጥ ነው፡፡ ከቁጥር 35–40 ውስጥ፤ ያቆብና ዮሐንስ ባዶ (ራቁት) የሆነ ራስን ማስተዋወቅ ውስጥ ሲገቡ አይተናል፡፡ ታላቅ ልትሆን እንደሆነ አውቀናል፤ እናም በክብርህ ጊዜ በቀኝና በግራህ መሆን እንፈልጋለን፡፡ ልክ እንደ ያቆብና ዩሐንስ፤ እኛ ራሳችን ለስልጣን (ለቦታ) ሁልጊዜ ስንታገልና ስንጨነቅ ና ስኬታማም ስንሆን እንገኛለን፡፡ ነገር ግን ስኬት የምናገኘው በሰው አይን ቦታን ስናገኝ ብቻ ነው፡፡ በእግዚአብሔር አይን ቦታን የሚሰጥ፤ ብቸኛው አንዱ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ረስተናል፡፡

ቅጣይ

በወደፊቱ የእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ያለ ቦታ (ስልጣን)፤ የራሳቸውን ቦታ በአሁኑ ጊዜ ለተዉ ደቀመዛሙርቶች የሚሰጥ ነው፡፡ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ መሪ እንዲሆኑ አልጠራቸውም፡፡ ተከታይ እንዲሆነ ጠርቷቸዋል፡፡ የመስቀሉን መንገድ የሚከተሉ ሰዎች እንዲሆኑ ጠርቷቸዋል፡፡.መፅሃፍ ቅዱሳዊ መሪነት፤ በዓለም ካለው መሪነት የተለየ ነው፡፡ መፅሃፍ ቅዱሳዊ መሪነት በሌሎች ላይ የበላይ ከሚያደርገው መሪነት፤ *ጋር* ምንም የሚያገናኘው ጉዳይ የለም፡፡ ፍፁም ተቃራኒ ነው፤ የቅድመ ውጥረት የነገሰበትን፤ ቦታ (ስልጣንን) በመተው ከሚመጣ የተሰቀለውን ኢየሱስ ከመከተል *ጋር* የሚያገኛኘው ጉዳይ ነው ያለው፡፡ የጳውሎስ ቃላት በዚህ ረገድ የሚነግረን፤ ተከተሉኝ ምክንያቱም እኔ የእናንተ እግዚአብሔር የቀባኝ መሪያችሁ እና በእናንተ ላይ ስልጣን የተሰጠኝ ነኝ አይልም፡፡ እኔ ኢየሱስን እንደ ምከተል እኔን ተከተሉ ነው ያለው፡፡ ኢየሱስ ህዝቡን የጠራው መሪዎቹን እንዲከተል ሳይሆን ተከታዮችን እንዲከተል ነው፡፡ እናም ኢየሱስን ለመከተል ቦታችንን ሁሉ መተው የግድ ነው ፤ ራስን በመካድ መንገድ ውስጥ ያለውን የመስቀሉን ጉዞ መጓዝ ነው፡፡

መ. የወንጌሉ ቀጣይነት

ማርቆስ 1፡1 የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመርያ የሚለው ቁጥር ፤እንደ መፅሃፉ መግቢያ ተደርጎ ያገለግላል፡፡ በርግጥ መፅሃፉ ድንገተኛ በሆነ መልኩ ለምን አንደሚያበቃ ጠቃሚ የሆነ ሃሳብ ማሳያ ነው፡፡ የፍጻሜው ድንገተኛነት ቀድሞ የነበሩትን ክርስትያኖችን አውኳቸው ነበር፡፡ አስገራሚው ፍጻሜ የቀደምት ጊዜ ክርስትኖችን ይረብሻቸው ነበር፡፡ በአንዳንድ ትርጉም ውስጥ ተካቶ የሚገኝ ረጅም ፍጻሜ አለን፤ የመካተቱ ማስረጃ የዘገየ ቢሆንም እንኳን፡፡ ሌሎችም የተለየው ፍጻሜ ወንጌሉ ሲዘዋወርና ሲተላለፍ በቅርብ እንደጠፋ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ፡፡ ይሁንና፤ እንግዳ የሆነውን አስገራሚ ፍጻሜ፤ ደማቅ ከሆነው የተለየ ፍጻሜ

ጋር ማጣመር የተሻለ ይመስላል። መልዕክቱ የኢየሱስ ወንጌል መጀመርያ የሚመስል መሆኑ ነው፤ ከህይወቱ፤ ከሞቱ እና ከትንሳኤው ትረካ ጋር የመጣው መጀመርያው ብቻ ነው። የቀረው ታሪክ ኢየሱስ እስከሚመለስ ድረስ የሚቀጥል ይሆናል። ነገር ግን መጀመርያው ወሳኝ ነው፤ የሚቀጥለውን ባህሪ በፍጹም ይወስናል። ስለኢየሱስ በወንጌሉ የሚመጣው የአዳኙ የመጨረሻ ጊዜ የእግዚአብሔር ግዛት የተዋወቀበት እና ደህንነትን በራሱ መከራና ሞት ያሳካበት ነበር። ይሁንና ከዚያም የአሁኑን የተከታዮቹን ህልውና በማዳኑ ህግ ልምድ የሚያደርጉ ብቻ ሳይሆን ከመከራው ጋር በተጨማሪ ሲያያዝት በሃይል የተነሳበት በሚወስን መልኩ ያቀናጃል። በሰይጣን ላይ የተደረገውን የተሟላ ድልም በተጨማሪ ይወስናል፤ በዚህ ዓለም ያለን የጥላቻን ሃይል በትንሳኤው አስወግዶ፤ የወንጌሉን የመጨረሻ ነፃ አውጪነት ኢየሱስ በሃይል እንደሚመለስ ለሚያምኑ ተስፋን ሰጥቷል። የአንድ ሁነኛ ደቀ መዝሙር ምላሽ ገና በአየር ላይ ቀርቷል። ምን ያደርጋሉ ይህ ምናልባት የማርቆስን ብልህንት የሚያሳይ ነው።ታሪኩን ክፍት አድርጎ በመተው፤ አንባቢውን ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲያውቅ ጋብዟል። በወንጌሉ ውስጥ የተወሰነው ፍንጭ፤ ማለትም ማርቆስ የነገረን ታሪክ መጀመርው ብቻ እንደሆነ እንደሚያምን ፤ በመግለፅ ከዚህ ጠንካራ አድናቆት ጋር ይተወናል። በማርቆስ 16፡7 ውስጥ መልዓኩ መመሪያን ሰጥቷል። (የ14፡28 ፍፃሜን) ደቀመዛሙርቱ ወደ ገሊላ በመሄድ ኢየሱስን መጠበቅ ነበረባቸው። በማርቆስ 1፡8 ውስጥ ዮሐንስ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቁን ያወጀ ሰው ነበር። ሆኖም፤ በወንጌሉ በየትኛውም ስፍራ፤ ቅድመ ትንበያው ወደ ፍፃሜ እንደመጣ የሚያሳይ የለም። ስለሆነም፤ የያዕቆብ ቃላቶችና ዮሐንስ 10፡39 ውስጥ ሁሉም ወደ አእምሮአችን የሚያጭረው ሃሳብ፤ የራይትስን የአዲስ ኪዳን ስልጣን ባህሪን አስተያየት ይሰጣል፤ ባጠቃላይ፤ በድራማ የመጀመርያው የጨዋታ ክፍል እንደሚሰጠው ገፀ ባህሪን ይመስላል። እንደተነገረው በመጀመርያው ክንውን ላይ ጨዋታውን እውነተኛ በሆነ መንገድ መጨረስ ነው። እናም የማርቆስ ፍጻሜ የተሰጠን ጅማሬው ብቻ እንደሆነ ይሞግተናል። ነገር ግን በዚህ መንገድ ልናተኩርበት የሚገባው ዋናው ጉዳይ ሊሆን የሚችለው ውድቀት ነው።

የትረካው ፍጥነቱና ድምፀቱ

ሀ. በማርቆስ ውስጥ ያሉ ድርጊች ፈጣኖች፤ የሚስቡ በተከታታይ የተለያዩ ቦታዎች ውስጥ የሚከሰቱ እና አነስተኛ የሆኑ ትምህርቶችን እንደያዘ እንመለከታለን። ለአንባቢዎች ስለመልዕክቱ በቀጥታ መንገድ ከማሳየት ይልቅ፤ ለመንገር ጥቂት ተብሏል። ምዕራፎቹ ግልጽ ናቸው። ማርቆስ በተደጋጋሚ ወዲያውኑ የሚል ቃል ተጠቅሟል። ውጤቱ ፤ ስለንስሃ አስፈላጊነት ዘመኑ መፈፀሙንና መንግስቱ የቀረበ መሆኑን፤ በሚያሳይ ብርሃን ውስጥ ያለውን ከኢየሱስ ማዕከላዊ መልዕክት ጋር ላለው ትረካው ፈጠን ያለ ድምፀት ለመስጠት ነው።

ለ. ነገር ግን በመጨረሻ፤ ፍጥነቱ ድራማዊ በሆነ መልኩ ይቀንሳል። በወንጌሉ መጨረሻ፤ ድርጊቶች ቀን በቀን ከዚያም ሰዓት በሰዓት፤ የኢየሱስ በኢየሩሳሌም መሞትና መነሳት ላይ ያለውን ጠቀሜታ ላይ ትኩረት አድረጎ በማስቀመጥ ይገልፃል።

ምፀት

ምፀት ማለት በቀላሉ ተቃራኒ ትርጉም ያለው ንግግር መናገር ማለት ነው

1. የአይሁድ ንጉስ፡- ኢየሱስን የሰቀሉት ወታደሮች፤ የአይሁድ ንጉስ እንደሆነ ጠርተውታል ነገር ግን እውነቱ ግን በሚያስቅ ሁኔታ አንድም ሰው በፍጹም አሱን እንደንጉስ አላየውም፤ በተለይ አሳፋሪ በሆነበትን እና በሚሰደብበት ቦታ በመስቀሉ ላይ። አዚ ቃለዊ ምፀት ብቻ ሳይሆን፤ ደራማዊ የሆነ ምጸትም ነበር፤ ይህን ለማየት የመጡ ለአንባቢዎች ፤ ከመሰቀሉ ውጭ በርግጥም የአይሁድ ንጉስ ነበር። በተመሳሳይ፤ ማን እነደመታው ትንቢት ተናገር ይሉት ነበር፤ ነገር ግን አንባቢዎች እሱ በርግጥም ነቢይ እንደነበር አውቀዋል። ኢየሱስ ቤተመቅደሱ እንደሚያፈርስ በማሾፍ ተንጓጧል፤ ነገር ግን አንባቢዎች በርግጥም ቤተ መቅደሱ እንደሚጠፋ ያውቅ ነበር።በመጨረሻም፤ ራሱን ከመስቅል በማውረድ እንዲያድን ተነግሮታል፤ ነገር ግን አንባቢዎች የኢየሱስ ህይወት ዘላለማዊ (የሚድነው)፤ ሕይወቱን በሞት ሲያጣ ብቻ እንደሆነ ተረድተዋል።
2. አብዛኛው ይህ ምፀት፤ የትልቁ ምፀት ክፍል ነው፤ አብዛኞቹ የእግዚአብሔር ማዳን መንግስት ውስጥ የሚቀበለትና የሚካፈሉት የሚጠብቁት አልነበረም፤ በርግጥ መንግስቱ የሚመሰረተው ከሞቱ በኋላ በሚሆነው ነገር ውስጥ ነበር አቋማቸው።
3. የስዕሞን ስም ወደ ኬፋ (ጴጥሮስ) መቀየር ሌላኛው ምፀት ነው። ትርጓሜውም አለት ማለት ነው፤ ጴጥሮስ ምንም ነው ነገር ግን ዓለት እንደሆነ በትረካው ውስጥ ተገልጽዋል።
4. በዚህ ሁሉ ውስጥ፤ የማርቆስ ምፀታዊ አጠቃቀም ፤ እግዚአብሄርን እንደ አንድ ከግምቶች በተቃራኒ እንደሚያደርግ፤ ከሃይሉ ማዕከል የራቀ፤ በመከራ የሚያልፍ መሲህ፤ የእስራኤልን ተስፋ ቃል የሚያስፈፅምና ከእስራኤል ተቃራኖ ያለው፤ ከሰናፍጭ ቅንጣት ጋር ሊነጻጸር በሚችል መንገድ መንግስቱን መመስረት ይገልጻል።

ዋና ዋና ነጥቦች

ሀ. ኢየሱስ እውነተኛ መሲህ ነው፡፡

ለ. የኢየሱስን ማንነት ከፍ ባሚው መለየት የማይችል ነው፡፡

መመዘኛ መልመጃዎች

መመሪያ አንድ፡ የሚከተሉትን አርፍተ ነገር በጥንቃቄ በማንበብ ፤ጥያቄዎችን መልስ፡፡

1. የመፅሃፉ ዓለማ ምን ያሳየናል?
2. ማርቆስ ኢየሱስን አንዴት ያቀርበዋል?
3. የወንጌሉ ቁልፍ ቁጥር እና መዕከላዊ መልዕክቱ ምንደን ነው?
4. ማርቆስ ለማን ፃፈው?
5. በመጽሃፉ በስፋት ያለው ቀልብን የሚይዘው ባህሪ የቱና የቱ ነው?
6. ማርቆስ የጌታ ራትን ልምድ ዘግቦ ይሂል?
7. ማርቆስ ወንጌል ውስጥ ታላቁ ተልዕኮ ተሰጥቷል ወይ?

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ተዛመጅ ካሳቸው ክፍሎች ጋር በማያያዝ መተነተን</u>

<u>መግቢያ</u>

ይህ የሞጁሉ ክፍል በእየንዳንዱ የማርቆስ ወንጌል ምዕራፎች ውስጥ ያለውን ስነ መለኮታዊ እንድምታውን እናያለን፡፡

ዓላማው

ይህንን ክፍል በብቃት ካጠናቀቁ፤ ተማሪዎች

- በማርቆስ ወንጌል ውሰጥ ያሉትን የፅሁፎች ትረጉም ይረዳሉ
- ከመፃህፉ አንዱን በመውሰድ የራሳቸውን ዔክሰጅቲካል ስራ እንዲያቀርቡ ይበረታታሉ

ውድ ተማሪዎች

---

i) ማርቆስ 1፡2-8፤ ማርቆስ ወንጌሉን ከብሉይ ኪዳን ምንጭ በመጥቀስ ይጀምራል፡፡ ምንጩም የትንቢተ ኢሳያስ መለያ አለው፤ በርግጥ ሁለት ፅሁፎችን አንድ ከኢሳያስ 40 እና አንድ ሚል 3፡1 ደባልቋል፡፡ ማርቆስ በሚልኪያስ 3፡1 ውስጥ ለአንት የሚለውን ተውላጠ ስም ለእኔ በሚለው መሻሻሉ የሚያስደንቅ ነው፡፡ ይህ በሚልኪያስ ውስጥ ያለው እኔ እና በኢሳያስ 40 ጌታ ተብሎ የተጠቀሰው ያህዌ ፤ ለማርቆስ ስነ ክርስቶሳዊ አበርክቶ እንዳለው በግልፅ አሳይቷል፡፡ የዮሐንስ አገልግሎት የኢሳያስ ፤በምድረ በዳ የሚጮህ ድምፅ ፍፃሜ እና የሚልኪያስ ኤልያስን የሚመስል መልዕክተኛ፤ነገር ግን ለሚመጣው ለያህዌ ለራሱ መንገድን የሚጠርግ፤ መምጣቱ ከኢየስስ መምጣት ጋር የሚስተካከል የሚመስል ነጥብ አለው፡፡ ሁለቱ ምንጮች ፤ የኢየሩሳሌም ወደ ቀድሞ ሁኔታ መመለስንና የኤልያስ መመለስ ያላቸውን ሁለት ወሳኝ እስካቶሎጂ ሃሳቦችን ግንኙነት ለመረዳት ሁለቱ ጭብጦች ጠቀሜታ አላቸው፡፡ በዮሐንስ መምጣት፤ የእስራኤል መመለስን ጊዜ አንደደረሰ እና የኤልያስን መምጣት የጌታ ቀን ከመጠናቀቁ በፊት እንደሚሆን ማርቆስ ያስታውቃል፡፡

ii) ማርቆስ 1፡12 ማርቆስ ስለ ፈተና የተናገረው ምንም ነገር የለም፤ በስነ መለኮት ጉብዝና በሰይጣን፤ በዱር እንሰሳት እና በመላዕክት ከመፈተንን ልምድ ጋር ያያይዘዋል፡፡ ለማርቆስ ግልፅ አልነበረም፤ ኢየሱስ እየደጋገም የእስራኤልን ልምምድ በጫካ ውስጥ እንደ ማቴዎስ ማርቆስ ፍላጎት ሌላ ቦታ የሚያርፍ ይመስላል፡፡ የሰይጣንና የክፉ ግንኙነት፤ በተገቢው አኳኋን ቀጥተኛ ነው ፡፡ በሰይጣን ላይ ድል እንዳገኘበት ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ ፤በአጋንንትም ላይ ድሉ በቀረው ወንጌል ሁሉ ላይ ይጠበቃል፤ የፃድቃን ተፈጥሮአዊ አጋር በሆኑት መላዕክት ተገልግሏል፡፡ ነገር ግን የዱር እንሰሳቱ መጠቀስ ግን ያነሰ እውነት ነው፡፡ ያንን ለማለት፤ ፡በቀላሉ የምድረ በዳው ቦታ አካል ክፍል ነበሩ፡፡ የኢየሱስን መለየት ትኩረት መሰጠቱ እንግዳ

ያስመስለዋል፤ ምክንያቱም ሁሉም ነገር በስነ መለኮት ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ነው። በአንቀፁ መረዳት ውስጥ ፤ ሁለቱን ኪዳኖች በሚያያይዘው ስነ ፅሁፍ፤ በፅድቅና በሃጢያን መካከል በሚናገረው የተለያዩ መሆኑ ክፍሎችን ከሚያገናኘው ውስጥ ነው፡ እግዚአብሄር፤ ሌሎች ሰዎች፤ ሰይጣን፤ መላዕክት እና የዱር እንሰሳት።። አንዳንዶች የራሳቸውን ሃሳብ እንዲህ በማለት ይሰጣሉ፤ የዱር እንሰሳት እንደ ሰይጣን አጋር ሆነው፤ ኢየሱስን በመቃወም እንደፈተኑት ታይቶ ነበር። ነገር ግን ምናልባት፤ አንደ ሆሴ 2፡18 እና በተለይ ኢሳ 11፡6-9 ወደ ኋላ ያሉትን አንቀፆች መመልከት የተሻለ ነው።እነዚህ አንቀፆች የመሲሁን ዘመን ፤የዱር እንሰሳት አንደ ፈታና የመቁጠር ሂደት ከዚህ በኋላ አይጠበቅም። ነገር ግን በተለየ መንገድ፤ በፍጥረት ውስጥ የመሲሁን ሰላም ከመመለስና ከመመስረት ጋር ይያያዛል። ይህ መመለስ እንደ አንዱ በኢየሱስ የመጣ የመጨረሻው ዘመን ጥናት፤ የደህንነት አሰራር ተደርጎ የተገለፀ ነው። (See R. Bauckham in Jesus of Nazareth: Lord and Christ.)

iii). ማርቆስ 1:14-5 -ለአጠቃላዩ የማርቆስ ወንጌል፤ ፕሮግራማዊ መገለጫ የአሁን ጊዜ ይዘት አለው። ጊዜው ፍጻሜ እንዳገኘ፤ የፍፁማዊ ሰዋስው መንግስቱ የመቅረቡን እውነታ ከመግለፅ ያለፈ ነው በማለት ሃሳብ ያቀርባል፤ እውነታው ግን አንደደረሰ ያሳያል።

iv). ማርቆስ 2:1-3:6 ከዚህ ማስተዋወቅ እና ከደቀ መዛሙርቱ መጠራት በኋላ፤ የመንግስቱ መቅረብ ወዲያውኑ ተቃውሞና ግጭት እንደሆነ በግልፅ ታይቷል። ግጭቱም ከተፈጥሮ ሃይላት ጋር፤ ከሰይጣን ጋር እና ከበሽታ ጋር ነበር፤ ግጭት ከአይሁድ ባለስልጣናት ጋር፤ግጭት ከደቀ መዛሙርቱ እንኳን ሳይቀር ነበር። በዚህ ክፍል ውስጥ፤ አምስት ክፍሎች ይገኛሉ። ክፍሎቹም በኢየሱስ ስልጣን ላይ እና በአይሁዳውያን መሪነት ልዩነት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።በመጀመርያውና በአምስተኛው፤ በፈውሱና በኢየሱስ ላይ ያልተነገረ ክስ መካከል ተያያዥነቱን ያደርጋል። ነገር ግን አንዲሁም በሁለተኛውን በአራተኛው የአይሁደ ህግን በተቃረነ መልኩ የተመገቡበት መንገድ ላይ ትኩረት ያደረጉት ማለት ነው። በመሃል ውስጥ፤ ለጥያቄዎቹ የኢየሱስ መልስ አምስቱንም ክፍሎች አጉልቶ ያሳያል። የሙሽራው መምጣት አዲስ ሁኔታን ይፈጥራል፤ የተለየ አዲስ ተግባርን ጠርቷል፤ አሮጌው የባህልና የህግ ክፍፍል እና ለመግለፅ በቂ አልነበረም፤ በኢየሱስ የመጣው አዲስነት ፍርድ ሰጥቷል።

v) ማርቆስ 4 - ማርቆስ ስለ ምሳሌዎቹ በርቀት ተናግሮናል። በማርቆስ 4 ላይ የተሰጠው የኛ አስተያየት ግልፅ ሊሆን ይችላል። ማርቆስ በሚነግረን ምሳሌ ውስጥ የሚገጥምን አስቸጋሪ ጉዳዩ፤ በማርቆስ 4 ላይ ሊኖረን የሚችለው አስተያት የማርቆስ ምሳሌዎች ፍጽመነት ላይ የሚገጥመንን ተግዳሮት ፤ አስቸጋሪው እውነታ ሚስጥሩ የተገለፀው በውስጥ ላሉት እንደሆነ የተነገረው ሃሳብ ላይ ነው።ደቀ መዛሙርቱም በወንጌሉ ውስጥ ሁሉ አልተረዱትም፤ ሳይረዱትም ቀርተዋል። ፈተናው ልክ እንደ አራተኛው አፈር ከሆንን፤ ደቀ መዛሙርቱ በግልፅ ያገኙት ፈተና አይሆንም። አንድ ሰው እንደሚያገኘው እንኳን ፈተና አይሆንም።ስለሆነም፤ ምሳሌዎቹ ተስፋን ይዘዋል። እንደተባለው፤ በኢየሱስ በራሱ ታረክ አውድ ውስጥ፤ ማንኛውም ያነሰ ውጤት፤ በወንጌል ውስጥ ተስፋ የተገባው የሚሰበሰበው ነዶ፤ ማፍራቱ የማይቀር ነው። ማርቆስ 4 ብቻ እንኳን ብንመለከት፤ ደቀመዛሙርቱ በምንም መልክ በግንዛቤ ከሌሎች የተለዩ እንደነበር የምናውቅበት መንገድ የለም።በርግጥ፤ በወንጌሉ ኋለኛው ክፍል፤ የደቀ መዛሙርቱ ልብ ደንድኖ እንደነበር ተነግሮናል። (6፡51-2). ኢየሱስ ደቀ መዘሙርቱን እንዲህ በማለት ጠይቋቸው ነበር፤ እስካሁን አትመለከቱምን አታስተውሉምና ልባችሁ ደንድኗል ፤ አይን አላችሁ ግን አትመለከቱም፤ ጆሮ አለችሁ ግን አትሰሙም። እዚህ ቦታ ደቀመዛሙርቱ በውጭ ካሉት በተሻለ ሁኔታ መለየት አንደማይችሉ ተደርገው ተገልፀዋል። ነገር ግን፤ ደቀ መዛሙርቱ መመልከት ካልቻሉ ፤ ምናልባትም እንደሚያዩ ተስፋ ቀርቶላቸዋል። ነገር ግን ለነሱ የማይቻል ነው። (10፡26-7) በማያሻማ መንገድ የሚያረጋግጠው ነገር ቢኖር ማን እንደሚመለከት ለመወሰን የሚችለው እና ማን ከኢየስስ ጋር ብቻ እንደነበር ነው። የማየትና የመስማት ጉዳይ በፍፁም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ውስጥ ነው፤ ወንጌሉ የሚያመላክተው ማየትና መስማት አንዴ ደቀ መዛሙረቱ ከኢየሱስ ሞት ጋር ወደ መያያዝ ሲመጡ ሊሆን የሚችል ብቻ ነው። ከዚያም በኋላ ምስጢር የሆነው ይገለጣል፤ ከጣራም በላይ ይታወጃል።

vi). ማርቆስ 7 - ማርቆስ 7 በኢየሱስና በፈሪሳውያነ መካከል ስለ መንፃት ወይም ንፅህና በተነሳው ጥያቄ ላይ ግልፅ ልዩነት እንዳለ ይክዳል። መንፃት ከሰውነት ላይ አንድ ሰው በተደጋጋሚ ቆሻሻን ከሰውነት ላይ ከማስወገድ ጋር ምንም የሚያያይዘው ነገር የለም። ከተወሰኑ የሃይማኖት ሁኔታዎች ጋር ተያያዥነት ካለቸው፤ በብሉይ ኪዳን ህግ እንደ አለመንፃት ፍቺ ከተሰጠባቸው ጉደዮች ጋር ይያያዛሉ። ለምሳሌ፤ ከመውለድ በኋላ፤ በሰው ላይ በሚመጡ አንዳንድ ነገሮች፤ በቆዳ ላይ የሚከሰቱ ጉርብርታዎች ወይም የቆዳ ችግር (ቁምጥና ነገር ግን በአሁን ጊዜ ቁምጥና ከምንለው የተለየ) ወዘተ።; በብሉይ ኪዳን ውስጥ እነዚህ አለመንፃቶች የተለየ ችግር አልነበረባቸውም። የማይቀር የህይወት አካል ተደርገው ይታዩ ነበር። በሌላ አባባል፤ የሚያጠፉ አልነበርም። ይህንን ለማጥፋት አለመሞከር ግን እንደችግር ይወሰዳል፡ ግልፅ ባለ ሁኔታ የአስራኤል ቅድስና የተገለፀው ይህንን አለመንፃት ከማስወገድ ጋር ነው። ከዚያም ይህን ማየት ቀላል ነው። ፈሪሳውያን ወደዚ አመለካከት እንዴት እንደመጡ፤ ቅድስና በቀላሉ የተበላሸን ነገር ሲከሰት ከማስወገድ ጋር

ሳይሆን፤ ነገር ግን በተቻለ መጠን እንዳይፈጠር መከላከል ነው ። ይህ ለእጅ መታጠብ ልምምድ መነሳት ምክንያት ሆኗል። ይሁንና ኢየሱስ ከተበላሸው ነገር ጋር የተያያዘ ጥያቄ ሲነሳለት ደስተኛ አልነበረም። ሁሉም ካለመንፃት ጋር ተያያዥነት ያለቸው ጉዳዮች ፤ ከቅድስና ጋር ተያይዘው ከሚነሱ ጥያቄዎች ጋር አግባብነት የሌላቸው እንደሆነ ኢየሱስ ይሞግታል። ንፁህ ባትሆንም እንኳን፤ ቅድስናህን ካንተ ሊወስደው አይችልም። ቅድስናን ሊጎዳ የሚችለው ነገር በውስጣችን ያለው ክፋት ነው ። ቁ. 15 ከሰው የሚወጡት ሰውን የሚያረክሱ ናቸው እንጂ ከሰው ውጪ የሚገባውስ ሊያረክሰው የሚችል ምንም የለም፤ ወደ ልብ አይገባም ነገር ግን ይልቁንም ወደ ሆድ ከዚያም ወደ እዳሪ ተብሎ ተተርጉሟል። ስለዚህም ቅድስናውን ከሱ ሊወስድበት አይችልም።የአንድ ሰው ቅድስና በልብ ውስጥ በሚኖረው ክፋት ሃሳብ፤ ግብረገባዊ ባልሆነ ነገር፤ ንፉግነት ወዘተ ወዲያውኑ ረክሷል። በሌላ መልኩ፤ ንጽህናን አንደቅድስና መገለጫ አድረጎ መከተል የሌለን ነገር አንደመከተል አስቂኝ ይሆናል። እነዚህ ሁሉ ነጥቦች ወደ ኢየሱስ ስንምግባር ነጥቦች፤ ትኩረት ወደ ተሰጣቸው ትረጉም አልባ ወደ ሆኑት ከቅድስና በተለዩት ሃይማኖታዊ ምልክታዎች ያመራናል። ችግሩ በኢትዮጲያ ውስጥ ካሉት ኦርቶዶክስና ሙስሊም ጋር አይገናኝም። እኛ እንደ ወንጌላውያን አማኞች የራሳችን የሆነ የቅድስና መገለጫ አድርገን የምንጠቀምበት ሃይማኖታዊ ምልክታ አለን። በመዘምራን ውስጥ መካፈል፤ አልኮልን ማስወገድ ወይም የተለየ የአለባበስ ሁኔታ ለሆን ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ምንም ዋጋ የላቸውም እንደ ቅድስና መገለጫ ፤ቅድስና ራሱን ስተነዋል ማለት ነው።

